# Pentateuch

Old Testament One

**Radiante Theological Seminary**

Course No. BIB102

# ማውጫ


መግቢያ

I. የኮርሱ አላማ

**ምዕራፍ አንድ**

II. የጥንታዊ ሚሶፖታሚያ ታሪክ

ቅድመ አባቶች እና የአባቶች ዘመን

**ምዕራፍ ሁለት ዘፍጥረት፡ ቅድመ አባቶች እና የአባቶች ዘመን**

1.1. ፍጥረት፣ ውድቀት እና መዋጀት (መቤዠት)

1.2. የጥፋት ውሃ

1.3. የአባቶች ዘመን

- የአብርሃም ታሪክ
- የይስሐቅ እና የያዕቆብ ታሪክ
- የዮሴፍ ታሪክ

**ምዕራፍ ሦስት፡ ዘጸዓት ከባርነት ወደ ነጻነት**

የመጽሐፉ አጠቃላይ መግቢያ

2.1. የዘጸዓት መጽሐፍ

2.2. የእስራኤል የግብጽ ባርነትና የሙሴ መጠራት

2.3. የሙሴ ተልዕኮ

2.4. ወደ ሲና የተደረገ ጉዞ የእግዚአብሔር ህግና የመገናኛው ድንኳን

**ምዕራፍ አራት፡ ዘሌዋዊያን "አምልኮና አገልግሎት"**

3.1. መስዋዕቶችና ካህናቶች

3.2. የዘሌዋዊያን መጽሐፍ

3.3. የእግዚአብሔር መገኘት

3.4. መንጻትና ሌሎች ህጎች

**ምዕራፍ አምስት፡ ዘኍልቁ እግዚአብሔርን ማገልገል**

4.1. የዘኍልቁ መጽሐፍ

4.2. እስራኤል በሲና

4.3. ከሲና ወደ ቃዴስ

**ምዕራፍ ስድስት፡ ዘዳግም ‹‹የምድረበዳው ቆይታ››**

5.1. የመጽሐፉ አከፋፈል

5.2. የመጽሐፉ ዝርዝር ሂደትና አበይት ተግባራት

**ማጠቃለያ**

**የአምስቱ የሙሴ መጽሐፍት ስነመለኮት**

ዋቢ መጽሐፈት

# የትምህርቱ አጠቃላይ መግቢያ

የመጀመሪያዎች አምስት የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት "ፔንታቱክ " ከዓለም አፈጣጠር ተነስቶ እስከ ሙሴ ሞት ድረስ የሚቀጥል ታሪክ የያዘ የትረካ መጽሐፍት ነው። እነዚህ መጽሐፍት የህግ ዝርዝር ስለሰፈረባቸው ሙሉ በሙሉ የህግ መጽሀፍት ናቸው ማለት አንችልም ደግሞም የትውልድ ታሪክ ዝርዝር ስለያዙና የትውልድን ታሪክ ስለያዙ እንዲያው በጥቅሉ የታሪክ ዘጋቢ ብቻ አድርገን የምንወስዳቸውም አይደሉም። እነዚህ መጽሐፍት እስከዛሬ የመኖራቸውም ምክንያት ያለፈውን ታሪክ እያስታወስን እንድንደሰትም አይደለም። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ህዝብ ከምን አይነት አምላክ ጋር ህብረት እያደረጉ እንደሆነ እና እንዴት ህብረት ማድረግ እንደሚገባቸው ስለ እግዚአብሔር ባህሪ ለማስተማር ነው።

በጥቂቶች የስነ መለኮት ጠበብት ሙሴ እንደጻፋቸው ባይታመንም እንኳ አምስቱን የህግ መጽሐፍት ማለትም ዘፍጥረት፣ዘጸዓት፣ዘህልቁ፣ ዘሌዋዊያንና ዘዳግም በአብዛኛው የስነመለኮት ምሁራን ዘንድ ሙሴ እንደጻፋቸው ስምምነት አለ። ሁሉንም ወይንም ጥቂቶችን መጽሐፍት ሙሴ አልጻፋቸውም ብለው የሚሞግቱ ምሁራን በመጨረሻው የእስራኤል ታሪክ አካባቢ በሌላ ሰው ተጽፎ ሊሆን ይችላል ይላሉ።

ይህ ኮርስ ሶስት ዋና ዋና ዘመናትን 1) ቅድመ አባቶች ዘመንን 2) የአባቶችን ዘመን እና 3) የእስራኤልን የመካከለኛውን ዘመን ያጠቃልላል። የመጀመሪያው ምዕራፍ የመጀመሪያውንና የሁለተኛውን ዘመን ይዳስሳል። የቀሩት የትምህርቱ ሶስት ምዕራፎች ሶስተኛውን ዘመን ማለትም የእስራኤልን የምድረበዳው ረጅም ህይወት ይዳስሳሉ። የኖህ ዘመን ታላቁ የውሃ ጥፋት ከቅድመ አባቶች ዘመን ታሪክ ወደ አባቶች ዘመን መሸጋገሪያ ሁኖ እናየዋለን። በመሆኑም ምዕራፍ አንድ በዮሴፍ ሞት ታሪክ ይደመደማል።

በዚህ ትምህርት የእስራኤልን ታሪክ በሁለት መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ከፍለን እናያለን። በግብጽ እና ከከነዓን ውጪ በሆነው ምድረበዳ።

የአምስቱ የሙሴ መጽሐፍት ታሪክ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ እስራኤላዊያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ወደ ከነዓን አልገቡም ነበር።

በዚህ ኮርስ የግለሰቦችን ስኬት እና ውድቀት እናጠናለን። ለምሳሌ ሄኖክና ኖህ ከቅድመ አባቶች እና የሽግግር ዘመን፣ አባቶች ከአብርሃም እስከ የሴፍ እንዲሁም ሙሴ፣ በሙሴ የመሪነት ብቃት የምንበረታታበት እና በእርሱም የተስፋይቱን ምድር አለመውረስ የምናዝንበትን ታሪክ በኮርሱ መጨረሻ እናያለን። በአጠቃለይ በሰዎቹ ውድቀት የእግዚአብሔርን ምህረትና ጸጋ በማየት በመደነቅ እንሞላለን። በተጨማሪም አምስቱ የህግ መጽሐፍት የእግዚአብሔርን ጸጋና ምህረት በእያዳንዳችን ህይወት እየተለማመድንና ለሌሎችም እያወጅን የምንኖርበትን መንፈሳዊ ጉልበት የምናዳብርበትን እውቀት የምንገበይበት ይሆናል።

## የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ዝርዝር በቤተክርስቲያን አከፋፈል

**አምስቱ የህግ መጽ ሐፍት** (The Pentateuch (Five volumes)
ዘፍጥረት፣ ዘጸዓት፣ ዘሌዋዊያን፣ ዘኑልቁ እና ዘዳግም
**የታሪክ መጽሐፍት** (Historical Books)
ኢያሱ መሳፍንት፣ ሩት፣ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል፣ 1ኛ እና 2ኛ ነገስት፣ 1ኛ እና 2ኛ ዜና፤፣ እዝራ፣ ነህምያ እና አስቴር
**የቅኔ መጽሐፍት** (Poetic Books)
ኢዮብ፣ መዝሙር፣ ምሳሌ፣ መክብብ፣ መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን እና ሰቆቃወ ኤርምያስ
**የትንቢት መጽሐፍት** **(Prophetic Books)**
***ሀ. አበይት ነቢያት*** ***(Major Prophets)***
ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ህዝቅኤል፣ እና ዳንኤል
**ለ. ደቂቀ ነቢያት** **(Minor Prophets)**
ሆሴዕ፣ ኢዮኤል፣ አሞጽ፣ ኢዮቤድ፣ ዮናስ፣ ሚኪያስ፣ ናሆም፣ እንባቆም፣ ሰፎንያስ፣ ሐጌ፣ ዘካሪያስ እና ምልኪያስ

## የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ በአይሁድ አከፋፈል

**የህግ መጽሐፍት (ቶራ) (the Law (Torah)**

ዘፍጥረት፣ ዘጸዓት፣ ዘጸዓት፣ ዘሁልቁ እና ዘዳግም

**ነቢያት (prophets)**

ቀደምት ነቢያት፡- ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ 1ኛና 2ኛ ሳሙኤል እና 1ኛ እና 2ኛ ነገስት

ኋለኞቹ ነቢያት፡- ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ህዝቅኤል፣ የ12 ነብያት መጽሐፍ

**ጽሑፎች (The Writings)**

አምስቱ ጥቅሎች ፡- መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን፣ ሩት፣ ሰቆቃወ ኤርምያስ፣ መክብብ እና አስቴር

የጥበብ መጽሐፍት፡- ምሳሌ፣ ኢዮብ፣ መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን፣ መክብብ

የቅኔ መጽሐፍት፡- መዝሙር. ምሳሌ እና ኢዮብ

**ሌሎች (Other)**
1ኛ እና 2ኛ ዜና፣ እዝራ (ነህሚያ) እና ዳንኤል

## የትምህርቱ አላማ

የዚህ ትምህርት ዓላማ ተማሪው በጥንቱ ዘመን ከነበሩት መጽሐፍት መካከል የፔንታቱክን (የአምስቱን የሙሴ የህግ መጽሐፈት) አስተምህሮና ጠቀሜታ በመረዳት ለአሁን ጊዜ የሚሆነውን መልዕክት እንዲረዳ ማስቻል ነው፡፡ ስለዚህም ወደዚህ ግብ ለመድረስ በሚያደርገው ጥናት፡-

1. ፍጥረት የእግዚአብሔር ተዓምራዊ የመፍጠር ችሎታ ውጤት መሆኑን ይገነዘባል
2. የሰው ውድቀት ምክንያትና የእግዚአብሔርን የመቤዠት ተስፋ ይገነዘባል
3. በዘፍጥረት መጽሐፍ የተገለጠውን ሐጢአትና የሐጢአት እድገት እንዲሁም የእግዚአብሔርን የቅጣት መንገድ (ሁኔታ) ይገነዘባል
4. ዕብራዊያን ከግብጽ ባርነት በእግዚአብሔር የጸናች ክንድ እንዴት እንደወጡ በመገንዘብ ማብራራት ይችላሉ፡፡
5. የማደሪያው ድንኳን ጠቀሜታና የእግዚአብሔር ከሰው መካከል የመኖር ምክንያት ይረዳል
6. የካህናት ጥሪና ለአገልግሎት የመለይት ሥርዓት ከአዲስ ኪዳን ጥሪና አገልግሎት ጋር በማዛመድ መረዳትን ያገኛል ማብራራትም ይችላል፡፡
7. የእስራኤላዊያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ያለመድረስና በምድረበዳ የመቅረት ምክንያትና የእግዚአብሔርን ባህሪ ይረዳል ያብራራል
8. በመጨረሻም የእስራኤልን ታሪካዊ አመጣጥ ወይም እድገት እንዲሁም የአምልኮ ይረዳል
9. የሙሴ ህግ (ፔንታቱክ) ለምን የእስራኤል ታሪክና ሐይማኖት መካከለኛ እንደሆነ ይረዳል

# ምዕራፍ አንድ

## ትምህርት አንድ

## የብሉይ ኪዳን ታሪካዊ ዳራ

### የጥንታዊ የሜሶፓታሚያ ታሪክ

ስለ ጥንታዊው ዓለም እና ስለ መጀመሪያው ስልጣኔ ለማወቅ የታሪክ ተመራማሪዎች ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ዓበይት ተግባራት በስርዓት እና በቅደም ተከተል ዘግበውታል፡፡ እነዚህ ምሁራን በዚህ ሥራቸው የሚከተሉትን ዋና ዋና የመረጃ ምንጮች በመጠቀም ነበር ስራቸውን ያከናወኑት፡፡

1. የታሪክ ማንነት
2. መረጃ መሰብሰብ
    - ቅርስ ስብስብና ምርምር
    - ቃለ መጠይቅ በማድረግ
    - የተለያዩ ጽሑፎችን በማሰባሰብ
3. መረጃዎችን መተርጎም
    - የክንውንኖችን ሁኔታ በማጥናት ትርጓሜ በመስጠት
    - የነገሮችን ትርጉም በመፈለግ፡ ለምሳሌ ይህ ምን ማለት ነው?
    - የተገለጠው ታሪካዊ ክስተት ዓላማው ምንድነው?
    - የመጀመሪያዎቹ ተደራሲያን ነገሩን እንዴት ተመልክተውታል? የሚለውን የዘመኑ ሰዎች ለክንውኑ የሰጡትን ትርጉም ወይም ምላሽ በመፈለግ የራሳቸውን ድምዳሜ ይሰጣሉ፡፡

ይሁንና የታሪክ ሰዎች ወይም የታሪክ ተመራማሪዎች ሊታዩ የሚገባው በተከሰተው ክስተት ወይም ታሪክ ላይ የራሳቸውን ጥናት በማደረግ እውነታ አፈላላጊዎች እንጂ ራሳቸው ታሪክ ሰሪ

ሳይሆኑ ወይም የታሪኩ አካል እንዳልሆኑ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ስናይ የሚሶፓታሚያ ዘመን ታሪክም በዚህ መልኩ በተደረገ ጥናት የተፈገኘ መረጃ ነው፡፡

### የህግ መጽሐፍት ጸሐፊ (The Authorship of the Pentateuch)

በህግ መጽሐፈት ላይ የሰፈሩትን መረጃዎች በጥንቃቄ ካየናቸው እንዲሁም ውስጣዊና ውጫዊ መረጃዎችን በአግባቡ ማጤን ከቻልንና ዋጋ ከሰጠናቸው ከታሪካዊ እውነታዎችም ጋር በማዳመር የህግ መጽሐፍት ጸሐፊነትን ለሙሴ በመስጠት አንድ ጠንካራ መከራከሪያ መቅረጽ እንችላለን፡፡

ስለ ሙሴ ጸሐፊነት የመጽሐፍት ምስክርነት፡-

**1. የህግ መጽሐፍት ራሳቸው ሙሴ ስለመጻፉ ወይንም ስለማቀናበሩ ይመሰክራሉ።** እግዚአብሔርም ሙሴን፦ የአማሌቅን ዝክር ከሰማይ በታች ጨርሼ እደመስሳለሁና ይህን ለመታሰቢያ በመጽሐፍ ጻፈው፥ በኢያሱም ጆሮ ተናገር አለው። (ዘጸ 17፡14) እንዲሁም "ሙሴም የእግዚአብሔርን ቃሎች ጻፈ ማለዳም ተነሣ፥ ከተራራውም በታች መሠዊያን፥ አሥራ ሁለትም ሐውልቶች ለአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ሠራ።" የሚል ቃል (በዘጸ 24፡4) እናነባለን። በቁጥር 7 ላይ "የቃል ኪዳኑንም መጽሐፍ ወስዶ ለሕዝቡ አነበበላቸው እርሱም፦ እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን እንታዘዛለንም አሉ።"

ዘጸዓት 34፡27፣ ዘህልቁ 33፡1-2 "የእስራኤልም ልጆች ጕዞ ከሙሴና ከአሮን እጅ በታች በጭፍሮቻቸው ከግብፅ በወጡ ጊዜ እንዲህ ነበረ። ሙሴም በእግዚአብሔር ትእዛዝ እንደ ጕዞአቸው አወጣጣቸውን ጻፈ እንደ አወጣጣቸውም ጕዞአቸው እንዲህ ነበረ።" ዘዳ 31፡9፣11 ላይ ደግሞ "ሙሴም ይህችን ሕግ ጻፈ፥ የእግዚአብሔርንም የቃል ኪዳኑን ታቦት ይሸከሙ ለነበሩት ለሌዊ ልጆች ለካህናቱ ለእስራኤልም ሽማግሌዎች ሁሉ ሰጣት። «… ይህን ሕግ በእስራኤል ሁሉ ፊት በጆሮው አንብበው።» ከእነዚህ ማጣቀሻዎች እንደምንረዳው ቢያንስ ለእነዚህ መጽሐፍት እንኳን ቢሆን ሙሴ ጸሐፊ መሆኑን የሙሴን የህግ መጽሐፍት ጸሐፊነት የሚደግፉ ምሁራን ይስማማሉ።

**2. በሌሎች የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት የምናገኘው መረጃ**

በዕብራዊያን እና በአማሌቅ መካከል የተደረገው ጦርነት በሙሴ መዘገቡ (መጻፉ) (ዘጸ 17፡14)

ኢያሱ 1፡8 "የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም።" ቁጥር 7 "… ባሪያዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ፥ አድርገውም በምትሄድበትም ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል።" በኢያሱ 8፡31 እንዲሁ "የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ የእስራኤልን ልጆች እንዳዘዘ፥ በሙሴም ሕግ መጽሐፍ እንደ ተጻፈው" እናነባለን። ኢያሱ የሙሴን ህጎች እንደገና ጻፋቸው የሚል በቁ 32 እናነባለን።

1ኛ ነገስት 2፡3 ንጉስ ዳዊት እንዲህ ይላል "በሙሴ ሕግ እንደ ተጻፈ ሥርዓቱንና ትእዛዛቱን ፍርዱንና ምስክሩንም ትጠብቅ ዘንድ፥ በመንገዱም ትሄድ ዘንድ፥ የአምላክህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቅ።" 2ኛ ነገ 14፡6 "በሙሴ ሕግ መጽሐፍም እንደ ተጻፈ፥ እግዚአብሔርም፦ ሁሉ በኃጢአቱ ይሙት እንጂ አባቶች በልጆች አይሙቱ፥ ልጆችም በአባቶች አይሙቱ ብሎ እንዳዘዘ የነፍሰ ገዳዮቹን ልጆች አልገደለም።" ይህ ከዘዳግም 24፡16 የተወሰደ ሃሳብ ሲሆን የተጠቀሰውም በ796 ዓ.ዓ አካባቢ ነው። 2ኛ ነገ 21፡8 ያዘዝኋቸውንም ሁሉ፥ ባሪያዬም ሙሴ ያዘዛቸውን ሕግ ሁሉ ቢያደርጉ ቢጠብቁም ለአባቶቻቸው ከሰጠኋት ምድር የእስራኤልን እግር እንደ ገና አላቅበዘበዝም ባለው ቤት የሠራውን የማምለኪያ ዐፀድን የተቀረጸውን ምስል አቆመ።

ይህም ታሪክ ምናሴ በነገሰ ጊዜ ማለትም ከ696-642 ዓ.ዓ አካባቢ የተከናወነ ነው።[1]

---

[1] በዚህ ክፍለ የተሰጡት ማጣቀሻዎችና የዘመን ቁጥሮች ከብሉይ ኪዳን መግቢያ ዳሰሳ በግሊሰን ኤል. አርቸር በ1994 በዩ ኤስ ኤ ከታተመው መጽሀፍ ነው

ተጨማሪ ማጣቀሻዎች (እዝራ 6፡18፣ ነህ 13፡1፣ ዳን 9፡11-13 ሚል 4፡4)

3. **በአምስቱ የሙሴ መጽሐፍት ከሙሴ ጸሐፊነት በቀር ሌላ ሰው ስለመጻፉ ምንም አይነት ፈንጭ አለመገኘቱ**

ከላይ እንዳየነው የህግ መጽሐፈት የሙሴን ጸሐፊነት ይናገራሉ ምንም እንኳን ሙሴ ከሞተ በኂላ ያለው ታሪክ ከሙሴ ውጭ በሌላ ሰው የተጻፈ ቢሆንም፡፡

4. **አዲስ ኪዳን ስለ ሙሴ ጸሐፊነት አበክሮ ይናገራል**

የህግን መጽሐፈትና ሙሴን ከሚያገኛኛቸው ማጣቀሻዎች ባሻገር በቀጥታ ከሙሴ ከራሱ ጋር የሚገናኙትን ክፍሎች መርጠን እንይ፡፡ ማቴዎስ 19፡8 "እርሱም፦ ሙሴስ ስለ ልባችሁ ጥንካሬ ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ፤ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም።" በዮሐንስ 5፡46-47 ደግሞ "ሙሴንስ ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር፤ እርሱ ስለ እኔ ጽፎአልና።" እንዲሁም በዮሐ 7፡19 ላይ ክርስቶስ እንዲህ ይላል "ሙሴ ሕግን አልሰጣችሁምን? ከእናንተ ግን ሕግን የሚያደርግ አንድ ስንኳ የለም። ልትገድሉኝ ስለ ምን ትፈልጋላችሁ?" ሐዋሪያው ጴጥሮስ ደግሞ የዘዳግም 18፡15 ሐሳብ በመውሰድ ሙሴ የተናገረውን የጠቅሳል፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስም እንዲሁ በሮሜ 10፡5 ላይ ዘሌዋዊያን 18፡5ን በመጥቀስ እንዲህ ይላል "ሙሴ ከሕግ የሆነውን ጽድቅ የሚያደርገው ሰው በእርሱ በሕይወት እንዲኖር ጽፎአልና።"

የወንጌል ጸሐፊው ማርቆስ በ12፡26 ላይ "ስለ ሙታን ግን እንዲነሡ እግዚአብሔር፦ እኔ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ እንዳለው በሙሴ መጽሐፍ በቍጥቋጦው ዘንድ የተጻፈውን አላነበባችሁምን?" በማለት የዘጸዓት 3፡6ን ታሪክ በመውሰድ የህግ መጽሐፍትን ጸሐፊነት ከሙሴ ጋር ያገናኘዋል፡፡ ስለዚህ ከእነዚህ መረጃዎች በመነሳት የህግ መጽሐፍት ጸሐፊ ሙሴ ነው ማለት እንችላለን በማለት ግሊሰን አርቸር ይሞግታሉ፡፡ በመሆኑም ክርስቶስና ሐዋሪያቱ ተሳስተዋል ወይም ዋሽተዋል ካላልን በቀር ይላሉ ግሊሰን በምንም ሁኔታ የሙሴን ጸሐፊነት መካድ አንችልም ወይንም ሙሴ ጸሐፊ አይደለም የሚለውን መቀበል አንችልም ይላሉ፡፡

**አምስቱ የህግ መጽሐፍት ቅርጽ እና ይዘት**

ምንም እንኳን ስለ አምስቱ የህግ መጽሐፍት ቀርጽና ይዘት አስቀድመን ማየት የሚገባን ቢሆንም ስለ ዘፍጥረት ቅርጽና ይዘት ለመነጋገር እንደመነሻ ለማድረግ አሁን ማየት አስፈልጎናል፡፡

ብዙውን ጊዜ ሲነገር እንደሚሰማው በኦሪት ዘፍጥረት እስከ ዘዳግም ድረስ 5 መጽሐፍት በአንድ አንን ተካትተው አምስቱ የህግ መጽሐፍት ("Pentateuch") በመባል የሚታወቁ ሲሆን አሁን አሁን አንዳንድ የስነ መለኮት ምሁራን ደግሞ የኢያሱን መጽሐፍ በመጨመር የህግ መጽሐፍት ቁጥር ስድስት መሆን አለበት በማለት ሙግት ገጥመዋል፡፡ እንደ ምክንያት የሚያነሱትም የእስራኤላዊያን የተስፋይቱን ምድር (ከነዓንን) መውረስ በዘዳግም መጽሐፍ አለመጠቃለሉንና የኢያሱ ሙሉው መጽሐፍ የሚተርከው ስለ ዕብራዊያን የተስፋይቱን ምድር መውረስ ነውና ነው፡፡ በዚህም ምክንያት እነዚህ ምሁራን የህግ መጽሐፍትን ፔንታቱክ በመባል ፈንታ "ሄክሳቱክ" "hexateuch" መባል አለበት ብለው ይከራከራሉ፡፡

ይሁንና በዚህ ትምህርት የህግ መጽፍት ብለን የምናጠናው ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ዘዳግም ያሉትን አምስት የህግ መጽሐፍት ማለትም ዘዳግም፣ ዘጸዓት፣ ዘሁልቁ እና ዘዳግም ይሉትን መጽሐፍት ነው፡፡ የዘፍጥረት መጽሐፍ ቅድመ - ሙሴ ታሪኮችን "Pre-Mosaic History" የሚያካትት ሲሆን ቀሪዎቹ አራቱ የኦሪት መጽሐፍት የሙሴን የጥሪ አገልግሎትና ዕብራዊያንን ከግብጽ እስከ ተስፋይቱ ምድር ጫፍ ያለውን ታሪክ በስፋት የሚያብራረሩ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ዘፍጥረት፡ የቅድመ አባቶችና የአባቶች ዘመን

ትምህርት አንድ፡- ፍጥረት፣ ውድቀት እና መዋጀት

ትምህርት ሁለት፡- የጥፋት ውሀ

ትምህርት ሶስት፡- የአብርሃም ታሪክ

ትምህርት አራት፡- የይስሐቅና የያዕቆብና ታሪክ

ትምህርት አምሰት፡- የዮሴፍ ታሪክ

## ትምህርት ሁለት

### 1.1. ፍጥረት፣ ውድቀት እና መዋጀት

በዚህ ትምህርት የሚከተሉትን ዋና ዋና ሀሳቦች እንዳስሳለን

- የዘፍጥረትን እና የፔንታትዩክን አወቃቀርና ጭብጥ ሐሳብ
- የፍጥረት ሁኔታ
  - የእግዚአብሔር ፍጥረት
  - ጊዜ በፍጥረት ሂደት
  - ምድርን ማዕከል ይደረገ የጊዜ ሁኔታ
  - የሰው በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠር
- ውድቀትና የመዋጀት ተስፋ
  - የመጀመሪያው ሰው
  - ሐጢአትና ጸጋ
  - የሐጢአት ውጤት

**የትምህርቱ ዓላማ፡**

ይህ ትምህርት ሲጠናቀቅ ተማሪው የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያገኛል

1. በዘፍጥረት 1፡1 በፍጥረት (በአፈጣጣር) ጉዳይ ላይ የሚነሱትን የተሳሳቱ አስተምህሮዎች መቋቋምና በአፈጣጠር ላይ የተሰጡትን የተለያዩ የጊዜ ቀመሮች ይገነዘባል መግለጽም ይችላል፡፡
2. መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የፍጥረት ሂደት በማጤን የመቤዠትን ተስፋ ጠቀሜታ ይረዳል
3. ተማሪው የራሱን የመዳን (የመቤዠት) ስራ እየተመለከተ በአድናቆት የጠፉትን ለማዳን የእውነትን ወንጌል ለመስበክ ይበልጥ ይነሳሳል

### 1.1.1 የዘፍትረት አጠቃላይ መግቢያ

ይህ የዘፍጥረት መጽሐፍ መጀመሪያው የተጻፈው በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲሆን "Bereshith" ትርጉሙም "በመጀመሪያ" "in the beginning" የሚል ነው። "Genesis" የሚለው ስያሜ የተሰጠውም በ300 ዓ/ዓ 72 በሚሆኑ የአይሁድ ሊቃውንት በሰባ ቀናት ውስጥ የብሉይ ኪዳንን መጽሐፈት ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ቋንቋ ሲተረጉሙት የሰጡት ነው። ትርጉሙም የመጀመሪያ "origin" ምንጭ "source" ወይም ትውልድ "generation" ማለት ነው። ይህም የዕብራይስጥ ትርጉም "ሰፕቱጀንት" "subtuagint" በመባል ይታወቃል።

የዘፍጥረት መጽሐፍ "መጀመሪያ" የሚል ስያሜ ያገኘበት ምክንያት

- የፍጥረትን ጅማሬ ጠቅልሎ ስለያዘ
- የሰዎች የመጀመሪያው ህብረት ስለተገለጠበት
- የሐጢአትና የፍርድ እንዲሁም የተስፋ ጅማሬ ስለሰፈረበት
- የእምነትና በእምነት የሚገኝ ጽድቅ ጅማሬ

## 1.1.2 ጥንታዊ ዘመን (Primeval Period)

ይህ በእንግሊዝኛው (primeval period or History) በመባል የሚታወቅ ሲሆን ስለ ፍጥረት አፈጣጠር ስለ ሰው ውድቀት እና ስለ እግዚአብሔር የመቤዡት ዓላማ የሚያወራ የታሪክ አንድ ክፍል ነው። ጸሐፊው እጅግ ስልታዊ በሆነ ሁኔታን ቅንብር የክስተቶችን ቅደም ተከተል ጠብቆ ጽፎታል። በዚህም እግዚአብሔር በትውልድ መከካል እንዴት ስራውን ሲሰራ እንደነበር መረዳት ይቻላል። የትውልድ ሐረጎችን እንደሃሳቡ መግቢያ በማድረግ ከአንድ ክፍል ወደ ሌላኛው የተሸጋገረበትን ሁኔታ ስናጤን የጸሐፊውን ብስለት እንረዳለን። ለምሳሌ የሰማይና የምድር ጅማሬ ታሪክ፣ የትውልድ ሐረግ እና የመሳሰሉት ማየት ይቻላል። በተጨማሪም ይህ የመጽሀፍ ክፍል የዚህ ዘመን የመጽሐፉ አንባቢዎች ራሳችንን እንድናይ ማለትም የእኛንም መፈተን፣ትዕቢት፣ እና ውድቀት እንድናይ ያደርገናል። በዚህ አይነት ውስብስብና እጅግ ክፋት በበዛበት ዓለም እግዚአብሔር የሚገልጠውን ጸጋና ምህረት እያየን እንድንደነቅም ያደርገናል። በተጨማሪም ያለንበትን ዓለም መንፈሳዊና ማህበራዊ ሁኔታ እንድናስተውልና እንዴት ደግሞ ከዚህ ዓለም ርኩሰት ራሳችንን ጠብቀን መኖር እንደምንችል ያስተምረናል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲጸልይ "ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም" ብሏል (ዮሐ 17፡15)።

ይህ ክፍል ፍጥረትን በሚመለከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ሃሳቦች በመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎች በመመዘን የምንዳኝበትና እውነታውን የምናሳይበት ክፍል ነው።

### 1.1.3. የዘፍጥረት ቅርጽና ይዘት

የዘፍጥረት መጽሐፍ ከሌሎቹ የፔንታቱክ መጽሐፍት ሰፊ እና ብዙ ምዕራፎች አሉት። በዚህ መጽሐፍ የእግዚአብሔር መገለጥ፣ የመፍጠር ችሎታ፣ ከመታወቅ በላይ የሆነው ሀይሉ እና ጥበቡን እንዲሁም ባህሪውን የሚነግረን ሲሆን መጽሐፉ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

1. **ጥንታዊ ዘመን (Primeval History or Age) ዘፍ 1-11**

ሀ. የዘፍትረት 1-11 ከዘመናዊው የምዕራባዊያን ሳይንስ ጋር እንዴት ይዛመዳል?

- አጠቃላይ ተቃርኖ
- ጠቅላላ ስምምነት
- የስምምነት ነጥቦች

ሳይንስ የምርምር ዘዴ ነው፡፡ እርሱም ዘመናዊ ክስተት ሲሆን ነገር ግን ሁል ጊዜ በአዲስ ነገር ሲገኝ ይለወጣል፡፡ እግዚአብሔር እንደፈጣሪነቱና አዳኝነቱ «በሁለቱም መጽሐፍት» በአንድ ላይ ተያይዟል ተፈጥሮ (የተፈጥሮ ራዕይ መዝ 19፡1-6፣ እና ልዩ መገለጥ 19፡7-11)፡፡ እግዚአብሔር ሁለቱን ጽፏል አለመስማማት የለባቸውም፡፡

ለ. ዘፍጥረት 1-11 ከዘመናዊው ታሪክ አንጻር እንዴት ይታያል?

1. የምስራቅና የምዕራብ የስነጽሑፍ ዘውጎች የተለያዩ ናቸው፡፡ ይህ ሲባል ግን እውነት ወይም ውሸት በሚል አይደልም፣ ትክክልና ትክክል ያይደለ በሚልም አይደለም ነገርግን የተለያዩ ናቸው፡፡ ዘፍጥረት 1-11 ቅድመ ታሪክ ነው፡፡ ከስነመለኮት አኳያ ጠቃሚና ዋነኛ ነው፡፡ ነገር ግን በአጫጭር ጽሑፎች የተሸፈነ ነው፡፡ በታሪካዊ ተውኔት የተሸፈነ ነው፡፡ በዘመን መጨረሻ ራዕይ የተሸፈነ ነው፡፡
2. ክርስትና እንደ ይሁዲነት በታሪክ ላይ የተመሰረተ እምነት ነው፡፡ የሚቆመውም ሆነ የሚወድቀው በራሱ በታሪክ እውነታዎች ላይ ነው፡፡ ለምሳሌ ከዘፍጥረት 1-11 ባለው ክፍል ከእኛ መረዳት በላይ የሆኑ ሁነታዎች አሉ፡፡ ምንም እንኳ በተብራራ መልኩ ሳይሆን በተከማቸ መልኩ (Exhaustively) ቢቀርቡም አቀራረባቸው ግን እኛ ልንረዳው በምንችልበት ሁኔታ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ከመጀመሪያው ስናጠና ትኩረት የሚያደርገው በመዋጀት ስራ ላይ አንጂ በፍጥረት ሂደት ጉዳይ ላይ አይደለም፡፡ ይህም የሆነው ከስነመለኮት ጠቀሜታ አኳያ ነው፡፡
3. ዘፍጥረት 1-11 ከስነ-ጽሑፍ ጋር ያለው ተዛምዶ
   - በሜሶፖቶሚያ ምንጮች ከምዕ 1-2፣ 3 እና 6-9 ትይዩዎች አሉ፡፡ በቃላት፣ በዝርዝር እና ከታሪክ አኳያ አካሔዳቸው ተመሳሳይ ነው፡፡ ሆኑም የመጽሐፍ ቅዱስ ውህደት ወይም አንድነት እና የሰው ልጆች ክብር የተለዩ ናቸው፡፡
4. መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ሥነ-ጽሑፍ መውሰድ ቢያንስ ለሁለት አደጋዎች ያጋልጣል

ሀ. እንደ ሥነ-ጽሑፍ ታሪካዊነት በአጠቃላይም ታሪካዊነት የሌለው መጽሐፍ ያደርገዋል

ለ. እንደ ሥነ - ጽሑፍ በጥሬው የተጻፈና በዘይቤያዊ ቋንቋ ያልሆነ፣ የምስራቃዊ ዘውጎች የሌሉት፣ ተውኔታዊ ያልሆነ ግነታዊ እውነታዎች ሁነው ይቀራሉ፡፡

እግዚአብሔር ራሱን የገለጠው ለተወሰነ ጊዜና ባህል ሲሆን የሰዎችን ቋንቋ በመጠቀም ነው፡፡ ይህም እውነትና የታመነ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተጠቃለለ አይደለም፡፡

5. ፍጥረት እየጨመረ የሚሔድ ሐቅ ራዕይ ነው፡፡ ዘፍ1-2 መሰረታዊ ናቸው እንዲሁም መዝሙራትና አዲስ ኪዳን ለትክክለኛ አስረሳሰብ ወሳኝ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ለፍጥረት ዘዴና ዓላማ ስነመኮታዊ መረዳት ይጨምራሉ፡፡
6. ዘፍጥረት 1-11 እንዴት እንተርጉም

ሀ. ሁሉም እንዴት ተጀመረ እንዴትስ ያበቃል

ለ. ለእግዚአብሔር ምላሽ ለመስጠትና መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት የሚረዱን ሐቆች እንዳሉን መረዳት

ሐ. በዘፍ 1-11 መመልከት ያለብን

- ከጽሑፍ አንጻር
- ከታሪክ እንጻር
- ከስነመለኮት አንጻር
- በዘፍጥረት በተገለጠው የእግዚአብሔር አውነት መሰረት ሁሉም ሰው በታሪክ ወደ አላም በገባው ሐጢአት ምክንያት በፍርድ ወንበር ፊት እንደሚቆም ከግንዛቤ በማስገባት እንዲሁም የእግዚአብሔርን ጽድቅና የሰውን አመጻኛነት መሰረት ባደረገ መልኩ በፍጥረት ላይ ሰፊ ጊዜና አላስፈላጊ ትንታኔ ከመስጠት ይልቅ ወደ ዘላለማዊው የመቤዠት ተስፋ በማተኮር መተርጎም ይቻላል፡፡

✓ ፍጥረት (ዘፍ 1-2)
✓ ከውድቀት እስከ ውሀ ጥፋት (ዘፍ፡ 3-8)
✓ ከጥፋ ውሃ እስከ ሃገሮች መመስረት (ዘፍ፡ 9-11)

7. የአባቶች ዘመን (Patriarchal History or Age) (ዘፍ፡ 12-50)

✓ አብርሃም (ዘፍ፡ 12-25)
✓ ይስሐቅና ያዕቆብ (ዘፍ፡ 26 -36)
✓ ዮሴፍ (ዘፍ፡ 37-50)

# ትምህርት ሦስት

## እግዚአብሔር እና ፍጥረት (ዘፍ 1፡1 መዝ 90፡1-2፣ 14፡1)

የዘፍጥረት መጽሐፍ የፍጥረትን ታሪክ ሲዘረዝር የእግዚአብሔርን ከፍጥረት በፊት መኖር በሚያረጋግጥ ሁኔታ ይጀምራል፡፡ በየትኛው ጊዜና ቀን አለማት እንደተፈጠሩ ባይናገርም እግዚአብሔር ግን ፈጥሮታል፡፡ ይህም በህልወተ እግዚአብሔርና በፈጣሪነቱ የሚያምኑ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ከዘፍ 1፡1 ጀምሮ ስለ እግዚአብሔር እና ስለፍጥረት ግንኙነት የሚናገረውን ይህንን ክፍል ለእግዚአብሔር ህልውና እንደመነሻ እና የእምነታቸው መሰረት አድርገው ይወስዱታል፡፡

በተቃራኒው ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ እምነት የሌላቸው የፍልስፍና ዘርፎች በእግዚአብሔር ህልውና ላይ የተለየ አመለካከት ያነሳሉ፡፡

በስፋት ከሚታወቁት ፍልስፍናዎችና አመለካከቶች መካከል ዋና ዋና የሚባሉትን የአራቱን አቋም ወይም አመለካከት በሚከተለው ሰንጠረዥ እንመለከታለን፡፡

| ተ.ቁ | የፍልስፍና ስም | አስተምህሯቸው | ክርስቲያናዊ የመከራከሪያ ሐሳብ |
|---|---|---|---|
| 1 | ኤትይዝም | እግዚአብሔር ወይም ፈጣሪ የለም | ፍጥረት ያለ ፈጣሪ ካለመኖር ወደ መኖር ሊመጣ ካለመቻሉም በላይ የፍጥረት ስርዓት በሉዓላዊ አምላክ እየተዘጋጀ ነባራዊ ዓለም ይነግረናል |
| 2 | አግኖስቲሲዝም | እግዚአብሔር መኖሩንም ሆነ አለመኖሩን ሰው እርግጠኛ ሊሆን አይችልም፡፡ | እግዚአብሔር ሁሉን እንደፈጠረ የሚያምኑ (በእምነት የተቀበሉ) ሁሉ የእግዚአሔርን ህልውና በሰራው ስራ አረጋግጠዋል፡፡ |
| 3 | ፓንቴይዝም | የምናየው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ነው፡፡ | በዘፍ 1፡1 "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ" የሚለው ዓረፍተ ነገር በእምነት ለተቀበሉ ሁሉ፣ እግዚአብሔር ከፍጥረት ህልውና በፊት በራሱ የሚኖር አምላክ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ |
| 4 | ፖሊቴይዝም | ብዙሀ አማልክት አሉ | ኤሎሂም የሚለው የእግዚአብሔር መጠሪያ በእብራይስጥ ብዙ አማልክትን "The Plurality of God" ሳይሆን በእብራይስጥ ከአንድ በላይ የሆነ መገላጫ ያለው የእግዚአብሔር "the Plural Hebrew from of God " በዘፍ 1፡1 መገለጹ ነው፡፡ |

ሰንጠረዥ 1

## ሀ/ ፍጥረትና ጊዜ በዘፍጥረት አንድ

በዘፍጥረት 1 እና 2 የምናነበውን የጊዜ ሁኔታ በግልጽ ለመረዳት አስቸጋሪ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ስለዚህ ርዕሰ በሰፊው ለመነጋገር የሚቻለው በፔንታቱክ ኮርስ ሳይሆን በብሉይ ኪዳን ስነ መለኮት ወይም የዘፍጥረትን መጽሐፍ እንደ አንድ ብቸኛ ኮርስ በምንማርበት ጊዜ ነው፡፡

ይሁን እንጂ የነገረ መለኮት ምሁራን በዘፍጥረት 1 እና 2 ያለውን የጊዜ ሁኔታ የሚረዱበትን እና የሚተረጉሙበትን መንገድ በጥቂቱ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

| ተ.ቁ | ስያሜው | መግለጫ |
|---|---|---|
| 1 | እያንዳንዳቸው 24 ሰዓታትን የሚያካትቱ 6 ቀናት | እያንዳንዳቸወቅ 24 ሰዓታትን በሚያካትቱ 6 ተከታታይ ቀናት መላው ዓለም የፈጠረ ሲሆን ዘፍ 1፡1 በፊትም ሆነ በኋላ ምንም አይነት የጊዜ ክፍተት (there was no gap or interval of time or period) የለም። |
| 2 | በክንውኖች መካከል ራሱን የቻለ ክፍተት አለ (interval theory) | እያዳንዳቸው 24 ሰዓታት ያላቸው 6 ቀናት ሲሆኑ በቀኖች መካከል ግን በውል የማናውቀው ክፍተት አለ። |
| 3 | ማንም የማያውቀው የጊዜ ክፍተት አለ (gap theory) | በዘፍ 1 የተገለጸው የመጀመሪያው ፍጥረት ከጠፋ በኂላ እግዚአብሔር አሁን ያለውን ፍጥረት እንደገና ፈጥሯል። ስለዚህ ከዘፍ 1፡3-31 ያለው አዲስ ፍጥረት በመሆኑ በቁ 1 እና 2 መካከል የዘመን ክፍተት አለ ይላሉ። ማረጋገጫቸውም የቅሪተ አካላት (fossils) እድሜ ነው። |
| 4 | አንድ ቀን እንደ አንድ ዘመን (day age theory) | እያንዳንዱ ቀን ዘመንን ይወክላል። ስለዚህ ፍጥረት የተፈጠረው በስድስት ዘመናት ነው ይላሉ። |
| 5 | የቀናት ትረካ ሁኔታ (day of narration) | ፍጥረት የተፈጠረበት ዘመን እጅግ ረዥም ዘመን ሆኖታል። 6ቱ ቀናት የሚያሳዩን እግዚአብሔር ለሙሴ ስለ ፍጥረት ሁኔታ የገለጸባቸው ቀናት ናቸው። |
| 6 | ቅኔያዊ አገላለጽ (poetic language) | በዘፍ 1 የምናየው ነገር ሁሉ (የቀኖች ጉዳይ) ቅኔያዊ ወይም ምሳሌያዊ አገላለጽ ናቸው። |

ሰንጠረዥ 2

ዘፍጥረት አንድ

በዘፍጥረት 1 እና 2 የምንመለከተው እግዚአብሔርን እና ፍጥረትን ማለትም እግዚአብሔር በፍጥረት አፈጣጠር ውስጥ ያሳየውን የመፍጠር ችሎታ እና ስልጣን እንዲሁም የፍጥረት ቅደም ተከተልን ነው። በዚህም የፍጥረት ሂደት ውስጥ የሰውን በልዩነት መፈጠርና አላማ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ህብረት ይናገራል። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነትና ህብረት የመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃለይ አስተምህሮ መሆኑን ከግንዛቤ ማስገባት መጽሐፍ ቅዱስን ለሚያጠኑ ሁሉ አስፈላጊ ነው።

1፡ 26-27 በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስለሰው ሁለንተና የተለየ ሁኔታ እንዳለው ማለትም ሰው የስጋ የመንፈስ እና የነፍስ ውህደት የሚገልጽ ቢሆንም በዚህ ክፍል የምናገኘው እውነት ግን ሰው በእግዚአብሔር መልክና አምሳል መፈጠሩን ነው፡፡

ስለ ሰው አፈጣጠር የሚከተሉትን ነጥቦች ማየት እንችላለን

ሀ. ሰው በእግዚአብሄር መልክና አምሳል ተፈጥሯል

1. መንፈስና ነፍስ አለው፡
    - ይህም መንፈሳዊ ህይወትና የመንፈሳዊነት ዝንባሌ እንዳለው ያመለክታል፡፡
    - ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት የሚያደርግ እና አብሮ የሚኖር መሆኑን ያስረዳል፡፡
2. ስብዕና ፡
    - ➢ ሰው እውቀት፣ ስሜትና ፈቃድ አለው
    - ➢ ሞራል

ለ. ሰው የእግዚአብሔር ወኪል ነው

- ➢ የዳበረ ንቃተ ህሊና አለው
- ➢ ጥያቄ መጠየቅና መልስ መስጠት ይችላል
- ➢ የመወሰንና የመፈጸም ችሎታ ተችሮታል

ሐ. እግዚአብሔር በፈጠረው ፍጥረት መካከል ሰው ማዕከላዊ ስፍራን ይዟል፡፡

- ➢ በምድር ላይ ለተፈጠረው ፍጥረት በሙሉ መጋቢ፣ ጠባቂና ተንከባካቢ ነው
- ➢ በአጠቃላይ ሰው የእግዚአብሔር ማንነት ነጸብራቅ ነው፡፡

**ዘፍጥረት 2፡**

ቁ 7 እግዚአብሔር ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፡፡ በአፍንጫውም የህይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፡፡ ይህ እስትንፋስ ነው ዘፍ 1:26 እግዚአብሔር መልክ እና አምሳል የተባለው፡፡ ይህም ስብዕና (personality) ጥራትን (quality) እና ህሊናን (consciousness) ያካትታል፡፡ በዚህም ምክንያት ሰው ከሌሎች ፍጥረታት የተለየ እና ክቡር ፍጥረት እንዲሆን አስችሎታል፡፡

**የጋብቻ ድንጋጌ**

የመጀመሪያውን የጋብቻ ድንጋጌ የምናገኝበትም በዚህ ምዕራፍ ነው፡፡ በዘፍጥረት ከምናገኛቸው አስደናቂ የሆኑ ትምህርቶች መካከል ስለ ጋብቻ የተነገረው ይገኝበታል፡፡ “ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ፡፡” (ዘፍ 2፡24) ይህንን የጋብቻ ድንጋጌ ኢየሱስ ክርስቶስም አይሁድ መፋታትን አስመልክቶ ለጠየቁት ጥያቄ ምላሽ ሲሰጥ እንደ ጋብቻ መሠረት ተጠቅሞበታል፡፡ ስለዚህ ጋብቻ አንዱ ለሌላኛው ሙሉ መሰጠትን የሚያሳይበት በሁለቱ መካከል ልዩነት ሳይኖር የህይወት ዘመን ትስስር እንዳለና በምንም ሁኔታ የጋብቻ መፍረስ ተቀባይነት እንደሌለው አስረጂ ነው፡፡ (ማቴ 19፡5)

**ዘፍጥረት 3**

### ለ/ ፈተና ፣ ውድቀት እና መቤዠት

በዘፍ 3፡1-7 የውድቀትን ታሪክ እናገኛለን፡፡ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ከተከሰቱት አደገኛና ከፍተኛ ጉዳት ካደረሱ ሁኔታዎች ውስጥ የዘፍጥረት 3 ውድቀት የመጀመሪያውና ለሌሎቹ ሁሉ መሪ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የውድቀት ውጤት ፍጥረትን ሁሉ አግኝቷልና ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰውን በታልቅ ባርኮት ቢባርከውም ሰው ግን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ በማመጽ ፈቃዱን ማድረግ አቅቶት ይታያል፡፡ በዚህም ምክንያት ሰው በኤደን ገነት የእግዚአብሔርን ድምጽ ሲሰማ ደስ እንደመሰኘት ፍርሃት እና ሽሽት ውጦታል፡፡

### የመጀመሪያው ፈተና

ጳውሎስ ቢ.ሆፍ የተባሉ የስነመለኮት ምሁር ከዘፍ 3፡1-5 ያለውን የፈተና ሂደት እንዲህ ያብራሩታል:-

- የእግዚአብሔር ቃል የነገሮች ምንጭና እውነተኛ ነው፡፡
- እግዚአብሔር በባህርዩ ታማኝ፣ መልካም እና ፍቅር ነው፡፡
- እንዲሁም እግዚአብሔር በእውነታ ላይ የተመሰረተ የፍትህ አምላክ ነው፡፡

በዚህ ክፍል የምናገኘው የሰይጣን ፈተና እነዚህን እውነቶች የሚያስረሳና በተቃራኒው መንገድ የሚያስኬድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

1. **ሔዋን ብቻዋን ሳለች ተፈተነች፡፡**

ሰይጣን አዳምና ሔዋን አብረው ሳሉ አልነበረም የፈተናቸው፡፡ ሰይጣን ምናልባት ይሔዋንን ብቸኝነት የተጠቀመው ከአዳም ይልቅ በፈተና ለመታለልና ለመውደቅ እርሷ ትቀልላለቸው ብሎ ይሆናል፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ሰዎች አብረው በመሆን እንዴት ፈተናን ሊቃቋሙ እንደሚችሉ ሊያመለክት የሚችል ማስረጃ ነው፡፡ የወንድሞች በህብረት መቀመጥ በብሉይ ኪዳን እንዲሁም የመሰባሰብ ጠቀሜታ በአዲስ ኪዳን በዕብራዊያን መልዕክት የተጻፈው አንድነትና ህብረት ባለበት እግዚአብሔር ከሚያፈስሰው በረከት በተጓዳኝ ጠላትንም ድል ማድረግ የሚያስችል መንፈሳዊ ጉልበት ስለሚያስገኝ ነው፡፡

2. **ለፈተና ሌሎችን መጠቀም**

ሰይጣን ወደ አዳምና ሔዋን ሲመጣ እራሱ በአካል ተገልጦ አልመጣም፡፡ እባብን በመጠቀም ሔዋንን አሳታት ሔዋንም አዳምን አሳተችው፡፡ ከዚህም የምንረዳው ፈተና ከምንወዳቸው እና ከምናምናቸው ሰዎች ሲመጣ ምን ያህል ከባድ መሆኑን ነው፡፡ ሰይጣን የብርሃን መልዓክ መስሎ እና ጭንብል ለብሶ ይመጣል፡፡ (1ቆሮ 11፡13-15)

3. **የእግዚአብሔርን ክልከላ ጥያቄ ውስጥ ማስገባት**

በዚህ ክፍል እንደምናየው ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል በመቃወም የማታለል አላማውን አላከናወነም፡፡ ይልቁኑ እግዚአብሔር ወይስ ሌላ? በሚል አይነት ጥያቄ ይፈጥርባታል፡፡ "ሴቲቱንም፦ በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት፡፡" (ዘፍ 3፡1) በማለት ይጠይቃታል፡፡ በሔዋን አዕምሮ ወይም ልብ እንዴት መልካሙ እግዚአብሔር እንዲህ

አይነት ክልከላ ያደርጋል የሚል ሀሳብ እንዲፈጠር አደረገ። እኚህ ጸሐፊ የሉተርን ሃሳብ ሲገልጹም፡ አንድ ሰው በእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል ላይ ጥርጥር ካደረበት ከዲያብሎስ ጋር የሚያደርገውን የፈተና ጦርነት ከወዲሁ ግማሹን ተሸንፏል ማለት ነው ብሏል ይላሉ።

4. **የእግዚአብሔርን መልካምነትና ፍቅር ከጥያቄ ውስጥ ማስገባት።**

የእባቡ (የሰይጣን) አላማ ከሔዋን አዕምሮ ስለ እግዚአብሔር መልካምነትና ፍቅር ጥያቄ መፍጠር እንደ ነበር ከጥያቄው እንረዳለን። "ሴቲቱንም፦ በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት።" ሰይጣን የሴቲቱን ልብ ከፈጣሪዋ ከእግዚአብሔር ከተሰጣት ብዙ በረከት ይልቅ ወደ ተከለከለችው የዛፍ ፍሬ እንድታይና እንድትጓጓ ያደረጋት ይህን ጥያቄ በማንሳት ነበር "ለመልካሙ እግዚአብሔር ከዛፎች ፍሬ እንዳትበሉ ብሎ መከልከል ይቻል ይሆንን? በእርግጥ እግዚአብሔር እናንተን እንዲህ የሚወስናችሁ ከሆነ ይወዳችኋል ማለት ይቻላልን?"።

በእግዚአብሔር ፍቅርና መልካምነት ላይ መጠራጠር በፈተና እና በእኛ መካከል ያለውን ገደብ መስበር ነው። ይህም ሰይጣን ሁል ጊዜ አማኞችን ከእግአዚብሔር ፍቅርና መልካምነት ለመለየት የሚጠቀምበት የማሳሳቻ መንገዱ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለሆነው ለእግዚአብሔር ህግ ወይም የህይወት መርህ መገዛት አስቸጋሪና የማንወጣው መሆኑን በተለያየ መንገድ በመግለጽ ተልዕኮውን ይፈጽማል። በዚህም ሔዋን እግዚአብሔር ያልተናገረውን "አትንኩትም" ብሎናል የሚለውን በመጨመር ሌላ አላስፈላጊ ማብራሪያ ውስጥ ስትገባ ትታያለችለች። (ዘፍ 3፡3)

5. **የሐጢአት አስከፊነት ወይም የሐጢአትን ውጤት መካድ:**

ስለ እግዚአብሔር መልካምነት ጥያቄ ከፈጠረባት በኋላ ሰይጣን ያደረገው በቀጥታ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መቃወም ነው "ሞትን አትሞቱም" በማለት። (ዘፍ 3፡4)

እግዚአብሔርን ውሸታም በማድረግ ሐጢአት እንደማያስቀጣና ዋጋም እንደማያስከፍል አድርጎ አቀርቧል። በዚህም ዘመን ቢሆን የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚክድ ሰው የመጽሐፍ ቅዱስን መለኮታዊ መገለጥ ይክዳል። (ማቴ 13፡40-42፣ ራዕይ 20፡11-15) በሐጢአት መክንያት የሚመጣውን ቅጣት መካድ የእግዚአብሔርን ህግ ደካማ ከማድረጉም በላይ በዕለት ከዕለት የህይወት ጉዞአችን የእግዚአብሔርን ህግ በትጋት እንዳንፈጽምና ለተጨማሪ ክፋት በር ይከፍታል።

6. **ምኞትን ወይም ፍላጎትን ለማነሳሳት እውነታዎችን ገልብጦ በተሳሳተ መልኩ ማቅረብ፡**

ሰይጣን እግዚአብሔርን እየከሰሰ ያለው ከፈጠረው ፍጥረት የደበቀው መልካም ነገር መኖሩን በማሳየት ነበር። "ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ።" (ዘፍ 3፡5)። ይህም እግዚአብሔር ራስ ወዳድ በመሆኑ የፈጠረው ፍጥረት እርሱን እንዳይመስል የደበቀው ነገር እንዳለ በማሳየት የሔዋንን ልብ ለማሸፈት የተፈጸመ ደባ ነው። ማክላረን የተባሉ ምሁር ይህን ክፍል ሲያብራሩ ሰይጣን ዛሬም ቢሆን እኛን ለማታለል እንዚህን ሁለት መንገዶች ያጠቀማል 1ኛ. "ብታደርገው አይጎዳህም" በማለትና 2ኛ. "መልካሙን ባለማድረግ እራስህን

ከመልካሙ እያራቅክ ነው" በማለት፡፡ በዚህ ክፍል እንደምንረዳው ሰይጣን መልካም የሚለው የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መጣስን ነው፡፡

በእርግጥ እግዚአብሔር ልጆቹ እርሱን እንዲመስሉ ይፈልጋል፡፡ ነገር ግን እንዴት ነው እርሱን መምሰል የሚቻለው? የሚለው ጥያቄ ቢነሳ መልሱ አትብሉ የተባለውን የዛፍ ፍሬ በመብላት ወይንም ትዕዛዙን በመጠበቅ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ፈቃድ በመውጣት የትክክለኛውንና የስህተቱን፣ የመልካሙንና የክፉውን ምንነት ለመለየት በሌላ መስመር ብንጠይቅ በራሳችን ላይ አደጋን እንደማምጣት ይቆጠራል፡፡ ምክንያቱም ለትክክልና ለስህተት ለመልካሙና ለክፉው ፍጹም ዳኝነት መስጠት የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነውና ነው፡፡

"ክፉውን መልካም መልካሙን ክፉ ለሚሉ፥ ጨለማውን ብርሃን ብርሃኑንም ጨለማ ለሚያደርጉ፥ ጣፋጩን መራራ መራራውንም ጣፋጭ ለሚያደርጉ ወዮላቸው! በዓይናቸው ጥበበኞች በነፍሳቸውም አስተዋዮች ለሆኑ ወዮላቸው!" (ኢሳ 5፡20-21)

እግዚአብሔርን በመታዘዝና በእርሱም ላይ በመደገፍ ብቻ

- እውነተኛ እውቀት፣
- እግዚአብሔርን መምሰል እና
- ሁለንተናዊ እርካታን እናገኛለን፡፡

7. **ያቀረበውን ማታለያ በተለያየ ሁኔታና ደራጃ ማጠናከር**

ሰይጣን በተጠቀመው የማታለያ ዘዴ ሔዋንን በእግዚአብሔር ቃልና ባህሪይ ላይ የነበራትን እምነት ሸርሽሮታል፡፡ ከፈተና በመራቅ ከአዳም ወይንም ከእግዚአብሔር ጋር በጉዳዩ ላይ ከመነጋገር ይልቅ በራሷ ፍላጎት በመነዳት የተከለከለውን የዛፍ ፍሬ በላች፡፡ (2ጢሞ 2፡22፣ ያዕቆብ 1፡14-15) ወደ ዛፉ ፍሬ ባየች መጠን ፍሬውን የመብላት ፍላጎቷ ይጨምር ነበር፡፡ ፈተናው የቀረበላት ለሁለንተናዋ ማለትም ለስጋዊ የምግብ ፍላጎትዋ፣ ለእውቀት የነበራትን ፍላጎት፣ እና መንፈሳዊ ምኞቷን ሊያሟላ በሚችል መልኩ ነው፡፡ (1ዮሐ 2፡16-17)

ትልቁ የሔዋን ስህተት ከእግዚአብሔር ይልቅ የሰይጣንን (የፈታኙን) ሐሳብ መቀበሏ ነው፡፡ ወደ ተከለከለው የዛፍ ፍሬ ባየች ጊዜ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ከመደገፍ ይልቅ በራሷ ፍላጎትና ምክንያታዊነት ላይ ተደገፈች፡፡ በመጨረሻም በፈተና ተሸነፈች፡፡ በራሷ ሙሉ ፈቃድ እና በምርጫዋ "ከፍሬውና ወሰደች በላች" (ዘፍ 3፡6)፡፡

8. **ፈተናን ወደ ሰው ማሻገሩ**

ሰይጣን ሔዋንን ለመፈተን ከፍጥረታት መካከል እባብን ነበር የመረጠው፡፡ አዳምን ሲፈትነው ግን የተጠቀመው ሔዋንን ነው፡፡ ብዙ የጠለቀ ነገር ስለታሪኩ ባናውቅም "ከፍሬውም ወሰደችና በላች ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ" የሚል ቃል እናነባለን (ዘፍ 3፡6) ለምን አዳም ተቀብሏት በላ? መጽሐፍ ቅዱስ አዳም እንዳልተታለለ ይናገራል (1ጢሞ 2፡14) ነገር ግን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከማክበር ይልቅ የሚስቱን ቃል ሰማ (ዘፍ 3፡17)፡፡ በመሆኑም ከፈጣሪው

ከእግዚአብሔር ይልቅ ረዳት እንድትሆነው በእግዚአብሔር በራሱ የተሰጠቻውን ፍጡሯን ሔዋንን የወደደ ይመስላል፡፡

በዚህ ዘመን ምን ያህል አማኞች (ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች) በተመሳሳይ ሁኔታ በፈተና ውስጥ ያልፉ ይሆን? ያልተገባ ወዳጅነት ከማያምኑ ሁነ ከሚያምኑ ጋር ማድረግ ለጥፋት መንገድ ከፋች መሆኑን ከአዳምና ከሄዋን ውድቀት መማር ያስፈልጋል፡፡

የመጀመሪያዎቹ ሰዎች እግዚአብሔርን ባለመታመን በፈቃዳቸው ሰይጣንን አደመጡ፣ የራሳቸውን ፍላጎት እንጂ የእግዚአብሔርን አልፈለጉም በመሆኑም ወደቁ፡፡

በአጠቃላይ በውድቀት ታሪክ

- ✓ ጥርጥር
- ✓ ፍላጎት
- ✓ ውይይት
- ✓ ውሳኔ እና
- ✓ አለመታዘዝ እናገኛለን፡፡

የእነዚህ ድምር ውጤት ነው ሐጢአት የሚባለውን ክፍ ጠላት ወደ ሰው ዘር እንዲገባና በእግዚአብሔርና በማህበራዊ ኑሮው መካከል እንቅፋት እንዲፈጠር ያደረገው፡፡

**የሐጢአት ትርጉም በዕብራዊያን አስተምህሮ**

1. ሐታ (Hata) ኢላማን መሳት ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ደረጃ ዝቅ ማለት
2. ፔሳ (Pesa) አመጻ ወይም መተላለፍ፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ ማመጽ
3. አዎን (Awon) ጥፋተኝነት ወይም ታማኝነትን ማጉደል ወይም ታማኝ አለመሆን፡፡ ከተቀመጠው ደረጃ ወደ ተቀራኒው አቅጣጫ መዞር (መዝ 51)

የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ያን ይህል አስቸጋሪ ሆኖ አልነበረም ይልቁንም ትዕዛዙ የሚያሳየው እግዚአብሔርን የማምለክና ያለማምለክ ነጻ ፈቃድን የመጠቀም መብት እንጂ፡፡[2]

**ይህንን በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ አምልኮ ባለመፈፀሙ እና ሐጢአትን በማድረጉ ሐጢአት በሰውና በአካባቢው ላይ ያደረሰውን ውጤት እናያለን**

***1. በማንነቱ (personality) ላይ ችግር ፈጥሮበታል፡፡***

እርቃናቸውን በማየት ሐፍረት እንዲሰማቸው ሁኗል፡፡ ምንም እንኳ ውጫዊ ሐፍረታቸውን ለመሸፈን ቅጠልን ማገልደም እንደአማራጭ ቢወስዱም የውስጥ ባዶነታቸውን ሊሸፍን አልቻለም ነበር፡፡ በመሰረቱ ዘፍጥረት አንድ ላይ እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት መልካም እንደሆነ አየ የሚለውን ስናነብ በሰው የአካል ክፍል ይህ ብልት ንጹህ ይህኛው ደግሞ እርኩስ ወይም ክፉ ነው ማለት እንችል ይሆንን? ከዚህ ክፍል አኳያ የትኛውንም የአካላችን ክፍል እርኩስ (ክፉ) ማለት አንችልም ነገር ግን ይህ ክፉ ነው ብሎ መደምድም ያስቻለው በአዕምሮአቸው ውስጥ ሲሆን

[2] የመጀመሪያው ፈተና ከሚለው ስር የተዘረዘሩት ስምንት ነጥቦች በፖል ቢ. ሆፍ ከተዘጋጀ ዘፍጥረት(ጄነሲስ)፣ አይ.ሲ. አይ ዩኒቨርሲቲ፣ ዩ.ኤስ.ኤ፣ 1998 ዓ/ም እትም

ይህም በራሳቸው መልካምና ንጹሑን ክፉ ወይም ነውር አድርገው እንዲያዩ አድርጓቸዋል፡፡ ከዚህም ጊዜ ጀምሮ ለመልካም የተፈጠረው ሰውነት ለአመጻና ለእርኩሰት መጠቀሚያ ሆነ፡፡ እግዚአብሔርም ለአዳምና ለሔዋን ለነቃው ህሊናቸው ሽፋን ይሆነ ዘንድ ቁርበትን አለበሳቸው፡፡

***ሀ. መንፈሳዊውንም ሆነ ማህበራዊ (ወደላይ እና ወደጎን ያለውን) ግንኙነት አበላሽቶበታል፡፡***

የበደለኝነት ስሜትና፣ ፍርሃት በእግዚአብሔር ላይ የነበራቸውን መታመነንና ለእርሲም የነበራቸውን ፍቅር ተክቶታል፡፡ ለዚህም ነው አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ፊት የተሸሸጉት፡፡ ሐጢአት ሁልጊዜ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያለቸውን ህብረት በማበላሻት ከእግዚአብሔር ፊት ወይም መገኘት እንዲሸሹና እንዲርቁ ያደርጋል፡፡ ከስነመለኮት አንጻር ሲታይ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ህብረት ማፍረስ የህይወት ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር መለየት ነው ደግሞም መንፈሳዊ ሞት ነው፡፡

**ለ. በኤደን ገነት የተዘጋጀለትን አቅርቦት (providence) አሳጥቶታል፡፡**

ሰው በሐጢአት ከመውደቁ በፊት በኤደን ገነት ሁሉም ነገር ተዘጋጅቶለት ነበር በመሆኑኑም ያለስጋትና ያለጭንቀት ነበር ህይወቱን የሚመራው፡፡ ሐጢአት ግን ይህንን ትልቅ እድል አሳጥቶታል

**ሐ. ሞትን አስከትሎበታል**

ፍሬውን በበላበት በዚያው ዕለት መንፈሳዊ ሞት ሞተ፣ ይኸውም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ጤናማና መልካም ግንኙነት አበላሽቶበታል የዘላለም ሞትንም አስከትሎበታል፡፡ ቀጥሎም ስጋዊ ሞት ሞተ መጨረሻውም የዘላልም ፍርድ ሆነ፡፡

**2. እግዚአብሔር እባብንና ምድርን ረገመ (course)**

«እግዚአብሔር አምላክም እባብን አለው፡፡ ይህን ስላደረግህ ከእንስሳት ከምድር አራዊትም ሁሉ ተለይተህ አንተ የተረገምህ ትሆናለህ በሆድህም ትሄዳለህ፡፡ አፈርም በህይወትህ ዘመን ሁሉ ትበላለህ» እግዚአብሔር አዳምን አለው «የሚስትህ ቃል ሰምተኃልና÷ ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተኃልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን ፤ በህይወትህ ዘመን ሁሉ ከእርሷ በድካ ትነበላለህ፤» ከዚህ ዝየምንረዳው የአዳም እና የሔዋን ዋጋቸው በተረገመች ምድር ዋጋ ከፍለው መኖር ነው፡፡

***3. አዳምና ሔዋን እንዲሁ በሐጢአታቸው ምክንያት ተቀጡ ወይም ፍርድ (Judgment) ተላለፈባቸው፡፡***

በአጠቃላይ ውድቀት ያመጣው የተጠበቀውን እንደ እግዚአብሔር መሆንን ሳይሆን ይልቁንም በእነርሱ ውስጥ የነበረውን የእግዚአብሔርን መልክ አበላሸው፡፡

ክፉን በመረጃ ደረጃ ማወቅ አንድ ነገር ነው አደገኛና የሚያስቀጣው ግን ክፋትን በህይወት ስንለማመደው ነው፡፡

በዚህ ክፍል ከውድቀት ጋር በተያያዘ እንደማጠቃለያ የምናየው የመልካም ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር እንደሆነና ይህንንም የፈጠረውን ፍጥረት መልካም እንደሆነ አየ ከሚለው ስንረዳ በተቃራኒው ደግሞ የክፋት ምንጭ ሰይጣን መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

## ሐ. የመቤዠት ተስፋ

ከላይ የሰውን ውድቀት እና የእግዚአብሔርን ምላሽ አይተናል፡፡ የዘፍጥረት ጸሐፊ የእግዚአብሔርን እርግማንና ፍርድ ብቻ ነግሮን ሊያበቃ አልፈለገም ይልቁኑ ታላቁንም የመቤዠት የተስፋ ቃል ይገልጣል እንዲህ በማለት "በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ፡፡" (ዘፍ 3፡15)

ከዚያም ለአዳምና ለሔዋን ሐፍረታቸውን ለመሸፈን ያደረጉትን ጥረት በማየት ለአዳምና ለሔዋን ለስጋ ብቻ ሳይሆን ለመንፈሳዊ ህይወታቸው የሚከፈለውን ዋጋ በሚያሳይ መልኩ እግዚአብሔር ራሱ የመጀመሪያውን መስዋዕት በመሰዋት መሸፈኛ ይሰጣቸዋል፡፡ ይህም እግዚአብሔርን ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅርና ርህራሔ ያሳያል፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** የዘፍጥረት 3፡1 ባለው ክፍል ብቻ ነው እባብ ቃል በቃል በእንስሳነት ተገልጦ ከሰይጣን ማለትም ከእግዚአብሔር ዋና ጠላትና ሰዎችን ካሳተው ጋር ግንኙነት ያለው ሁኖ የምናው፡፡ በእርግጥ በዚህ ክፍል ሰይጣን በስም አልተጠቀሰም፡፡ በሌሎች ክፍሎች ግን ለምሳሌ 1ቆሮንቶስ 11፡13-15 ጳውሎስ ሴቲቱን ያሳታት ሰይጣን መሆኑን ይናገራል፡፡ በራዕይ 20፡2 "የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው፥" ተብሎ ተጠቅሷል፡፡

### የሐጢአት መስፋፋት

**ዘፍጥረት አራት**

ሰው እግዚአብሔርን ከሚያመልክበት፣ በእግዚአብሔር አቅርቦት ከሚደሰትበትና ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ከሚያደርግበት ከኤደን ገነት ከተባረረ በኋላ የደረሰበትን የህይወት ውጣ ውረድ ጅማሬ በዚህ ክፍል እናነባለን፡፡

አዳምና የሔዋን የመጀመሪያዎቹን የሰው ልጅ ዝርያዎች ሲወልዱ ማለትም ሁለተኛውን ትውልድ እናያለን፡፡ ወንድማማቾቹ ቃየልና አቤል እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚያደርጉትን ጥረት ይደርጋሉ፡፡ ሁለቱም የአምልኮ ሰዎች ስለመሆናቸው ታሪኩ ያስነብበናል፡፡ ይሁንና ለምን እግዚአብሔር የቃየንን ትቶ የአቤልን መስዋዕት ተቀበለ? ምክንያቱ የሁለቱ አቀራረብ ሲመዘን የአቤል በትክክለኛው የቃየን ደግሞ ትክክል ባልሆነ ሁኔታ በመቅረቡ ነው፡፡ ብዙ ምሁራን ቃየንና አቤል እግዚአብሔርን እንዴት ሊቀርቡ እንደሚገባ አስቀድሞ በመለኮታዊ መገለጥ ተረድተው ነበር እንደሚሉ ጆርጅ አሳድ የተባሉ ምሁር ይገልፃሉ፡፡[3]

የወንድማማቾቹ ልዩነት ምንጩ የውስጣቸው ዝንባሌ መሆኑን የዕብራዊያን መልዕክት ጸሐፊ ያስረዳል፡፡ "አቤል ከቃየል ይልቅ የሚበልጥን መስዋዕት ለእግዚአብሔር በእምነት አቀረበ.." (11፡4)

**ውጤቱም፡-** የመጀመሪያውን የእምነት ሰማዕት እና የመጀመሪያውን ነፍሰ ገዳይ አስገኝቷል፡፡

[3] ጆርጅ አሳድ አምስቱ የህግ መጽሐፍት፡ የጥናት መርጃ. አይ.ሲ.አይ ዩኒቨርሲቲ - 2004. ገጽ 25

ይሁንና ምህረት የእግዚአብሔር ቀዳሚው ባህሪይ በመሆኑ በቃየል ግንባር ላይ ያገኘው ሁሉ እንዳይገድለው ምልክት ሲያደርግበት እናያልን፡፡ ሌላው በዚህ ክፍል የምናገኘው ትምህርት የስልጣኔን መስፋፋት፣ የሐጢአት መስፋፋትና ምድርን ማዳረስ፣ በሐጢአት ከተጨማለቀው እንደ ቃየል ካለ ሰው ጋር እግዚአብሔር የሚገናኝበት የጸጋውን ብዛትም እንማራለን፡፡

እንዲሁም በአንድ በኩል የቃየል ተስፋ የሌለው በሌላ በኩል ደግሞ መጪው ጊዜ በተስፋ ዘር ሐረግ በ“ሴት” በኩል መጀመሩን እናገኛለን፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዘፍ 4 የቃየንን ትውልድ ታሪክ እናነባለን፡፡ የቃየን ልጆች ከተማን ሰሩ (ዘፍ 4፡17)፡፡ ከአንድ ሚስት በላይ ማግባትን መለማመድ ጀመሩ (4፡9)፡፡ አምባ ገነኖች ነበሩ (4፡23-24)፡፡ የ‹ሴት›ን ትውልድ በተደጋጋሚ በመውረራቸው ሐጢአተኛነታቸው ይታያል፡፡ ያልተገባ ጋብቻ በመፈጸም፣ በአንድ ላይ በመኖርና እንደ አንድ ሰው በመሆን በእግዚአብሔር ላይ ሐጢአትን በማድረግ በክፋታቸው ምድርን አረከሷት፡፡

# ትምህርት አራት፡

## ዘፍጥረት አምስት

## 4.1. ቅድመ ጥፋት ውሃና የጥፋት ውሃ

### ሀ. ቅድመ የጥፋት ውሃ ታሪክ

ይህ ምዕራፍ በአዳምና በኖህ መካከል ያለውን ረጅም ዘመን በማገናኘት እንደ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በዚህ ጊዜ

- የሐጢአት የመግደል ኃይል ገና ወደ ሙላት አልደረሰም ነበር፡፡
- በዚህ ክፍል የተጠቀሱት ሰዎች የኖረበት ዘመን በጊዜው በነበሩት ጋር ሲነጻጸር ይበዛ ነበር፡፡

ይህንን የእድሜ ዝርዝር ሀሳብ በማንሳት ይህ የእድሜ ዝርዝር ሁኔታ የሚገልጸው የሰዎችን እድሜ ሳይሆን የጎሳዎችን ነው ብለው የሚከራከሩ አልታጡም፡፡ ማቱሳላ 969 ዓመት ሲኖር የእርሱ ልጅ ላሜህ ግን 777 ዓመት ኑሯል፡፡ በዘፍጥረት አምስት የምናገኘው የቅድመ አባቶች የእድሜ ጣራ በአማካይ 847 ዓመት ነው፡፡

በሌላ በኩል የምናገኘው አስደናቂ ትምህርት ደግሞ መንፈሳዊ ሕይወቱ ወይም አረማመዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገው ሰው ደግሞ ከሌሎች ያነሰ እድሜ መኖሩ ነው፡፡ ይህም በቅድመ አባቶች ዘመን ከተዘረዘሩት አስር ትውልዶች መካከል አጭሩ እድሜ የሄኖክ መሆኑን ነው፡፡ ይህም የሚያሳየን ሰው በምድር ላይ ከኖረበት የዘመን ብዛት ይልቅ ዋናውና አስፈላጊው የአኗኗሩ ሁኔታ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረው ጤናማ ህብረት መሆኑን ነው፡፡

### *ስለ ሔኖክ የሕይወት ምስክርነት ጥቂት እውነቶች*

1. ሔኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ (ዘፍ 5፡22)
2. እግዚአብሄርን አስደሰተ (ዕብ 11፡5)
3. ስለ እግዚአብሔር መሰከረ (ይሁዳ 4)

ይህንን የቅድመ አባቶች ዘመን የእድሜ ጣራና የአባቶችን የእድሜ ጣራ ስናመዛዝን ጥያቄ የሚፈጥር ሁኔታ ይገጥመናል፡፡ ለምሳሌ፡-

| የአባቶችን የእድሜ ጣራና የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል | | | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የአባቶች ስም | የእድሜ ጣራ | ማጣቀሻ |
| 1 | አብርሃም | 175 ዓመት | ዘፍጥረት 25፡7 |
| 2 | ይስሐቅ | 180 ዓመት | ዘፍጥረት 35፡28 |
| 3 | ያዕቆብ | 147 ዓመት | ዘፍጥረት 47፡28 |
| 4 | ዮሴፍ | 110 ዓመት | ዘፍጥረት 50፡22 |

ሰንጠረዥ 3

**ዘፍጥረት ስድስት**

## ለ. የጥፋት ውሀ

እንደ ስታንሊ አውተላው[4] በዘፍ 6፡1-8 ያለውን ሐሳብ ወደ ጥፋት ውሃ የሚመሩ ሁኔታዎች በማለት ይከራከራሉ ምንም እንኳን ሁሉም ምሁራን በይስማሙበትም፡፡ በዚህ ክፍል የምናገኘው የመጀመሪያው አከራካሪ ትምህርት የአምላክ ልጆች ከሰው ልጆች ጋር ጋብቻ የመመስረታቸው ሁኔታ ነው፡፡ እነዚህ “የሰውን ልጆች” የሚባሉት ያገቡት “የአምላክ ልጆች” የተባሉትን የወደቁት መላዕክት ናቸው በዚህም ጋብቻ ምክንያት በአካላቸው ትልልቅ ወይም ግዙፍ የሆኑ ሰዎች ተወለዱላቸው በሌላ በኩል ደግሞ የአምላክ ልጆች የሚባሉት እግዚአብሔርን የሚፈራው “የሴት” ትውልድ ሲሆኑ የሰውን ልጆች ማለትም እግዚአብሔርን የማይፈራው የቃየንን ወገን በማግባት መንፈሳዊ ህይወታቸውን ያበላሹት በዚህም ጋብቻ ምክንያት የተወለዱት ሰዎች በጣም አስቸጋሪዎችና ማንንም የማይፈሩ ስርዓት አልበኞች የሆኑ ሊሆን ይችላሉ፡፡

ይህም ባህሪያቸው ወደ ከፍተኛ ክህደት ወይም ከመስመር የወጣ አካሔድ እንዲሄዱ አደረጋቸው የእግዚአብሔርም ቁጣ በሰዎች ላይ ነደደ፡፡

**ቁጥር** 6 እግዚአብሔርም ሰውን በመፍጠሩ ተጸጸተ ይላል፡፡ ይህን ሲል ግን ሰውን መፍጠር አልነበረብኝም እያለ ሳይሆን ከፈጠርኩት ዓላማ እና ክብር ተለይቶ ወደቀ እንዲሁም ለክብር እና ለመልካም ተግባር የፈጠርኩት ሰው ፍጻሜውን አበላሸ የሚል ጸጸት ነው፡፡ ስለ እግዚአብሔር መጸጸት እነዚህን ተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በጥንቃቄ ተመልከት (1ሳሙ 15፡35፣ 1ዜና 25፡15፣መዝ 106፡45፣ አሞጽ 7፡3 እና 6)

**ምዕራፍ 6፡8** እግዚአብሔር ባለጸጋ እና ምህረቱ የበዛ በመሆኑ አሁን ሊመጣ ያለው ፍርድ የሰው ልጆች የታሪክ ፍጻሜ አይደለም፡፡

**ቁጥር 11፡** ትውልድ ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ሲያምጽ ኖህ ግን አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፤ በመሆኑም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አገኘ:: ይህ ክፍል እግዚአብሔር ራሱን ያለ ምስክር አይተውም የሚለውን የአዲስ ኪዳን ትምህርት በተጨባጭ የምናይበት ክፍል ነው፡፡

**ቁጥር 22፡** እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት የመርከቡን ሥራ አጠናቀቀ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አደረገ፤ ለትውልድ ጸድቅን አስተማረ በመጨረሻም ለፍጥረት የድነት መተላለፊያ መንገድ ሆነ፡፡

## ሐ. የጥፋት ውሀ እና አዲስ ጅማሬ ዘፍጥረት 6፡9-9 እና 29

### 1. የጥፋት ውሃ ሁኔታ

- ✓ ለጥፋት ውሃ መምጣት የተደረገ ዝግጅት
- ✓ የጥፋት ውሃ መምጣቱ
- ✓ የጥፋት ውሀ ያስከተለው ውጤት

[4] ኤች.ዲ. ሐሪሰን (አሪታኢ) የብሉይ ኪዳን ዳሰሳራንደል ሃውስ ፐብሊኬሽን፣ ዩ.ኤስ፣ኤ፣1993 ገጽ10

ምድርና በእርሷ የነበረው ሁሉ ከኖህና በመርከቧ ከእርሱ ጋር ከነበሩት በስተቀር ጠፍተዋል፡፡ በአንድ በኩል በጥፋት ውሃው የእግዚአብሔርን አለም ዓቀፋዊ ፍርድ በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔርን ወደር የሌለው ጸጋና ምህረት በእነዚያ ጥቂት ሰዎች ተገልጦ ትውልድ ሲቀጥል እናያለን፡፡ ጻድቁን ከሐጥዑ ጋር አይቀጣምና፡፡

2. የጠፋውን ዓለም እንደገና መገንባት
    - ✓ ደረቅ የመሬት አካል መታየት ጀመረ
    - ✓ የኖህ መርከብ፣ እንስሳዎቹና መርከቧ
3. የኖህ መሰዊያ

በዘፍጥረት 8፡20 የመሬቱን መድረቅ ተከትሎ ኖህ የወሰደውን እርምጃ እናያለን፡፡ የእግዚአብሔርን ታላቅ ጸጋ በመረዳት መሰዊያን ሰራ፡፡ ይሄ መሰዊያ በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው መሰዊያ ነው፡፡

**የኖህ መሰዊያ ሁለት አላማዎች**

ሀ. እግዚአብሔር ስላደረገለት ምስጋና ለማቅረብ

ለ. የሐጢአት ማስተሰሪያ መስዋዕት ነበር

4. እግዚአብሔር ለኖህ የገባለት ቃልኪዳን

እግዚአብሔርም የመስዋዕቱን መዓዛ አሸተተ ከኖህም ጋር ቃልኪዳን አደረገ፡፡ ቃል ኪዳን በሁለት አካላት መካከል የሚደረግ የስምምነት ውል ነው፡፡ አብሮ የመሆንና የመርዳት ከዚያም ላለፈ ግንኙነት የሚደረግ ስምምነት ማለት ነው፡፡ አንዳንድ ምሁራን ቃልኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው በዘፍ 6፡18 ሲሆን ሃሳቡ ግን ድጋሚ መሆኑን ይስማማሉ፡፡

**ለግንዛቤ እንዲሆን፡- በመጽሐፍ ቅዱስ የተዘረዘሩት ዋና ዋና ኪዳናት ተብለው በስነ መለኮት ምሁራን ዘንድ የሚታመንባቸው ከዚህ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል**

1. በኤደን ገነት ከአዳም ጋር የተገባ ቃልኪዳን
2. የኖህ ቃልኪዳን (ዘፍ 9)
3. የአብርሃም ቃልኪዳን (ዘፍ 15 እና 17)
4. የሙሴ ወይም የሲና ቃልኪዳን (ዘጸ 19፡24)
5. ለፊንሀስ የተገባው ቃልኪዳን (ዘሁ 25፡10-15)
6. የዳዊት ቃልኪዳን (2ሳሙ 7፡5-16)
7. አዲስ ኪዳን (ኤር 31፡31-34) ናቸው አንዳንድ ምሁራን ሌሎችንም ያካትታሉ፡፡

**ለኖህ የተገባው ኪዳን ዝርዝር**

- ✓ እግዚአብሔር ዳግመኛ ምድርን በውሃ እንደማያጠፋ (8፡21)
- ✓ የመብዛት ተስፋ (9፡1)
- ✓ የሰው ልጅ የገዥነት ስልጣን መመለስ (9፡2)
- ✓ የእንስሳት ሁሉ የመመገብ ፈቃድ (9፡3)

- ✓ ደም እንዳይመገቡ የተሰጠ ትዕዛዝ (9፡4)
- ✓ ሰዎች እንዳይገደሉ የተሰጠ ትዕዛዝ (9፡5-6)

**ከጥፋት ውሃ በኋላ የተሰጠ ተስፋ**

1. ከሰው ክፋት የተነሳ ዳግመኛ ምድር አትረገምም
2. የወቅቶችና የጊዜያት ሥርዓታቸውን ጠብቀው መፈራረቅ
3. በጥፋት ውሃ ዳግመኛ ዓለም ዓቀፋዊ የህይወት ጥፋት አይኖርም

**ዘፍ 9፡20-27 በኖህ እና በልጆቹ መካከል የተፈጠረው ሁኔታ**

በጥንታው ዘመን ታሪክ አወዛጋቢ ከሚባሉ ጉዳዮች መካከል አንዱ የዚህ የምንባብ ክፍል የምንመለከተው ጉዳይ ነው፡፡ ብዙ መቶ ዓመታትን በጽድቅ ከተጓዘ በኋላ ኖህ በመስከር ትልቅ ስህተት ሰራ የሚሉ ወገኖች አልታጡም፡፡ ኖህ የነበረበት ሁኔታ ኖህን ጻድቅ ያስብለዋል ወይስ ጽድቁን ይቀንሳል? የኖህን ጊዜያዊ ሁኔታን አይቶ መፍረድ ወይም መኮነን ይቻል ይሆን? ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ የምናቸው የእምነት አባቶች የአዲስ ኪዳንና እኛንም ጨምሮ ከድካም ነጻ ነበሩ ወይም ነጻ ነን የሚል ሀሳብ ወይም አስተምህሮ አናገኝም፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ ጻድቅና እንከን የማይገኝበት ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ በመሆኑ ነው፡፡ ይሁንና ጸሐፊው ስለኖህ ስካር ብዙም መናገር ሳያስፈልገው ስለልጆቹ መባረክና እርግማን መጻፍን መርጧል፡፡ የከነዓን አባት ካም የአባቱን ዕርቃን አይቶ ለወንድሞቹ ነገራቸው፡፡ ሴም እና ያፌት ግን የአባታቸውን ዕርቃን ሳያዩ የኖህን ስጋ ሸፈኑ፡፡

## እርግማንና በረከት

የኖህን ሐፍረተ ስጋ የገለጠው ካም ሲሆን ለምን ከነዓን ተረገመ የሚለው የብዙዎቻችን ጥያቄ ሊሆን ይችላል፡፡ ለዚህ ጥያቄ መልስ ይሆናሉ ተብሎ ከሚታሰቡ አመለካከቶች መካከል ሦስቱን እንመልከት፡

1. የኖህ በረከትም ሆነ እርግማን ትንቢታዊ እንጂ ወቅታዊውን የልጆቹን ሁኔታ ተንተርሶ የተደረገ የስሜታዊነት ውጤት አይደለም፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ነገ ምን እንደሚሆን አዋቂ ነውና የሚል፡፡
2. ታሪኩ የተከናወነው ምናልባትም ከጥፋት ውሃ በኋላ ዘግይቶ ሊሆንና በዚህ ጊዜ ከነዓንም ተወልዶና አድጎ እንዲሁም በአባቱ ሐጢአት ተባብሮ ይሆናል የሚል፡፡
3. የአባቶች የስራ ውጤት በራሳቸው ላይ ብቻ ሳይሆን በትውልዳቸው ላይም ይተላለፋል የሚሉ ናቸው፡፡ ዘጸዓት 20፡5-6 እንዲህ ይላል "በሚጠሉኝ እስከ ሶስተኛው እና አራተኛው ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ለሚወድዱኝና ትዕዛዜን ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምህረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር ነኝና"

የመጀመሪያዎች ሁለቱ ሀሳቦች ለክርክር በር ይከፍታሉ፡፡ በመጽሐፉ ውስጻ በዝርዝር የተቀመጡ አሳማኝ ሁኔታዎች እስካልተገኙ ድረስ ማከራከሩ አይቀሬ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የኖህ እርግማን በሐም ላይ ያስከተለው ውጤት ይታያል፡፡ ተጨማሪ ጥያቄ የሚነሳው ግን ኖህ ለምን ሐምን ረገመ? የሐም ሐጢአት ምንድን ነበር? የሚል ነው፡፡

የሐምን ሐጢአት በተመለከተ ቢያንስ ሁለት አመለካከቶች ይንሸራሸራሉ፡፡

1. በድካም ውስጥ ላለ ሰው ከመራራት ይልቅ ድካሙን ወደ አደባባይ ማውጣት
2. ለአባቱ የማይገባ ክብር መስጠቱ ነው የሚል ነው፡፡

**1. በድካም ውስጥ ላለ ሰው ከመራራት ይልቅ ድካሙን ወደ አደባባይ ማውጣት**

ሀ. አማሌቃዊያን የእስራኤልን መድከም በመረዳት ደፈጣ ጠብቆ ጉዳት አድርሶበታል (ዘዳ 25፡17-18) “ከግብጽ በወጣችሁ ጊዜ አመናሌቅ በመንገድ ላይ ያደረገብህን አስብ በመንገድ ላይ እንደተቃወመህ አንቴም ተስኖህ ደክሞህ ሳለህ ከአንተ በኋላ ደክመው የነበሩትን ሁሉ እንደ መታ እግዚአብሔርንም አልፈራም፡፡”

ለ. ዘጸዓት 34፡4 የእስራኤልን መሪዎች (እረኞች) በደካሞች ላይ ባሳዩት የራስ ወዳድነት ብልጫ በተለይ ህዝቡን በጭካኔና በኃይል በመምራታቸው ተወቅሰዋል፡፡

ሐ. እንባቆም 2፡15-16 ሌላኛውን ሰው በማስከር የተደረገ ራስ የማስደሰትና በሰካራሙ ላይ መዘባበት ባህሪያ (እንባ 2፡8)

**2. ለአባት (ለወላጅ) የማይገባ ክብር መስጠት ( ዘጸ 20፡12)**

አባትና እናትን የማክበር ትዕዛዝ ከዘስርቱ ህግጋት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ መታዘዝ እድሜን ያረዝማል፡፡ (ዘፍ 1፡11፣ ምሳ 1፡7፣ ኤፌ 4፣ እና ቆላ 3)

ሀ. የኖህ እርግማን በሐም ትውልድ ሁሉ ላይ ደረሷል ይላሉ፡፡

ለ. የአፍሪካዊያን የቀለም ጥቁረት የእርግማኑ ውጤት ነው ብለው ያምናሉ፡፡

ይህም አመለካከት በአፍሪካዊያን እና ጥቁር ቆዳ ባላቸው ህዝቦች ላይ ዘረኝነትን ለማስፋፋት እንደማረጋገጫ እንዲወስዱ እንዳደረጋቸው ይታመናል፡፡ በመሆኑም እጅግ አስከፊ በሆነ ሁኔታ አፍሪካዊያን በነጮች እንደባሪያ ሲሸጡና ሲለወጡ የቆዩት ከዚህ አመለካከት የተነሳ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ስለቀለም የተሰጠ አስተምህሮ የሚደግፍ አንድም ክፍል አናገኝም፡፡

ኖህ ሴምን ባረከው ከወንድሞቹም የበላይ አደረገው ከነዓንንም ባሪያው አደረገው ደግሞም ለያፌት በሴም ድንኳን እንደሚኖር አረጋገጠለት፡፡ ይህም ይላሉ ምሁራን ከሴም ነገድ የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ለብዙዎች መመኪያና መጠጊያ እንደሚሆን ትንቢታዊ መልዕክት አለው ይላሉ፡፡ ከዚያም በምዕራፍ 10 ላይ የኖህ ልጆች ምድርን ሲሞሏት ይሞሏታል፡፡ እነዚህ ሰባዎች የትውልድ ሀረጎች በቀጣዩም የብሉይ ኪዳን ታሪክ የህዝቦች መሰረት ይሆኑ ዘንድ የተመረጡ ናቸው፡፡

## ትምህርት አምስት

### ዘፍጥረት 10

### ሰዎች ከጥፋት ውሃ በኂላ ፡-

በዘፍጥረት 11፡9 ሰዎች ባቢሎን “Babel” ይኖሩ ነበር፡፡ የከተማይቱ ትርጓሜ “የእግዚአብሔር መግቢያ በር” “the gate of God” ማለት ይሁን እንጂ በመጨረሻ ግን በህዝብ አመጽ ምክንያት የእግዚአብሔር ፍርድ የተገለጠባት እና የሰዎች ቋንቋ የተደበላለቀበት ከተማ ሆነች፡፡

ከጥፋት ውሃ በኂላ የሴም ነገድ ወደ ምስራቅ እሲያ ያፌትም ወደ ምዕራብ አውሮጳ አካባቢ ተሰደዱ ደግሞም የሐም ትውልድ ወደ መካከለኛ ምስራቅና ወደ አፍሪካ እንደሄዱ ይታመናል፡፡

የኖህ ልጆች ወደ አለም ሁሉ ከመበተናቸው በፊት አንድ የተከናወነ ነገር ነበር እርሱም በባቢሎን ግንብ የቋንቋ መደበላለቅ፡፡ ለራሳቸው ስምን ለማድረግ ወደ እግዚአብሔርም ለመድረስ በነበራቸው መልካም ያልሆነ ተነሳሽነት ግንብ በመገንባት ላይ ሳሉ እግዚአብሔር ቋንቋቸውን በመደበላለቅ ሃሳባቸውን ከንቱ አደረገ፡፡ ሰዎች የገነቡት ረዥም ግንብ ሰማይና እና ምድርን የሚያገናኝ ማማ እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ የአምልኮ ማዕከል ሊሆን እንደሚችል ጆርጅ አሳድ የተባሉ ሰው አሊስ የተባሉ ሥነ መለኮት ምሁርን ሀሳብ በመጥቀስ ተናግረዋል፡፡

እግዚአብሔር ለምን ጣልቃ ገብቶ ስራቸውን አስቆመ የሚለው ጥያቄ ምሁራንን የተለያየ አመለካከት እንዲያራምዱ አድርጓቸዋል፡፡ የሚሰጡትንም ምክንያቶች እንደሚከተለው እናያቸዋለን፡፡

1. ድርጊታቸው እግዚአብሔር ምድርን ሙሉአት ያለውን ቃል ወይም ትዕዛዝ የሚጻረር በመሆኑ ነው የሚሉ
2. ምክንያቱ ከትዕቢት የተነሳ (የመነጨ) በመኖሩና እግዚአብሔር እስካለበት ለመድረስ ያለመ በመሆኑ ነው የሚሉ
3. ግንቡ የመጀመሪያው የሐሰት አምልኮ ሥፍራ እንዳይሆን ለማድረግ ነው የሚሉ
4. እግዚአብሔር ወደፊት ሊያደርገው ላቀደው እቅድ አንድነታቸው እንቅፋት ሊሆን ስለሚችል ከወዲሁ መገታት ስላለበት ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ፍርድ ምህረቱን ያሳያል ምክንያቱም ከዚህ ቋንቋው ከተደባለቀ ህዝብ መካከል፤ ለምድር አህዛብ ሁሉ በረከት የሚሆን ህዝብን ለራሱ መርጧልና፡፡

# ትምህርት ስድስት

## 1፡3. የአባቶች ዘመን (Ptriarical Period)

በዚህ በአባቶች ዘመን ውስጥ ከአብርሃም እስከ ዮሴፍ ያለውን ታሪክ እናጠናለን፡፡

### ሀ. የአብርሃም ታሪክ (ዘፍ 12፡1-25)

የአብርሃምን ታሪክ ስናጠና ከእርሱ ህይወረት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ክንውኖች ጎን ለጎን መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ቀጥሎ የምናየው ሠንጠረዥ ይህንን ሃሳብ በግልጽ ያሳየናል፡፡

| ተ.ቁ | ድርጊት | የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻ | የሰዎቹ እድሜ |
|---|---|---|---|
| 1 | ወደ ከነዓን መግባቱ | ዘፍ 12፡4-5 | 75 |
| 2 | የእስማኤል መወለድ | ዘፍ 16፡15-16 | 86 |
| 3 | የቃል ኪዳ ምልክት መቀበሉ | ዘፍ 17፡1-2፤24 | 99 |
| 4 | የይስሐቅ መወለድ | ዘፍ 21፡1-5 | 100 |
| 5 | የሳራ መሞት | ዘፍ 23፡1-2 | 137 |
| 6 | የይስሐቅ ጋብቻ | ዘፍ 25፡20 | 140 |
| 7 | የአብርሃም መሞት | ዘፍ 25፡7-8 | 175 |

ሰንጠረዥ 4

### 1.1. አብርሃም እግዚአብሔርን የተረዳበት መንገድ

እግዚአብሔር ለአብርሃም የተገለጠባቸውን መንገዶች መሠረት በማድረግ እግዚአብሔርን በተለያየ ስያሜዎች ጠርቶታል፡፡ ለምሳሌ፡-

- ልዕል እግዚአብሔር (ኃያል አምላክ) ዘፍ 14፡18-20
- የሚያይ እግዚአብሔር (ዘፍ 16፡11-13)
- ሁሉን የሚያዘጋጅ እግዚአብሔር "Jehovah-jarah" or "the lORD will provide" (22:13-14)

### 1.2. የሰዎች የስም ስያሜ እና ትርጉም

በአብርሃም ዘመን የሰዎች መጠሪያ ስም ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት እና ተግባራቸውን ያመለክታል፡፡

**አብራም/ አብርሃም** ከዘፍ 17 በፊት አብራም የሚል ስያሜ የነበረው ሲሆን ስሙ ሳይለወጥ ከእግዚአብሔር የተቀበለው ተስፋ 12፤3 በምድር የሚኖሩ ህዝቦች በአንተ ይባረካሉ የሚለው ተስፋ ፍጻሜ ያገኘው ከዘፍ 17 በኂላ ነው ማለትም ስሙ አብርሃም ወይም የብዙዎች አባት የሚለው ከተሰጠው በኃላ፡፡

***ሦራ /ሣራ፡*** የአብርሃም ሚስት የመጀመሪያ ስም ሦራ ሲሆን በዘፍ 17፡15 ግን ሣራ ተብሎ ተቀይሯል፡፡ ትርጉሙም የነገስታት እናት ማለት ነው (ሮሜ 9፡8-9)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሌሎችን ሰዎች እና የቦታዎችን ስያሜዎች እንመልከት፡፡

- ❖ እስማኤል (16፡11) እግዚአብሔር ይሰማል
- ❖ ይስሐቅ (17፡17-19) መሳቅ፣ እግዚአብሔር በሳቅ ሞላኝ
- ❖ ያዕቆብ ዘፍ 32፡28 እና 35፡10 እስራኤል ተብሎ ተቀየረ
- ❖ ቤቴል (28፡16-19) የእግዚአብሔር ቤት

## 1.3. የአብርሃም ዝግጅት

### ሀ. የአብርሃም መገኛ ዘር "His Human Origin"

የታራ ትውልድ፡ አብርሃም ናኮር እና ሃራን የታራ ልጆች ናቸው (ከዘፍ 11፡27)፡፡ አብርሃም እግዚአብሔርን በመታዘዙ እና አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጉ የእግዚአብሔር ወዳጅ ተብሎ ተገልጿል፡፡ (2ዜና 20፡7፣ ኢሳ 41፡8) በዚህም በእግዚአብሔር የድነት ዕቅድ ውስጥ ትልቁን የተልዕኮ መሰረት እንደጣለ እንመለከታለን፡፡

### ለ. የአብርሃም መጠራት፡ (ዘፍ 12፡1-14፤ 24)

አብርሃም የአደገበት ምድር ኡር የሚባል ስፍራ ሲሆን ብዙ አማልክት (polytheistic) ከሚያመልኩ ቤተሰብ መካከል እንደተጠራ በኢያሱ 24፡2 እናነባለን፡፡ የስነመለኮት ምሁራን ዑር የአምልኮ ማዕከል እንደሆነ እና ዋነኛው የሱምራዊያን አምላክ "chies god" ወይን "nanna" እንደሆነ ይነግሩናል፡፡ ኡር ብርሃን "light" ወይም የጨረቃ ብርሃን "moon light" የሚል ስያሜ አላት፡፡[5]

ዘፍጥረት 12 እና ሐዋ 7፡2-4 አብርሃም በእግዚአብሔር መጠራትን የሚነግሩን የምንባብ ክፍሎች ናቸው፡፡ አብርሃም እግዚአብሔርን በመታዘዝ የወሰደው እርምጃ አብርሃምን የእምነት ጀግና እንዳስባለው የዕብራዊያን ጸሐፊ በምዕ 11፡8 ላይ በግልጽ አስቀምጦታል፡፡

ከላይ የተመለከለትናቸው ነጥቦች የአብርሃምን ጠንካራ ጎን ሲሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይጠይቅ ወይም ሳያረጋግጥ የወሰዳቸው እርምጃዎች የአብርሃምን ደካማ ጎን ያስተምሩናል፡፡

- ✷ በአገሩ ራብ በሆነ ጊዜ ወደ ግብጽ ወረደ በዚያም ስለነፍሱ ሳስቶ ሣራን እህቴ ናት /እህቱ ነኝ በይ በማለት የወሰደው እርምጃ (ዘፍ 12፡10-20)
- ✷ ሣራ የልጅ መውለድ ተስፋዋ በተሟጠጠ ጊዜ ወደ አጋር እንዲገባና ከእርሷም ልጅ እንዲወልድ ስታደፋፍረው በእሺታ መቀበሉ (ዘፍ 16)
- ✷ አብርሃም እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ በጌራራ ሰዎች ፊት ሚስቱን እህቴ ናት በማለት ስህተት ሰርቷል (ዘፍ20፡1-2)

### ሐ. የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን (ዘፍ 15 ፣ 17)

አብርሃም የእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥሪ በደረሰው ሰዓት (ዘፍ 12፡1-3) ሶስት ዋና ዋና ተስፋዎችን ተቀብሏል

- ✷ ስለ አገር የተነገረው

[5] Assad, Pentateuch: A study Guide ICI university - 2004

- ስለ ዘር (የተስፋው ዘር)
- ስለ ህዝብ የተነገረው

ይሄ ኪዳን ከዘፍ 15፡18 የታደሰ ሲሆን በዘፍ 17፡13-14 ግርዘት የኪዳኑ አንድ አካል እንዲሆን እግዚአብሔር ድንጋጌን ሰጠው። አብርሃምም እግዚአብሔር ያዘዘውን ትዕዛዝ ፈጥኖ ተግባራዊ አደረገ።

### 1.4. የአብርሃም ጥንቃቄ

***ሀ/ የአብርሃም እምነት መፈተን***

አብርሃም ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ተስፋ እንዲሁ በቀላሉ አልወረሰም። ይልቁንም ህይወቱ በብዙ መንገድ የተፈተነ ሰው እንደነበር በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ጌታ ኢየሱስ በክረስቶስ በማርቆስ 13፡13 የደቀመዛሙርት ህይወት እንደ፣ ሚፈተን ያስጠነቀቀ ሲሆን ሐዋሪያው ጴጥሮስ ደግሞ ስለ ክርስቲያኖች እምነት መፈተን እና ተያያዥ ስለሆኑ ጉዳዮች በ1ኛጴጥ 1፡6-7 ባለው ጠቃሚ ምክሮች ጽፎልናል።

በዕብራዊያን 11 የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ዓለም ስላልተገባቸው መከራ እና ፈተና (ቁጥ 38) አሰቃቂ ቢሆንም በእምነት አሸንፈውታል (ቁ 39)። አብርሃም በተወሰኑ ፈተናዎች የወደቀ ቢሆንም እግዚአብሔር ልጅህን ይስሐቅን ሰዋልኝ ሲለው በሙሉ ልብ በመታዘዝ የእምነቱን ትልቅነት አሳይቷል (ዘፍ 22)።

**ለ/ የቃል ኪዳን ፍጻሜ**

በሰው አዕምሮ ወይም አመለካከት አብርሃም የተቀበለውን ተስፋ ወይም ቃል ኪዳን ፈጽሟል ብሎ ማመን ከባድ ነው። ነገርግን የሚሳነው ነገር የሌላ እግዚአብሔር (ኤር 32፡17) የተናገረውን ሁሉ ወደ ምልዓት አምጥቶአል። ይህም በስጋ የአብርሃም ዘር የሆኑት እስራኤላዊያን እንደ ህዝብ ወይም ሀገር መመስረታቸው ብቻ ሳይሆን በዘፍ 12 እንደተገለጸው የምድር ህዝቦች የአብርሃምን በረከት ተከታዮች በመሆናቸው ነው። (ሐዋ 17፡1፣ 19፡8) ወዘተ…

ሐዋሪያው ጳውሎስ አብርሃም የተቀበላቸው ተስፋዎች በከፊል እንደተፈጸሙና "partial fulfilled" በመፈጸም ላይ ያሉ "are still being fulfilled" እንዲሁም ወደፊት የሚፈጸሙ "will be completely fulfilled" መሆናቸውን በ2ቆሮንቶስ 1፡20 ፣22 በግልጽ ይነግረናል።

### 1.5. የአብርሃም ህይወት ጠቀሜታ

ከአብርሃም ህይወት መማር የሚገባን ሶስት መሰረታዊ ነጥቦች

*ሀ. እርሱ የተስፋው ህዝብ አባት ነው*

- እስራኤላዊያን የተደሰቱበት በረከትና ተስፋ ለአብርሃም የተገባ ነበር
- እስራኤላዊያን አህዛብ በብሉይ ኪዳን ዘመን እንኳ ቢሆን የተባረኩት በእርሱ በኩል ነበር። (ተስፋው አህዛብ በአንተ ይባረካሉ ይላልና)

ለ. አብርሃም በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ወደ እግዚአብሔር ለሚመጡት አማኞች ሁሉ አባት ነው፡፡ በመሆኑም እኛ በእምነት በኩል ለአብርሃም ልጆቹ ነን (ገላ 4)

ሐ. ለእኛ ትምህርት ሊሆነን የሚችል ብዙ ምሳሌያዊ ህይወት ያለው ሰው ነው፡፡

- የእምነት ቀዳሚ ወይም ፋና ወጊ ነው፡፡
- የእርሱ መታዘዝ መሰጠትና ጽናት ለእኛ መነቃቃት እና ተነሳሽነትን የሚፈጥሩ ነገሮች ናቸው፡፡
- በእግዚአብሔር መመራትን ከእርሱ ልንማረው የሚገባን ሌላኛው የህይወቱ መገለጫ ነው፡፡

**ለግንዛቤ፡- ዕምነት**፡ የብሉይ ኪዳን ስነ መለኮት ዋና ክፍል መሆኑን መገንዘብ መልካም ነው፡፡

በመጨረሻም የአብርሃምን የህይወት ድምዳሜ እግዚአብሔር ለይስሐቅ በተገለጠለት ጊዜ እንዲህ ብሎለታል «አብርሃም ቃሌን ሰምቶአልና ፍርዴን ትዕዛዜን ሥርዓቴንም ጠብቆአል» (ዘፍ 26፡5)፡፡

የአብርሃም ህይወት በመውጣት መውረድ የታጀበ ቢሆንም እንኳ ስለአጠቃላይ የህይወት ጉዞው በእግዚአብሔር የተሰጠው ምስክርነት እጅግ አስደሳች ብቻ ሳይሆን እኛም በመንፈሳዊ ጉዞአችን ከውጣ ውረዶቻችን ጎን ለጎን እግዚአብሔርን አስከብረን ማለፍ እንዳለብን አመላካች ነው፡፡

# ትምህርት ሰባት

## ይስሐቅና ያዕቆብ

### 7.1 የይስሐቅና የያዕቆብ ትውልድ

ይስሐቅና ያዕቆብ በቀጣይነት ለሚመጣው የተስፋው ህዝብ አባቶች ናቸው፡፡ ታሪካቸው አንዱ ከአንዱ ጋር ተያያዥነት ያለው በመሆኑ በአንዱ ላይ እናጠናዋለን፡፡ ታሪካቸው ውስብብስ ያለ አይደለም፡፡ ይልቁንም የማንነታቸውን የታሪክ ቅደም ተከተል በምዕራፎቹ ውስጥ እናያለን፡፡

**ይስሐቅ (ዘፍ 25፡19- ዘፍ 35)**

1. ይስሐቅና ቤተሰቦቹ
2. ያለፈባቸው ችግሮች

**ያዕቆብ (ዘፍ 37፡50)**

1. ያዕቆብ በአባቱ ቤት
2. ያዕቆብ በላባ ቤት
3. ያዕቆብ ወደ ቤተል መመለስ

**የይስሐቅን አጠቃላይ ሁኔታ የሚያሳይ ሰንጠረዥ(ዘፍ 25፡19- ዘፍ 35)**

| የይስሐቅ አጠቃላይ ታሪክ | | |
|---|---|---|
| ያለፈባቸው ሁኔታዎች | የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል | እድሜው |
| ውልደቱ | ዘፍ 21 ፡1-3 | - |
| መስዋዕት እንዲደረግ የታዘዘበት | 22፡1-6 | 25 |
| የእናቱ የሣራ ሞት | 23፡1-2 (ከ17፡17 ጋር አነጻጽር) | 37 |
| ርብቃን ያገባበት | 25፡20 | 40 |
| የኤሳውና የያዕቆብ መወለድ | 25፡25-26 | 60 |
| የአባቱ የአብርሃም ሞት | 25፡7(ከ21፡5 ጋር አነጻጽር) | 75 |
| የያዕቆብ ወደ አጎቱ ቤት መሰደድ | 28፡5 | 137 |
| የልጅ ልጁ የዮሴፍ መወለድ | 30፡22-31፣ 31፡ 41 | 151 |
| የዮሴፍ ወደ ግብጽ መሸጥ | 37፡2 እና 28 | 168 |
| ሞቱ | 35፡28-29 | 180 |

ሰንጠረዥ 5

በቅድመ አባቶች ዘመን የምናገኛቸው ትውልድ ለሚመጣው የተስፋ ወይም የተመረጠ ህዝብ ስፍራውን አንድ በአንድ በመልቀቅ ከመንገድ ወጥተው አሁን የምናገኘው የተስፋ ዘር የሚመጣበት የትውልድ ሐረግ ነው፡፡

በአብርሃም በኩል ሊመጣ ያለው የተስፋው ዘር የመጀመሪያው ወራሽ የሆነው የይስሐቅ ታሪክ ትኩረት ሰጥተን እናጠናዋለን፡፡ ይህ የአብርሃም ልጅ እና የያዕቆብ አባት የሆነው ይስሐቅ ከሁለቱም ባነሰ መልኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ስሙ ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ ይህ ማለት ግን ይስሐቅ በተስፋው ዘር ያለው ስፍራ አናሳ ነው ማለት አይደለም፡፡

እንዲሁም አብርሃም ከአጋር ለወለደው ልጁ ለእስማኤል የተሰጠው ጥቂት ስፍራ የጸሐፊው የትኩረት አቅጣጫ ወዴት እያዘነበለ እንደሆነ አመለካች ነው (ዘፍ 25፡ 12-18)፡፡ የዘፍጥረት ጸሐፊ ብዙም ትኩረት ባልሰጠው ሁኔታ ተገልጦ ስላለ እኛም ብዙ ማለት አንችልም፡፡ ይሁን እንጂ የእስማኤላዊያን የአስራ ሁለቱ ነገድ አባት መሆኑንና አስምረንበት ማለፍ እንችላለን፡፡

በሌላ በኩል እግዚአብሔር ለእስማኤል የተስፋ ቃል ሲገባለት ስናይ ለይስሐቅ ማለትም ለተስፋው ዘር የተገባው ቃል ኪዳን ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

### 7.2 ይስሐቅና ቤተሰቡ

ይስሐቅ ገና ርብቃን ባገባ ማግስት የገጠመው ተግዳሮት ቀላል አልነበረም፡፡

የመጀመሪያው ተግዳሮት የርብቃ ልጅ አለመውለድ (መሃንነት) ነበር፡፡ ይህ ለይስሐቅ አዲስ ልምምድ አልነበረም እርሱ ራሱ የተወለደው ከሃያ አምስት ዓመታት ጥበቃ በኋላ ነበር፡፡ ይስሐቅም የእናቱን የሞተ ሰውነት ህያው ወደ አደረገውና በእርጅናና ተስፋ በተቆረጠ ሰዓት እርሱን ወደ ሰጣት አምላክ ጉዳዩን ያቀርባል፡፡ ይህም ለአንድ እግዚአብሔርን ለሚያመልክ ሰው አማራጭ የሌለው የመጨረሻ መንገድ ነው፡፡

ቀጣዩ ተግዳሮት ደግሞ እግዚአብሔርም ልመናውን ሰምቶ ርብቃም በጸነሰች ጊዜ ልጆቿ በማህጸኗ ይገፋፉ ነበር፡፡ ይህም የሁለቱ ጠብ በማኅጠን ስለመጀመሩ አመላካች ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ይስሐቅ ሳይሆን ርብቃ ነበረች እንግዳ ስለሆነው እርግዝና ለእግዚአብሔር ለመናገር የሄደቸው፡፡ ይስሐቅና ርብቃ ከልጆቻቸው ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ስናይ (ዘፍ 25፡23) እግዚአብሔር ለርብቃ ልጆቿ ወደፊት የሚሆኑትን ሲነግራት ምናልባት ይስሐቅ በስፍራው አብሯት እንዳልነበረ ያመላክታል፡፡ የወላጆቻቸው አድልዎ አንዳቸው ለአንዳቸው የነበራቸው ለየት ያለ እንክብካቤ ይህንን አመለካከት ያጠናክራል፡፡

ይስሐቅ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃልኪዳን ለማይገባው ሰው ለኤሳው ለማስተላለፍ የወሰደውን እርምጃ በተመለከተች ጊዜ ርብቃም በይስሐቅ ስህተት ማዘኗ አልቀረም፡፡ ስለዚህ የራሷን አማራጭ ለመውሰድ ተገደደች፡፡

**ይስሐቅ ቢያንስ ሁለት ነገሮችን ልብ ማለት ነበረበት**

1. ትንቢቱ የመጣው ልጆቹ በእናታቸው ማህጸን ሳሉ መሆኑን
2. የእግዚአብሔር በሆነው ነገር ላይ የተገለጠውን የኤሳው ባህሪይ፡፡ ይህም ኤሳው ለቤተሰቦቹ ሐዘን እንዲሁም በእግዚአብሔር ፊት መልካም ያልሆነ ጋብቻ ከሄታይት ሴቶች ሁለት ሚስቶችን ማግባቱን ልብ እንበል፡፡ ይህም አብርሃም ለልጁ ለይስሐቅ ሚስት እንዲያመጣለት ታማኝ ባሪያውን በላከው ጊዜ የተናገረውን ይጻረራል (ዘፍ 24፡3፣ ዘፍ 28፡9)

ይስሐቅ ለቤተሰብ ራስ እንደመሆኑ ሃላፊነቱን በአግባቡ አልተወጣም፡፡ ለምሳሌ

1. ለአንደኛው ልጅ በማዳላት ለሌላኛው ትኩረት አይሰጥም ነበር (25፡28)

2. ልዩነቶቹ እንደተጠበቁ ሁነው ስለ ልጆቹ ባህርይ ከሚስቱ ጋር በግልጽ ሊወያይ ይገባ ነበር
3. ኤሳውን እግዚአብሔርን ለመምሰል እንዲችልና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ጋብቻ እንዲመሰርት ሊመክረውና ሊረዳው ይገባ ነበር።
4. ኤሳውን ስለሚወደው ብቻ የአብርሃምን ቃልኪዳን ለኤሳው ሊያስተላልፍ መነሳት አይገባውም ነበር።

### 7.3 ይስሐቅ የተጋፈጣቸው ተግዳሮቶች (Challenges)

በውስጥ ከሚገጥመው ችግር ሌላ

- ሚስቱን ለመውሰድ ሰዎች በተነሱ ጊዜ የገጠመውና እርሱም እንደ አባቱ እንደ አብርሃም ለራሱ ነፍስ በመሳሳት ዋሽቶ እህቴ ናት እስኪል የደረሰበትና እምነቱም ምን ያህል እንደሆነ የተፈተነበት የመጀመሪያው ተግዳሮት ነው። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ምህረቱን በማግነን ለአባቱ እንዳደረገው ለእርሱም ሲያደርግ እናያለን። (ዘፍ 26፡1-11)
- ሐገሩ ከነዓን ለቅቆ ወደ ግብጽ እንዲሰደድ ያደረገው ረሃብ ሌላኛው ፈተና ነው። እግዚአብሔርም በምድሪቱ እንዲቀመጥ አዘዘው እርሻውንም ባረከለት። (ዘፍ 26)
- በውሃ ጉድጓድ ምክንያት ከፍልስጥኤማዊያን ጋር የገጠመው አለመግባባት ሌላኛው ችግር ነው። በመጨረሻም በቤርሳቤህ የውሃ ጉድጓድን ቆፍረ ውሃም አገኘ ስሙንም ‹‹ርሆቦት›› ብሎ ጠራው። ርሆቦት ማለት ሰፊ ስፍራዎች ማለት ሲሆን ይስሐቅም ከሁኔታው በመነሳት ትንቢታዊ ቃል ይናገራል እንዲህ ሲል አሁን እግዚአብሔር አሰፋልን በምድርም እንበዛለን (ዘፍ 26፡22)። በዚህም ስፍራ (በቤርሳቤህ) እግዚአብሔር ተገልጦለት ለአብርሃም የገባለትን ቃል ኪዳን እንደገና አጸናለት። (26፡23-25)

### 7.4 ያዕቆብ (ዘፍ 27፡1-35፡27)

ያዕቆብ የኤሳው ብቸኛው ታናሽ ወንድም የበረከት እና የብኩርና መብት ፈላጊ (blessing and birth right seeker) በመሆኑ ይታወቃል። ይህንንም ለመሳካት ማድረግ የሚገባውን ሁሉ ከመፈጸም አልተመለሰም። ይህንንም ትገባሩን በአባቱ እና በወንድሙ ላይ ባሰየው ያልተገባ ሁኔታ መረዳት ይቻላል።

ያዕቆብ በአታላይነቱና በፈጣን አዕምሮውም (የነገሮችን አካሔድ በማየት መፍትሔ በመፈለግ) ይታወቃል። ከእናቱ ጋር በመተባበር ከአባቱ ከይስሐቅ የውርስ መብቱንና የአብርሃምን የቃልኪዳን በረከት ወስዷል።

**ሀ. የያዕቆብ ስደት**

**ያዕቆብ ወደ ሀራን የተሰደደበት ሁለት ምክንያቶች**

1. ከአጎቱ ከላባ ሴት ልጆች ሚስትን ለራሱ ለመውሰድ

2. ከወንድሙ ከኤሳው የመግደል ዛቻ ለማምለጥና ለመደበቅ

**ለ. ያዕቆብ በቤቴል (ዘፍ 28፡10-22)**

ያዕቆብ የአባቱ መኖሪያ ወደ ሆነችው ወደ ሃራን ሲጓዝ በነበረበት የብቸኝነት ጉዞ ሎዛ ተብላ በምትጠራ ስፍራ እግዚአብሔር ሌሊት በራዕይ ተገለጠለት፡፡ ያዕቆብም የዚያን ስፍራ ስም ይህስ የእግዚአብሔር ቤት ነው ሲል 'ቤተል' ብሎ ጠራው፡፡ እግዚአብሔርንም አመሰገነ፡፡ ስዕለትም ተሳለ፡፡ በቤቴል የነበረው መንፈሳዊ ልምምድ የእግዚአብሔርን ከእርሱ ጋር መሆን ነቅቶ እንዲከታተል አድርጎታል፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መሆን የአብርሃምን ቃልኪዳን (የተስፋ ዘር) ህጋዊ ወራሽ ከእርሱ ስለመውጣቱ ትልቅ ማረጋገጫ ነው፡፡ ያዕቆብ በቤቴል ያየው ህልም አስደናቂውን የእግዚአብሔርን ህልውና ወይም መገኘት ከመረዳቱ ባሻገር ቤቴል የእግዚአብሔር የአምልኮ ስፍራ (መቅደስ) እስኪሆን ደርሷል፡፡ እግዚአብሔር የተገለጠለት ለአብርሃምና ለይስሐቅ አስቀድሞ በተገለጠላቸው ሁኔታ ነበር (ቁጥ13)፡፡ በቃልኪዳት ህብረት አምላካቸው ሆኗል (ዕብ 11፡16) ለአብርሃም የተነገረውን በዘፍ 15 እና 17 እናገኛለን፡፡

**ሐ. ያዕቆብ በላባ ቤት**

ያዕቆብ በላባ ቤት በቆየበት ቆያታ ለባህሪዩ መስተካከልና ለመንፈሳዊ ህይወቱ እድገት እንዲሁም ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ መተማመኛ ወይም መመኪያ እንዳይኖረው አድርጎታል፡፡ ያዕቆብም ሆነ ላባ ጥበበኞች ነበሩ፡፡ ይሁንና በእያንዳንዱ ሂደት ውስጥ እግዚአብሔር ያዕቆብን ሲረዳው ይታያል፡፡ የያዕቆብና የላባ የአብሮነት ዘመን ምንም እንኳን ጅማሬው ላይ መላካም የነበረ ቢሆንም በኂላ ላይ ግን ሁኔታው በመለወጡ ላባን ሳይሰናበት ኮብልሎ እስከመሄድ አድርሶታል፡፡ ያዕቆብ የአጎቱን የላባን ቤት ለቅቆ ከመውጣቱ በፊት ሁለቱን የላባን ልጆች እና ደንገጡሮቻቸውን በማግባት ልጆችን ወልዶ እና በከብትና በሐብት በልጽጎ ነበር፡፡

**መ. እግዚአብሔርም ለያዕቆብ፡- (ዘፍ 28፡31)**

- ተገለጠለት
- በላባ ቤት በኖረበት ዓመታት ሁሉ መንፈሳዊ ህይወቱ እንዲያድግ አደረገው
- በምድራዊ ባርኮት አበለጸገው (29፡31-30፡24)

**ሠ. የያዕቆብ ወደ ከነዓን መመለስ (ዘፍ 31፡9-16)**

ያዕቆብ ወደ ከነዓን እንዲመለስ የረዳው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ መለኮታዊ ምሪት እንዲያገኝ ያስቻሉት ሦስት ነጥቦች ናቸው፡፡ እንርሱም፡-

ሀ/ የውስጥ መሻት (እግዚአብሔር ለማምለክ)

ለ/ ከላባ ጋር አለመግባባት መፈጠሩ

ሐ/ የእግዚአብሔር ቃል እና ራዕይ (ቀደም ሲል የተቀበለው የተስፋ ቃል እና ራዕይ) መሆናቸውን ፓውል ቢ. ሆፍ የተባሉ የስነ መለኮት ምሁር አበክራው ያስተምራሉ፡፡[6]

[6]Paul B. Hoff. Gnesis. An Independent Study Textbook Global Univrisity. 1999, p.255

### ረ. ብርቱ ጸሎት ማድረጉና ከኤሳው ጋር መገናኘቱ (ዘፍ 32፡1፣ 33፡17)

ይህ ክፍል የያዕቆብን የህይወት አቅጣጫ ስለለወጠው ታሪክ ይነግረናል፡፡ ይሁንና ጊዜው ከመቼውም በላይ ለያዕቆብ አስፈሪ ነበር፡፡ ምክንያቱም

1ኛ. ለረጅም ጊዜ ተሸሽጎበት ከነበረውና የብዙ ልጆችና ሃብት ባለቤት ከሆነበት ከአጎቱ ከላባ ጋር ጥሩ ባልሆነ ሁኔታ ተለያይቷል፡፡ ይህም የእርሱን ወዳጅነትና ቅን እርዳታ አሳጥቶታል፡፡

2ኛ. ለሞት ሲፈልገው የነበረውና ሸሽቶ ያመለጠው ወንድሙ ኤሳው ከፊት ለፊት እየመጣና ሊገናኘው እንደሆነ ተረድቷል፡፡ ኤሳው ደግሞ ሊበቀለው የማይችልበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ ይህን ማለት የሚያስችለን በቃየን ልብ የነበረውን የነበረውን ቂምና በቀል የሚያስወግድ ምንም አይነት መሃከለኛ ታሪክ ከዘፍጥረት መጽሐፍ ስለማናገኝ ነው፡፡

በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ያዕቆብ የነበረው አማራጭ እንደቀድሞው በብልጠት ከሁኔታዎች ማምለጥ አልነበረም፡፡ አንደኛው ምንም ምክንያት ሊያድነው እንደማይችል ተረድቷል ሁለተኛው መንፈሳዊ ህይወቱም ሆነ ባህሪዩ እንደቀድሞ አልነበረም፡፡

ስለዚህም እግዚአብሔር በሰጠው የመጨረሻ እድል በመጠቀም ወደ እርሱ ጮኸ፡፡ ይህም የሚያሳየን ከላይ እንዳየነው ያዕቆብ በጉልበቱ ፍሬ እና ሀብት የተባረከ ቢሆንም ገና ያልተቋጨ ነገር እንደነበረ ነው፡፡ ይኸውም «መለኮታዊ በረከት ከቃል ኪዳኑ ጋር ፊት ለፊት የሚያገናኘው በረከት» ነው፡፡ እግዚአብሔርም በዚያ ስፍራ ባረከው ስሙንም ለወጠ፡፡ የስሙ መለወጥና የባርኮት ቃል ለያዕቆብ የአዲስ ህይወት መጀመሪያ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ምክንያቱም የመንፈሳዊ ባርኮት ውጤቱ ከሚፈራው ሞትም ሊያስመልጠው ችሏልና ነው፡፡

በዘፍጥረት 32፡1 እግዚአብሔር መልዓኩን ልኮ መለኮታዊ እርዳታ እንዲበዛለት ከማድረጉ በላይ በዚሁ ምዕራፍ ከቁጥር 24-32 ደግሞ ራሱን ገልጦለት ያዕቆብን ባርኮታል፡፡ ይህም ባርኮት በያዕቆብ ህይወት ላይ ለውጦችን አምጥቷል፡፡ እግዚአብሔር ያዕቆብን በባረከው ስፍራ ወደ ቤተል እንዲመለስ ይነግረውና በዚያም ስፍራ ይባርከዋል ቃልኪዳኑንም ያድስለታል፡፡ ያዕቆብም በዚያ ስፍራ መሰዊያ ሰራ የእግዚአብሔርንም ሰም ጠራ (ዘፍ 35፡9-12)፡፡

### ሸ. የያዕቆብ ወደ ቤተል መመለስ (33፡18-35፡18)

የምዕራብ 33 የመጨረሻዎቹ ቁጥሮች እና 34ኛው ምዕራፍ በሙሉ የያዕቆብ እና የቤተሰቡ ኪሳራ የተዘገበባቸው የምንባብ ክፍሎች ናቸው፡፡ ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር እንግዶችን አማልክት በሴኬም እንዲቀብራቸውና ወደ ቤተል እንዲሄድ አዘዘው፡፡ ያዕቆብ እንግዶችን አማልክት በሴኬም ቀበራቸው ቤተሰቡንም ከርኩሰት አነጻ በመጨረሻም ወደ ቤቴል ተጓዘ፡፡

# ትምህርት ስምንት

## የዮሴፍ ታሪክ  የዘፍጥረት መጽሐፍ መደምደሚያ

### 8.1. የሕይወቱ አጀማመር እና ፍጻሜ

ይህ ወቅት የተስፋው ዘር ምርጥ ህዝቦች ወደ ትክክኛው ምዕራፍ እየመጡ ያለበት ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ለአስራ ሁለቱ የተመረጡ ነገዶች አባቶች የሚሆኑ አስራ ሁለቱ ልጆች ለያዕቆብ ተወልደውለታል፡፡ የያዕቆብ ዋናው ታሪክ በምዕራፍ 35 በቤተል መሰዊያን አዘጋጅቶ የአምላኩን የእግዚአብሔርን ስም በጠራ ጊዜ ተቋጭቷል፡፡ የዘፍጥረት ጸሐፊ በምዕራፍ 36 ስለ ኤዶማዊው ኤሳው ዝርያዎች የትውልድ ታሪክ ያስነብበናል፡፡ የዘፍጥረት መጽ ሐፍና   የመጽሐፍ   ቅዱስ አጠቃላይ ታሪክ በተመረጡት ትውልድ ላይ የሚያተኩር እንደመሆኑ የዘፍጥረት ጸሐፊ የኤሳውን ታሪክ ወደ ጎን በመተው ወደ ዋናው ሐሳብ ማለትም ወደ ተመረጡት ትውልድ ታሪክ መናገር ይቀጥላል፡፡

የአዳኙ ኢየሱስ ክርስቶስም የሚመጣው ከያዕቆብ አራተኛው ልጅ ከይሁዳ ነገድ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በዚሁ በይሁዳ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ለአብርሃም በተናገረው የትንቢት ቃል መሰረት (ዘፍ 15፡15-16) ለአራት መቶ አመታት ወደ ግብጽ የመውረጃው መንገድ ይከፈታል፡፡

ከዚህ በኋላ የምናገኘው በዚህ የትንቢት ፍጻሜ ውስጥ ከፍተኛውን ስፍራ የሚያዘውን የዮሴፍን ታሪክ ነው፡፡

ሀ/ ከቤተሰቡ ጋር ዮሴፍ የተወለደው በዘፍ 30፡24-25 ሲሆን ስለ አስተዳደጉ ብዙ የተገለጸ ነገር አናገኝም፡፡ ይሁንና አባቱ የሚወደውና ወደ እረኝነትም ከወንድሞቹ ጋር እንደማይልከው ስናይ በጥንቃቄ እንዳሳደገው እንረዳለን፡፡ በዘፍ 37፡2 እግዚአብሔር ለአገልግሎት ሲለየው እናያልን፡፡

ለ/ ወደ ግብጽ መሸጡ (ዘፍ 37፡28-36)

ሐ/ ዮሴፍ በጴጢፋራ ቤት (ዘፍ 39፡1-20)

መ/ በወህኒ ቤት (39፡21-40፡23)

ሠ/ በፈርዖን ቤተመንግስት መሾሙ (ዘፍ 41)

ረ/ ከወንድሞቹ ጋር መገናኘቱ (42-49)

ሰ/ የህይወቱ ማብቂያ (50)

### 8.2. ዮሴፍ በአባቱ ቤት

ዩሴፍ ታሪክ የሚጀምረው በዘፍጥረት 37፡2 ላይ ገና የ17 ዓመት ወጣት እያለ ነው፡፡ ዮሴፍ በአባቱ የተወደደ ልጅ ቢሆንም በወንድሞቹ ግን የተጠላ ነበር፡፡

ዮሴፍ በወንድሞቹ የተጠላበት ሶስት ምክንያቶች

- በአባቱ ፊት ያገኘው ሞገስና እንክብካቤ ( ዘፍ 37፡3-4)
- ስለወንድሞቹ መልካም ያልሆነ ስነምግባር ለአባቱ ያመጣው ወሬ ( 37፡2)
- ከህልሞቹ የተነሳ (37፡5-11)

በጥላቻቸውም ምክንያት ዮሴፍን ለማስወገድ የቀረቡ አማራጮች

1. ገድሎ በማስወገድ ለአባቱ መርዶ ማድረስ (ዘፍ 37፡20)
2. በጉድጓድ ውስጥ በመጣል በረሃብ ተሰቃይቶ እንዲሞት ማድረግ (37፡23-24)
3. ለእስማኤላዊያን ባሪያ እንዲሆን መሸጥ (ዘፍ 37፡26-28)

የያዕቆብ ልጆች በአባታቸውና በወንድማቸው ዮሴፍ ላይ በሳዩት ያልተገባ ባህሪይና በሴኬም ሰዎች ላይ ባደረሱት የበቀል ጥፋት መንፈሳዊ ህይወታቸው በምን ደረጃ እንደነበር መረዳት ይቻላል፡፡ በያዕቆብ ሚስቶችም መካከል የነበረውን ፍቅር ማጣት ስናይ የያቆብን ቤት መንፈሳዊ ህይወት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ ያደርገዋል፡፡

ዮሴፍ በአባቱ ቤት በክብርና በፍቅር እንዲሁም በግብጽ እንደባሪያ ያለፈባቸው ሁለቱ መንገዶች ፈጽሞ የማይገናኙና የየራሳቸው የሆነ የተለየ ባህሪይ ያላቸው ናቸው፡፡ ይህንን ሁኔታ መቀበል በራሱ ለዮሴፍ ቀላል አልነበረም፡፡

ዮሴፍ ወደ ግብጽ ከተሸጠ በኋላ ያጋጠመውንና ያለፈበት መንገድ ስናጠና እግዚአብሔር ሁለቱንም ማለትም ዮሴፍንም ሆነ ወንድሞቹን አስተምሯቸዋል፡፡

- ዮሴፍ ይቅር ብሎ መቀበልን ሲማር
- መጸጸትንና ንስሐ መግባትን ተምረዋል

**8.3 የይሁዳ የስነምግባር ሁኔታ (ዘፍ 38)**

ይህ ምዕራፍ የሚተርከው የያዕቆብን ልጅ የይሁዳ አጭር ታሪክ ነው፡፡ ጸሐፊው የሞራል ውድቀት ያለበትን ይሁዳንና የሞራል ጥንካሬ የሚታይበትን ዮሴፍን እያነጻጸረ ይመስላል፡፡ ይህንንም ዮሴፍ በጲጥፋራ ሚስት ተደጋጋሚ የማማለያ ጥያቄ እንደቀረበለትና እምቢ እንዳለ ይሁዳ ደግሞ ወደ ጋለሞታይቱ ሴት ለመግባት በቀላሉ መሳቡን በማተት በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት የሚጥር ይመስላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ እስራኤላዊያን ወደ ግብጽ በመሄድ ፈንታ በዚህ ምድር ቢኖሩ ኑሮ ምን ሊሆን እንደሚችል ግንዛቤ እናገኛለን፡፡ ይኸውም እስራኤላዊያን በከነዓናዊያን ክፉ ባህልና ጣዖት አምልኮ እንደሚበረዙና የከነዓናዊያንንም ሚስቶች ለራሳቸው በመውሰድ የተስፋውን ዘር ሊያበላሹት ይችሉ ነበር፡፡

ትዕማር የፋሬስ እናት በክርስቶስ የዘር ሐረግ መግባቷ ደግሞ ሌላኛው የእግዚአብሔርን ጸጋና ምህረት የተገለጠበት አስደናቂ ታሪክ ነው፡፡ በሮሜ 5፡20-21 ላይ «በደልም እንዲበዛ ሕግ ጭምር ገባ፤ ዳሩ ግን ኃጢአት በበዛበት፥ ኃጢአት በሞት እንደ ነገሠ፥ እንዲሁ ደግሞ ጸጋ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ በጽድቅ ምክንያት ለዘላለም ሕይወት ይነግሥ ዘንድ፥ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ» ይላል፡፡

የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል መጀመሪያ በሆነው በአብርሃምና የተስፋው ዘር ፍጻሜ በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ የዘር ሐረግ ውስጥ የይሁዳና የትዕማር መግባት የሚያሳየው የጸጋውን የምህረቱን ብርታት ብቻ ነው። ይህም የሚያሳየን የኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሃረግ ንጹህ አይሁድ ብቻ አለመሆኑን ነው። አይሁድ ያልሆኑ ግለሰቦችም በዚህ የዘር ሃረግ ውስጥ ገብተዋልና። ረዓብ፣ ሩት እና፣ የኦሪዮ ሚስት ሌሎቹ በክርስቶስ የዘር ሃረግ የተካተቱ አህዛብ ሴቶች ናቸው። (ማቴ 1፡5-6)

### 8.4 ዮሴፍ በግብጽ ሐገር በፈርኦን ቤት

ዮሴፍ ጲጥፋራ ቤት በነበረበት ጊዜ

- የሞራል ሕይወቱ የተፈተነበት ነበር
- ለእግዚአብሔር የነበረው ታማኝነት በግልጽ የታየውም እዚህ ነበር
- ዮሴፍ ተፈተነ ነገር ግን ራሱን ለተፈተነበነት ሐጢአት ከመስተት ይልቅ እግዚአብሔርን በመፍራትና በማክበር አለፈው።

የሰውን ትክክለኛ ባህሪ ለመግለጥ ፈተና ትክክለኛው መንገድ ሊሆን ይችላል። ልክ እንደ ዮሴፍ ሁሉ እግዚአብሔር ከፈቀደ ክርስቲያኖችም ይፈተናሉ በመከራም ያልፋሉ። የዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ካለው መለኮታዊ ፈቃዱና አላማው አንጻር በቅዱሳኑ ህይወት መከራና ፈተና እንዲመጣ ሊያደርግ ይችላል። አንድ ግልጽ መሆን የሚገባ እውነት ቢኖር አፍቃሪውና መሃሪው እግዚአብሔር የሚሻልና መልካም አላማ ከሌላው አንዳችን ነገር ወደ ህዝቡ እንዲመጣ እንደማይፈልግ እና እንደማይፈቅድ ነው።

ከፈርያን ቤት በተጨማሪ የእስር ቤቱ ቆይታ ለዮሴፍ ሌላኛው ትምህርት ቤት ነው። ምንም እንኳን በእስር ቤት የነበረው በሐሰት ክስ ቢሆንም መለኮታዊ ፈቃድ እንደነበረበት ግልጽ ነው። ለዚህም ማረጋገጫ የሚሆነን እና ጥሩ ስሜት የሚፈጥርልን ሀረግ «እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ፥ ሥራውም የተከናወነለት ሰው ሆነ በግብፃዊው ጌታውም ቤት ነበረ።» የሚለው ነው።

በእስር ቤት ቆይታውም ከፈተናው ባሻገር ሶስት መልካም የሆኑ ነገሮችም ገጥመውታል

- የፈርኦንን አገልጋዮች ይገናኛቸዋል ከእነርሱም አንዱ ለዮሴፍ ወደ ቤተመንግስት መግቢያ በር ሆኖታል
- እውነተኛ ባለአደራነትንና መሪነትን ተምሮበታል። የእስር ቤት አለቃ ሆኑ ማገልገሉን ልብ እንበል
- የህልም መፍታት ስጦታውንም ለመለማመድ ጠቅሞታል። መንፈሳዊ እድገት ያገኘበት ስፍራም መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

### 8.5. የዮሴፍ ስልጣን በግብጽ ሁሉ ላይ

ከብዙ ዓመታት የእስር ቤት ቆያታና መከራ በኋላ ዮሴፍ የግብጽን ኢኮኖሚ ለመምራት እድል አግኝቷል። በሮሜ 8፡28 እንደምናየው «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደአሳቡም ለተጠሩት

ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» የሚለው ቃል በዮሴፍ ህይወት ፍጻሜ እንዳገኘም እናይለን፡፡

በብዙ መከራና ስቃይ በማለፍ እግዚአብሔርን መምሰል የተማረ እና ጥበብን ያገኘ እንደመሆኑ መጠን በዚያ አስቸጋሪ ጊዜ ሰውን ለማዳንና ምፍትሔ ለመሆን የተገኘ ብቸኛው ሰው አድርጎታል፡፡

በተጨማሪም ለህልሞቹ ፍጻሜ የማግኛ ጊዜው እንደደረሰ አመላካች ነው፡፡ ይሁንና የህልሙ ፍጻሜ እርሱ ከጠበቀው በላይ ነበር የሆነው፡፡ በዘፍትረት 41፡43 ላይ የእርሱም በምትሆን በሁለተኛይቱ ሰረገላ አስቀመጠው፥ አዋጅ ነጋሪም፡፡ ስገዱ እያለ በፊት በፊቱ ይጮኽ ነበር እርሱም በግብፅ ምድር ሁሉ ላይ ተሾመ፡፡» ምንም እንኳን ዮሴፍ በልየ ልዩ ተግዳሮቶች መካከል ቢያልፍም እግዚአብሔር የተናገረው መልዕክቶች እንዴት ፍጻሜ እንዳገኙ እናያለን፡፡

## 8.6. ከወንድሞቹ ጋር የተደረገ እርቅ

ከዘፍጥረት 42-45 ባለው ክፍል ዮሴፍ ከወንድሞቹ ጋር ለመታረቅ የሔዳቸውን ሂደቶች ነው፡፡ አንዳንድ ምሁራን ዮሴፍ የመጀመሪያዎቹን የመንደርደሪያ ሃሳቦች እርምጃዎች የወሰደው እነርሱ ያደረሱበትን ክፋት በማሰብ የወሰዳቸው ናቸው ሲሉ ሌሎች ከእናቱ ልጅ ከወንድሙ ቢኒያምና ከአባቱ ከያዕቆብ ጋር ያለው ግንኙነት እንዳይቋረጥ ያደረገው ስልት ነው፡፡ ይህንን የሚያረጋግጥልን ከወንድሞቹ የወንድሙንና የአባቱን ደህንነት ከሰማ በኂላ ያደረጋቸው ሁኔታዎች የበቀል ሳይሆኑ የጥበብ እርምጃዎች መሆናቸው ነው፡፡ በተጨማሪም ዮሴፍ እንዲህ ያደረገው የወንድሞቹ ባህሪይ መለወጡን ለማረጋገጥም ነው ይላሉ፡፡

በመጨረሻም እርስ በርሳቸው ምን ይህል እንደሚዋደዱ፣ ለአባታቸውም ያላቸውን ፍቅርና እንክብካቤ ሲረዳ ራሱን በመግለጥ የእርቅ ጊዜ ያደርጋል፡፡

ዮሴፍ ወንድሞቹን ይቅር በማለት ትክክለኛውን የክርስትና ባህሪይ ያሳያል፡፡ የሸጡትንና እንዲያውም ለመግደል አስበው የነበሩትን ወንድሞቹን ይቅር በማለት ክርስቶስን መስሏል፡፡

ይሁንና ግን የዮሴፍ ወንድሞች የዮሴፍን ይቅርታ በሙሉ ልብ እንዳልተቀበሉት የሚያሳይ ሐሳብ በዘፍጥረት 50 ላይ እናገኛለን፡፡ አባታቸው ያዕቆብ ከሞተ በኂላ ዮሴፍ ይበቀለን ይሆንን እያሉ ሲሰጉ ይታያል፡፡ ይህም

**አንደኛ**፡ በዮሴፍ ይቅርታ አለመተማመናቸውን አመላካች ነው

**ሁለተኛ**፡- ምንም እንኳን ዮሴፍ ከልቡ ይቅር ያላቸው ቢሆንም የበደለኝነት ስሜት ገና እንዳልለቀቃቸው ያመለክታል፡፡

## 8.7. ያዕቆብ በግብጽ ከዮሴፍ ጋር

ዮሴፍ ከወንድሞቹ ጋር ዕርቅ ካደረገ በኂላ ለአባቱ ለያዕቆብ ሰረገላ በመላክ አባቱ ወደ እርሱ እንዲመጣ ያደርጋል፡፡ ከዘፍጥረት 46-50 ያለውም ክፍል ለያዕቆብ የ70 ዓመታት የግብጽ ቆይታ ተሰጥቷል፡፡ ያዕቆብ ለልጆቹ የአብርሃምን የቃልኪዳን በረከት ያስተላለፈበት የታሪኩን ዋና ክፍል

በምዕራፍ 49 እናገኛለን፡፡ እነዚህም የያዕቆብ 12 ልጆች ህዝበ እስራኤል፣ የተመረጠ ህዝብ በመባል በብሉይ ኪዳን ይታወቃሉ፡፡

ምንም እንኳን ረጅም በረከት ለዮሴፍ የተነገረው ቢሆንም ከመሲሁ ጋር የተገናኘው በረከት ግን ለይሁዳ ነው የተነገረው (49፡10)፡፡ ዮሴፍ በሞራል ሕይወቱም ሆነ በመንፈሳዊነት ከይሁዳ ቢሻልም የመሲሁ የመምጫ የዘር ግንድ ይሁዳ ሆኗል፡፡ ይህም የእግዚአብሔርን ጸጋና ምህረት እንጂ የሰውን ተገቢነት ወይም «የሚሻል» መሆን አያሳይም፡፡

ዮሴፍ በህይወት ጉዞው ፍጹም (እንከን የለሽ) የነበረ ባይሆንም እንኳ በመጽሐፍ ቅዱስ በሁሉም ስፍራ ስለርሱ የተጻፈው የሕይወት ታሪክ የሚያሳየን መልካምነቱን ነው፡፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የሚያመሳስላቸውን በአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ምንም ተጽፎ ባናገኝም የስነመለኮት ምሁራን በሚከተለው መልኩ አመሳስለዋቸዋል፡፡

- ሁለቱም በአባቶቻቸው የተወደዱ ነበሩ (ዘፍ 37፡3፣ ማቴ 3፡17)
- በራሳቸው ወንድሞችና ወገኞች ተጠልተዋል ተገፍተዋልም (ዘፍ 37፡4፣ዮሐ 15፡24)
- እንደመሪ ተገፍተዋል (ዘፍ 37፡8፣ ሉቃስ 19፡14)
- ተዶልቶባቸዋል (ዘፍ 37፡18፣ ማቴ 27፡1)
- በብር ተሸጠዋል (ዘፍ 37፡28፣ ማቴ 26፡15)
- ፈተናን ተቋቁመዋል አሸንፈዋልም (ዘፍ 39፡7-12፣ ዕብ 4፡15)
- ታላቅ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል (ዘፍ 41፡42-44፣ ማቴ 28፡18)

የተስፋው ህዝብ ገና በግብጽ ነው፡፡ ዘፍጥረትም የሚያቆመው የዮሴፍን አስደናቂ እምነት በመዘገብ ነው፡፡ ይኸውም እግዚአብሔር እብራዊያንን ከግብጽ ሲያወጣቸው የእርሱንም አጽም ይዘው እንዲወጡ በማዘዙ ታይቷል፡፡ ከዚህ በኋላ የምናየው የእስራኤላዊያንን ከግብጽ ሐገር የመውጣት ሂደት ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## ዘጸዓት "ከባርነት ወደ ነጻነት"

### ትምህርት ዘጠኝ

### የግብጽ ባርነት እና የሙሴ መጠራት

### መግቢያ

ቀደም ሲል እንዳየነው ያዕቆብ ከመጀመሪያዎቹ ልጆቹ እና የልጅ ልጆቹ ጋር 70 ሰው ሆኖ ወደ ግብጽ እንደገባ በዘፍጥረት 49 ላይ ተመልክተናል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ዕብራዊያን ከባርነት ለመላቀቅ ያደረጉትን ትግል በመጨረሻም በእግዚአብሔር እርዳታ ነጻ መውጣታቸውን እና ተዛማጅ ጉዳዮችን እንመለከታለን፡፡

ሰውን የመቤዠት ተግባር በዘፍጥረት የተጀመረ ቢሆንም የዘጸዓት መጽሐፍ እስራኤል ከግብጽ ባርነት ነጻ ስለመውጣቷ የሚናገር ብቻ ሳይሆን ስለ ሰው ልጆች ነጻነት ምሳሌ የሚሆን መጽሐፍ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ የክርስቶስ ኢየሱስን የመቤዠት ሥራ የሚያመለክቱ ምሳሌዎች ወይም ጥላዎች እናገኛለን፡፡

1. በምዕ 12፡3-14 የተደረገው ፋሲካ (ዮሐ 1፡29፡ 1ሮ 5፡7)
2. በምዕ 16፡10-15 ከሰማይ የወረደላቸው መና (ዮሐ 6፡31-35)
3. በምዕ 17፡1-6 እንዲያፈልቁ በበትር የተመታው ዓለት (1ቆሮ 10፡1-4)

### I. የዘጸዓት መጽሐፍ

የዘጸዓት መጽሐፍ ስለ እስራኤላዊያን (ዕብራዊያን) ከግብጽ ባርነት ተላቅቀው በሰላም ስለመውጣታቸው ይነግረናል፡፡ ዕብራዊያን በዮሴፍ ለግብጽ በነበረው መልካም አገልግሎት ምክንያት የፈርኦን እንግዶች ሆነው ይኖሩ የነበሩ ህዝብ ናቸው፡፡ ከያዕቆብና ከዮሴፍ ሞት በኋላ ዕብራዊያን በቁጥር መብዛታቸውንና ግብጽንም መሙላታቸውን (ዘጸ 1፡7) ያስነብበናል፡፡ ይህም ሁኔታ በፈርዖን መንግስት ስጋትን በመፍጠሩ ዕብራዊያንን በተለየ ሁኔታ መመልከት ይጀምራል (ዘጸ 1፡8-11)፡፡ በመሆኑም ዘመናት እየገፉ ሲመጡ በግብጽ ባሪያ የመሆን እጣፈንታ ደርሶባቸዋል "በብርቱ ሥራም ያስጨንቁአቸው ዘንድ ግብር አስገባሪዎችን ሾመባቸው ለፈርዖንም ፊቶምንና ራምሴን ጽኑ ከተሞች አድርገው ሠሩ፡፡" (1፡11)

ከዚህም ባርነት ለማምለጥ በከፍተኛና መራር ጩኸት የእግዚአብሔርን እርዳታ እንደፈለጉና በኋላም በሙሴ መሪነት ነጻ ወጥተው ለአብርሃም ወደተገባው ወደ ተስፋይቱ ምድር ግስጋሴ እንደጀመሩ ይዘግብልናል፡፡

በዚህ መጽሐፍ የሚታዩት ዋና ዋና ጉዳዮች

- የእግዚአብሔር የተናገረውን የተስፋ ቃል ጠባቂነት እና ፈጻሚነት እንዲሁም ከአብርሃም ትውልድ ጋር የነበረውን ህብረትና ከእነርሱም ጋር የገባውን ቃልኪዳን

- የሙሴ እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ነጻ እንዲያወጣና በእርሱ በኩል ቃል ኪዳኑን ሊገልጥና ለህዝቡም እንዲያስተምር በእግዚአብሔር መመረጡ
- በመጨረሻም የእስራኤልን (የዕብራዊያንን) ጠላቶቻቸውን ድል በማድረግ ምድሪቱን ለመውረስ መዘጋጀታቸውን እናያለን፡፡

**የመጽሐፉ ዋና ዋና ገጸባህሪያት**

- ሙሴ፣ የግብጽ ፈርዖን፣ አሮን እና እግዚአብሔር ናቸው

**የመጽሐፉ ዋና ዋና ክስተቶች**

- የዕብራዊያን የግብጽ ባርነት
- የሙሴ ጥሪ
- የዕብራዊያን ነጻ መውጣት
- የቃል ኪዳኑ መሰጠት
- የዕብራዊያን በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ
- ትክክለኛው የአምልኮ ገጽታ በእግዚአብሔር ለህዝቡ መገለጥ ይገኝበታል፡፡

ፖል አር. ሀውስ የተለያዩ ምንጮችን ጠቅሰው እንዳስፈሩት ከሆነ አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብና ዮሴፍ የኖሩት ከ2100 -1700 ዓ.ዓ ነው፡፡ በዚህ ዘመን ግብጽ በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውና በወታደራዊ ሀያል በጣም ጠንካራ ነበረች፡፡ ከ1700-1550 ዓ.ዓ ሂክስ በሚባሉ የውጭ ሀይሎች ሃያልነቷን አጥታ ነበር፡፡ እንደገና ግብጽ ከ1550 -1200 ዓ.ዓ ወራሪዎችን ድል በማድረግ የበላይነቷን አረጋገጠች፡፡ ሁሉም የታሪክ ምሁራን ከዘጸዓት እስከ ዘዳግም ያለውን ታሪክ የተፈጸመው በዚህ ዘመን እንደሆነ ይስማማሉ፡፡[7]

**ሀ/ ስያሜው**

ዘጸዓት የሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘው "Exodus" ከሚለው የላቲን ቃል ሲሆን ይህ ስያሜ የተሰጠው የሰፕቱዋጀንት መጽሐፍ በተዘጋጀበት ወቅት ነው፡፡ ቀጥተኛ ትርጉሙ መውጣት "going out" ወይም መውጫ መንገድ ማግኘት "pathway out" መሆኑን ጆርጅ አሳድ የተባሉ የስነመለኮት ምሁር ይናገራሉ፡፡ ይህ የተባለበት ምክንያት የመጽሐፉ የመጀመሪያዎቹ 12ቱ ምዕራፎች (1:1-12:36) ይህንን የሚደግፉ ሃሳቦችን አካትተው በመገኘታቸው ነው፡፡[8]

**ለ/ የመጽሐፉ ጭብጥ ሀሳብ**

የመጽሐፉ ጭብጥ ሐሳብ እግዚአብሔር የያዕቆብን ትውልድ ከግብጽ ባርነት ነጻ በመውጣት እስራኤል የምትባል አገር እንድትመሰረት ያደረገበትን መንገድ ማሳየት ነው፡፡ በዚህ ሂደት ታላላቅ መለኮታዊ ክንውኖች በመታየታቸው ምክንያት በርካታ ምሁራን "እንደ ዘጸዓት መጽሐፍ የእግዚአብሔር ታላቅ ሃይል እና ክብር የተገለጠበት መጽሐፍ የለም" ይላሉ፡፡

**ሐ/ የመጽሐፉ አከፋፈል**

---

[7] Paul R. House, Old Testament survey, U.S.A, 1992, p46
[8] George Assad. Pentateuch: A study Guide, ICI Univerisity- 2004. P 104

- እስራኤል በግብጽ (ዘጸ 1፡1-12፡26)
- ጉዞ ወደ ሲና ተራራ (ዘጸ12፡37-19፡36)
- እስራኤል በሲና ተራራ (ዘጸ19፡3-40፡38)

## II. የግብጽ ባርነት እና የሙሴ መጠራት

### ሀ/ የባርነቱ ሁኔታ

ከዘፍ 50 እስከ ዘጸ 1 ያለውን የጊዜ ክፍተት ለማወቅ አስቸጋሪ ቢሆንም አንዳንድ የስነ-መለኮት ሊቃውንት 71 ዓመት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ዕብራዊያኑ መከራ የገጠማቸው ዮሴፍን የማያውቅ ንጉስ ከነገሰበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን በዘጸዓት 1፡8 እንመለከታለን፡፡ በዘጸ 12፡40 ዕብራዊያኑ በግብጽ የኖሩበትን የዘመን ርዝመት በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን ይህም 430 ዓመት እንደሆነ ይነገራል፡፡

ግብጻዊያኑ ዕብራዊያንን በአስከፊ ሁኔታ ጭቆናና እንግልት ያደረሱባቸው ዋና ምክንያት በምዕራፍ 1፡9-10 የተጠቀሰ ሲሆን ይኸውም አንድ ቀን እብራዊያን በቁጥር በዝተው ከእኛ ሊበረቱ ወይም ከጠላቶቻችን ጋር (ከግብጽ ጠላቶች ጋር) በመተባበር በጠላትነት ሊነሱብን ይችላሉ ከሚል ስጋት የተነሳ ነው፡፡

**ዕብራዊያኑ የተቀበሉትን መከራ ከዚህ እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፡፡**

- በሚሰሩት ስራ የሚያስመርሩ ሃላፊዎችን መሾም (ቁጥ 11)
- ሸክምን ወይም ቀንበርን ማከበድ (ቁጥ 13-14)
- የዕብራዊያን ሴቶች ወንድ ልጅ ሲወልዱ በአዋላጆቹ በኩል ልጆቹ እንዲገደሉ ማድረግ (ቁጥ 15-16)
- ወንዶች ህጻናትን ሁሉ እንዲገድሉ ለባሎቻቸው ትዕዛዝ ሰጡ (ቁጥር 22)

### ለ/ የሙሴ አስተዳደግና ለአገልግሎት መጠራት

በሐዋሪያት ሥራ 7፡22-26 ስለ ሙሴ ህይወት "ከመወለድ እስከ አገልግሎት" በዝርዝር ተቀምጧል፡፡ ሙሴ የተወለደው በዘጸ 2 ሲሆን ከሌዊ ነገድ እንደሆነ እና አባቱ እንበረምም እናቱ ደግሞ ዮካብድ እንደሚባሉ በዘጸ 6፡19-20 ላይ እናነባለን፡፡ ሙሴ የተወለደው ወንዶች ሁሉ ሲወለዱ (ከማህጸን ሲወጡ) ይገደሉ የሚል ጥብቅ ትዕዛዝ በወጣበትና ተፈጻሚ በሆነበት ውቅት ነበር (ዘጸ 2፡1-4)፡፡

የእድሜው የመጀመሪያዎቹ 40 ዓመታት የግብጻዊያንን ትምህርት ለመማር የጠቀመው ሲሆን (ሐዋ 7፡22)፣ ግብጻዊያን በዕብራዊያን ላይ ግፍ እና በደል ባበዙበት ዘመን አንድን ግብጻዊ ገድሎ ወደ ምድያም ኮበለለ (ዘጸ 2፡11-15)፡፡ ከ40 ዓመታት ቆይታ በኋላ እግዚአብሔር በዘጸ 3 ሙሴን ለአገልግሎት ጠራው፣ የተጠራበት ዓላማ በዕብራዊያን 11፡20-26 በሐዋ 7፡20-43 እና በዘጸ 3 በግልጽ ተብራርቶ ይገኛል፡፡

## III. የሙሴ ተልዕኮ

በምድያም ለ40 ዓመታት የአማቱን በጎች ሲጠብቅ መቆየቱን አንዳንዶች ለሙሴ የፍሬ አልባነት ውቅቶች ናቸው ብለው ይናገራሉ፡፡ ሀቁ ግን ተቃራኒው ነው፡፡ ምክንያቱም ከፈርዖን ቤት የኮበለለ በስሜታነት ግብጻዊውን በመግደሉ ነው፡፡ ሙሴ መንፈሳዊ ብስለትን እና አንዳንድ አደራረጎችን በማስተዋል ማከናወን የተለማመደው በምድያም በቆየበት አመታት ነው፡፡ አይደለም ለአንድ ታላቅ መሪ ለሁላችንም ሚዛኑን የጠበቀ ዕድገት ለየግል መንፈሳዊ ህይወታችንም ሆነ ለአገልግሎታችን ወሳኝ ነገር ነው፡፡ ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ህይወትም የምንማረው ይህንን እውነት ነው (ሉቃስ 2፡52)፡፡ ከ40 ዓመት የምድያም ቆይታ በኂላ ልቡ የተዘጋጀ ወይም ብስለት የገነባ ህይወት እና ዝግጅት የነበረው ይመስላል (ምንም እንኳ የመጣውን "የክርስቶስ ቅድመ ስጋዌ መገለጥ" "Theophany" በመጠባበቅ የቆየ ባይሆንም) ዘጸ 3፡2-10፡፡ ይሁንና ግን እግዚአብሔር ህዝቡን ከባርነት ቀንበር ነጻ እንዲያወጣ ሲጠራው ሙሴ ግን ይህን ሐላፊነት በመቀበል ህዝቡን ነጻ ማውጣት የሚችል መሪ መሆን እንደማይችል ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ ይሰጣል፡፡ እግዚአብሔር ግን ለሙሴ ምላሽ በመስጠት ጥሪውንና ሐላፊነቱን እንዲቀበል ያደርገዋል፡፡

በአጠቃላይ ሙሴ የተሰጠው አላፊነት በቀላሉ መጣ አልነበረም፡፡ ቀንበር የከበደው ህዝብ ያሰማው ጩኸት በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ አግኝቶ ኖሮ ይህንን ህዝብ ከተጫነበት ቀንበር ነጻ ለማውጣት ነበር፡፡ የህዝቡም ጩኸት እግዚአብሔር ከአባቶቻቸው ጋር የገባውን ኪዳን እንዲያስብ አድርጎታል፡፡ በዘጸ 2፡24 እግዚአብሔርም ከአብርሃም ከይስሐቅና ከያዕቀብ ጋር ያደረገውን ኪዳን አሰበ ይላል፡፡ እንዚህ በጭንቅ ውስጠዥ የነበሩ ህዝቦች የተስፋ ህዝብ ቃል ኪዳን ሊገባላቸው ያሉ ህዝቦች ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ለሙሴ ሲገለጥም እንዲህ ነበር ያለው እኔ የአባትህ አምላክ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምለክ ነኝ ነው ያለው፡፡ (ዘጸ 2፡6) ስለዚህ ጥሪውና ተልዕኮው ወሳኝ ነው፡፡ እንዲሁ በቀላሉ አሻፈረኝ በማለት የሚታለፍ አልነበርም፡፡

**ሀ/ ከፈርዖን ጋር የተደረገ ግጭት (ዘጸ 5፡1-10፡29)**

በዘጸ 5፡1- 4 ያለውን የምንባብ ክፍል ስናነብ ሙሴ እና አሮን እግዚአብሔር የተናገራቸውን ሃሳብ ለፈርዖን ሲነግሩት እርሱ በእምቢተኝነት በመፅናት በዕብራዊያኑ ላይ የጭቆና ቀንበር አበዛባቸው (5፡5-14)፡፡ በዚህ ምክንያት ዕብራዊያኑ በሙሴ እና በአሮን ላይ ተቃውሞ አቀረቡ (ቁጥ 15-19)፡፡ በዚህ ጊዜ ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ብርቱ ጸሎት አቀረበ (ቁጥ 22-23) እግዚአብሔርም ፈጣን ምላሽ ሰጠው (6፡1-8)፡፡

ይግጭቱ ጡዘት በማደጉ ምክንያት በሙሴ እና በፈርኦን መካከል ሳይሆን በአንድ ጨቋኝ አገር እና በጭቆና ስር በሚማቀቁ ህዝቦች መካከል ሆነ ከዚያም አልፎ ጦርነት በእውነተኛው አምላክ "the one true God" እና በጣዖቶች (የሀሰት አማልክት) "the false pagan gods" መካከል እሆነ መጣ (ዘጸ 7፡10-12፣ ዘጸ 12፡12)፡፡ በመጨረሻም በእግዚአብሔር የበላይነት እና በእግዚአብሔር ታላቅ እርዳታ እስራኤላዊያን ፈርኦንን አሸንፈው ነጻ ወጥተዋል (ዘዳ 6፡21)፡፡

**ለ/ ፋሲካ (ዘጸ 11፡1-12፡36)**

ህዝቡን ነጻ ለማውት እግዚአብሔር የፈጸማቸው ዘጠኙ መቅሰፍቶች በግብጽ ምድር የሚኖሩ ህይወት ያላቸው ነገሮችን እና ተፈጥሯዊ ገጽታዎችን ጎድቷል፡፡ በመጨረሻም እግዚአብሔር

ሙሴን ተጠቅሞ እያንዳንዱ ቤት የሚገኝ በኩር ላይ የሞትን ፍርድ አድርጓል፡፡ (11:4-8) ነገር ግን ይህ መቅሰፍት እስራኤላዊያንን እና እንስሶቻቸውን አልነካም (11:7)፡፡ ይህ ክስተት በእስራኤላዊያንና በግብጻዊያን መካከል ትልቅ ልዩነት መፍጠሩን ከታሪኩ ፍጻሜ መረዳት ይቻላል፡፡ በመጨረሻም በግብጽ ምድር የነጻነታቸውን መታሰቢያ ፋሲካ ካደረጉ በኂላ ከፈርዖን ባርነት ተላቅቀው ወደ ተስፋይቱ ምድር ጉዞ ያደርጋሉ፡፡

የእስራኤላዊያን ከግብጽ ባርነት መላቀቅ ተፈጥራዊ ወይንም ስጋዊ ከሆነ ባርነት ከመላቀቅ ያለፈ ትርጉም አለው፡፡ ይህም በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ በኩል በሐጢአት ባርነት ስር የነበሩትን የሰው ዘር ሁሉ ነጻ የማውጣትና ወደ ዘላለማዊው መንግስት የማስገባትን (የማፍለስን) ስራ የሚያሳይ ነው፡፡

## IV. ወደ ሲና የተደረገ ጉዞ የእግዚአብሔር ህግ እና የመገናኛው ድንኳን

### 4.1. ወደ ሲና ተራራ የተደረገ ጉዞ

#### ሀ/ ከራምሴ ወደ ቀይ ባህር (ዘጸ 12-37-14:2)

በዘጸዓት 12-37 እንደምናው ዕብራዊያን ይኖሩበት ከነበረው ራምሴ ከተባለው አካባቢ ወደ ሱኮት የመጀመሪያውን እንቅስቃሴ አደረጉ፡፡ የጉዞውን ሁኔታም በፍጥነት እንደተደረገና የህዝቡም ቁጥር ወደ 3.000.000.000 (ሶስት ሚሊዮን) እንደሚጠጋ ሆልድሮፍት ጥናታዊ ግምታቸውን ያቀርባሉ፡፡[9]

ከዚህ በተጨማሪም በቁ 38 “ደግሞም ሌላ ድብልቅ ህዝብ…” የሚለው ዓለፍተ ነገር ከዕብራዊያን ውጭ የሆኑ ሌሎች ወገኖችን መሆኑን ሲያብራሩ ይህም የዕብራዊያን አምላክ ከግብጽ አማልክት ይልቅ ኃያል እና ሉዐላዊ መሆኑን ማረጋገጫ ነው፡፡ እንዚህ ወገኖች ከሌላ አገር የመጡ በጭቆና ስር የነበሩ ባሮች ናቸው በማለት ጥናታቸውን ያሰፍራሉ፡፡

የሌሎች ወገኖች ከዕብራዊያን ጋር የመውጣታቸው ምክንያት ናቸው ተብሎ የሚታሰበው

- ✓ ከዕብራዊያን ጋር በባርነት ሳሉ የነበሩበትን ሐይማኖት በመለወጥ የዕብራዊያንን የአንድ አምላክ አምልኮ የተቀበሉ (proselyte) ናቸው
- ✓ እግዚአብሔር በግብጽ ላይ ባደረገው ተዓምራት የተማረኩና በእምነት ከዕብራዊያን ጋር አንድ ለመሆንና እግዚአብሔርን ለማምለክ የወሰኑ ናቸው
- ✓ ቀንበሩና ጫናው የበዛባቸው ሰዎች ስለነበሩ አጋጣሚውን በመጠቀም ከዕብራዊያን ጋር የወጡ ሊሆኑ ይችላሉ የሚሉ ናቸው፡፡

እግዚአብሔር ሙሴን የሰውን፣ እና የእንስሳት በኩር ሁሉ ለእርሱ እንዲቀድስ አዘዘው ይኸውም እስራኤላዊያንን ከአስረኛው መቅሰፍት በመጠበቅና የግብጻውያንን በኩር በመቅሰፍ ህዝቡን ከግብጻዊያን ጫናና ቀንበር ማዳኑንና ነጻ ማውጣቱን ለማመልከት ነው፡፡ (በዘጸ 13:2 ና 12)፡፡ የእግዚአብሔር ዕብራዊያንን ከግብጽ የማውጣቱ ሂደት በዘጸዓት 13:17-22ተገልጿል፡፡

[9] Holderoft L. Tomas, The Pentatuch, Okland, California; Western Book Campany, 1966. P.62

*ከግብጽ ወደ ከነዓን የሚያደርሱ ሁለት አማራጭ መንገዶች ነበሩ፡፡*

አንደኛው በላይኛው ክፍል በመሬት ተጉዘው የሚደርሱበት ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ የቀይ ባህርን በመሻገር በደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በበረሃ የሚጓዙበት መንገድ ነው፡፡ (ዘጸ 13፡17-18)

**ለ/ ቀይ ባህርን መሻገር (ዘጸ 14፡3-15-21)**

ፈርዖን ዕብራዊያን ቀይ ባህርን መሻገር አይችሉም ብሎ ስለገመተ ታላቅ ሰራዊት እንዲከተላቸው አደረገ እነርሱም ፈሩ፡፡ "ሙሴም ለሕዝቡ አትፍሩ፥ ዛሬ የምታዩአቸውን ግብፃውያንን ለዘላለም አታዩአቸውምና ቁሙ፥ ዛሬ ለእናንተ የሚያደርጋትን የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ፡፡ እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል፥ እናንተም ዝም ትላላችሁ አላቸው፡፡" (14፡13-14) በማለት ህዝቡን ያበረታታል፡፡

እግዚአብሔር በፈጠረው ፍጥረት ላይ ሙሉ ስልጣን ስላለው ቀይ ባህርን ከፍሎ የቃል ኪዳኑ ህዝብ በደረቅ እንዲሻገሩ አደረገ (ቁጥር 22)፡፡ በተቃራኒው ግብጻዊያን በተከፈለው ባህር ለመሻገር ሲሞክሩ እግዚአብሔር የባህሩን ውሃ ወደ ቦታው እንዲመለስ ስላዘዘው እስከ ሰረገላቸው ሰጠሙ (ቁጥ 27)፡፡

በመሆኑም ቀይ ባህር ሁለት ታላላቅ ክንውኖች ተከናውነውበታል፡፡ እነርሱም

- የእግዚአብሔርን ለእብራዊያን (ለተስፋው ህዝብ) የተገለጠው ብርቱ የማዳን ክንድ
- የእግዚአብሔርን ፍርድ በህዝቡ ጠላቶች ላይ

በመጨረሻም ዕብራዊያኑ የእግዚአብሔርን ክብር እና ሃይል በማየታቸው ምክንያት ለእግዚአብሔር ታላቅ ምስጋና ያቀርባሉ፡፡ (15፡1-21)

ጳውሎስ የቀይ ባህርን መሻገር ከውሀ ጥምቀት ጋር ያገናኘዋል፡፡ (1ቆሮ 10፡1-2) ከቀይ ባህርር መሻገር በኋላ አሮጌውን የባርነት አለም ከኋላቸው ትተውታል በአዲስ ህይወት እግአብሔርንም የማምለኪያ ጊዜ ሆኖላቸዋል፡፡ (ዘጸ 15)

በዝማሬያቸውም በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን ጠንካራ እምነት ገልጠዋል፤ ከነዓናዊያንን ሲገጥሙ ተዓምራዊ በሆነ ሁኔታ ሊያድናቸውም እንደሚችል አሳይተዋል፡፡ (ዘጸ 15)

እግዚአብሔር ለምንድነው ህዝቡ ወደ ኋላ የመመለስ እድል በማያገኙበት አቅጣጫ ወደተስፋይቱ ምድር የመራቸው? ምናልባትም እምነትን ሊያስተምራቸውና ተዓምራቱን ሊያሳይቸው ፈልጎ ይሆን?

### 4.2. ከቀይ ባህር ወደ ሲና (ዘጸ 15፡22-19፡2)

በዚህ ወቅት እስራኤላዊያን ግብጽ የምትባለውን ሀገር ብቻ ሳይሆን አፍሪካ የምትባለውንም አህጉር ጭምር ለቀቀው ወደ እሲያ ወደምትባል አህጉር መጥተዋል፡፡ በመሆኑም ለስጋዊ ፍላጎታቸው ከግብጽ ሲያገኙ የነበሩት መሰረታዊ ጥያቄዎችን በተለይም ደግሞ ምግብ እና ውሃ የመሳሰሉ ነገሮች ፈጣን አቅርቦት የሚሹ ጉዳዮች ነበሩ፡፡ በረሃብና በጥም የሚያልቁ ስለመሰላቸው በእግዚአብሔር ላይ ማጉረምረም ጀመሩ (ዘጸ 15፡22-26)፡፡ በእግዚአብሔር ላይ ማጉረምረም

አለማመንን የሚያስከትል ሲሆን (ዕብ 3፡12- 4፡3) ውጤቱም ጥፋት መሆኑ በ(1ቆሮ 10፡10) ተጽፏል፡፡ ቢሆንም ግን እግዚአብሔር ከቸርነቱ እና ከሁሉን ቻይነቱ የተነሳ የሚጣፍጥ ውሃ በዘጸዓት 15፡25 እንዲሁም ከሰማይ መናን አውርዶ (በዘጸ 16) እንዲበሉ በመስጠት የህዝቡን ጥያቄ መልሷል፡፡ 1ቆሮንቶስ 10፡4-5 ዘጸዓት 17 ከአለቱ የወጣው ውሀ የክርስቶስ ምሳሌ መሆኑን ይጠቅሳል፡፡

ወደ ሲና ተራራ ከመድረሳቸው በፊት ሁለት ዋና ዋና ክስተቶች ነበሩ

- የእስራኤል ከአማሌቃዊያን ጋር መዋጋት (ዘጸ 17፡8-16)
- የሙሴ አማት ዮቶር ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር ሙሴን ሊጎበኘው መምጣቱ

ከዮቶር የተቀበለው ሀላፊነትን የማከፋፈል ምክር በሙሴ ተቀባይነት ማግኘቱ ስለ ሙሴ ትህትና የሚነግረን እውነት አለ፡፡

ሙሴን በእግዚአብሔር የሚታመን ሰው እንደነበረ በጸሎት ትጋቱ እና በዚህም ምክንያት በአማሌቃዊያን ላይ በተጎናጸፈው ድል እንመለከለታለን፡፡

**ሀ. አስርቱ ትዕዛዛት እና የተሰጠው ኪዳን (ዘጸ 19፡3-4፡18)**

በርካታ ሊቃውንት እንደሚናገሩት ከሆነ ከ6 ሳምንታት ጉዞ በኋላ እስራኤላዊያን ወደ ሲና ተራራ እንደደረሱ ይታመናል፡፡ እግዚአብሔር ሙሴን በዚያ ተራራ በታላቅ ድምጽ ማናገር መጀመሩን በዘጸ 19፡3 እንመለከታለን፡፡ በቁጥ 3 የሕጉ ዓላማ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ይህንን በትክክል መማር እና መቀበል እንዲችሉ ለማድረግ እና መንፈሳዊ ብስለታቸው እንዲያድግ በተራራው ስር ቢያንስ አንድ ዓመት ያህል እንደቆዩ ምሁራን ይናገራሉ፡፡

በምዕራፍ 19 በቂ ዝግጅት ከተደረገ በኋላ በምዕ 20፡1-17 ሙሴ 10ቱን ትዕዛዛት ከእግዚአብሔር የተቀበለ ሲሆን በምዕራፉ የመጨረሻ (በቁጥ 23-26) ራሳቸውን ከጣዖት እንዴት መጠበቅ እንደሚገባቸው እና ለእግዚአብሔር ምን ዓይነት መሰዊያ ማዘጋጀት እንደሚገባቸውም መመሪያ ተላለፈላቸው፡፡

**ለ. «የቃል ኪዳን ልብ /ማዕከል/» (ዘጸ 20-24)**

ከዘጸዓት 20-24 ያለው ክፍል አስርቱ ትዕዛዛት በመባል የሚታወቀው ህግ በሲና ተራራ በእግዚአብሔር ተጽፎ የተሰጠበት ነው (ዘጸዓት 20)፡፡ እግዚአብሔርም ከግብጽ ከወጡ በኋላ ከህዝቡ ጋር ቃል ኪዳን የገባበት የመጀመሪያው ስፍራ ነው፡፡

ቃል ኪዳን ማለት 'ስምምነት'፣ 'ውል' እንደማለት ነው፡፡ ቃል ኪዳን የሚገባቡ አካላት ቃልኪዳኑ የሚጠይቀውን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቃልኪዳን ወዳጅነትን፣ መሰጠትን እና በመሃላ መተሳሰርን የሚያመላክት ነው፡፡ ቃል ኪዳን የእድሜ ልክ ትስስርንና ህብረትን የሚጠይቅ በመሆኑ በቀላሉ የማይሰበር ወይንም የማይፈርስ ነው፡፡

በጥንቱ ዘመን ሐገሮች (ህዝቦች)፣ ግለሰቦች፣ ቤተሰቦች እንዲሁም የሐይማኖች ተቋማት ቃልኪዳን ይመሰርቱ ነበር፡፡ ቃል ኪዳን በሚገባበት ጊዜ የራሱ የሆነ ስርዓት አለው፡፡ ለምሳሌ ምግብ በጋራ

መብላት የመሃላ ስርዓት መፈጸምን የመሳሰሉ ስርዓቶች ይከናወናሉ፡፡ ቃል ኪዳኑ ስርዓት በለው ሁኔታ በጽሑፍ ተዘጋጅቶ አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ይጠበቃል፡፡ ቃልኪዳን ማፍረስ ከፍተኛ ስህተት ነው፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ አገሮች ወደ ጦርነት ሊያመሩ ይችላሉ፡፡ የግለሰቦች ህብረት ታማኝ ባልሆኑ ሰዎች ምክንያት ይበተናል፡፡ የቀደመው የቃል ኪዳን ሰንድ ይቀደዳል በድንጋይም ላይ የተቀረጸ ከሆነም ድንጋዩ ከጥቅም ውጭ እንዲሆን ይደረግና ሌላ አዲስ ቃልኪዳን የሚገባ ከሆነ በሌላ ይተካል፡፡ በየትኛውም ቃል ኪዳን ውስጥ ስምምነቱን የሚያስጠብቅ ግዴታ ይሰፍርበታል፡፡

ስለዚህ በሙሴ ጊዜ እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር የገባው ቃልኪዳን ምን ነበር? ይህ ቃልኪዳን በእስራኤልና በጎረቤቶቻቸው መካከል ፍጹም መተሳሰርን የሚያመጣ ኪዳን ነው፡፡ ስለዚህ ሁለቱም ወገኖች በኪዳኑ ተጠቃሚ እንደመሆናቸው መጠን ኪዳኑን የሚያፈርስ ወገን ተገቢውን ቅጣት ያገኛል፡፡ ከላይ እንዳየነው የተለያዩ ህዝቦች ግለሰቦች ቃልኪዳን ይገባባሉ፡ ይሁን እንጂ የእስራኤል ከሁሉም ይለያል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት

- ከሁሉም ዓይነት ኪዳኖች ውስጥ የእስራኤልን ልዩ የሚያደርገው እስራኤል ለአምላኳ ፍጹም መሰጠትን የምታሳይበት ኪዳን መሆኑ ነው፡፡
- የትኛውም ቡድን ወይም ህዝብ እስራኤል ለያህዌ የምታሳየውን የቃልኪዳን ታማኝነት ማሳየት ስለማይችል ነው፡፡

ይህም የህግ ዝርዝር በህዝቡ ልብ ፍርሃትን እንዳመጣ መረዳት ይቻላል፡፡

### *ሐ. የትዕዛዛቱ ሁለት ዋና ዋና ሐሳቦች*

ሀ. በህዝቡና በእግዚአብሔር መካከል ስለሚኖረው ግንኙነት

ለ. በህዝቡ የእርስ በርስ ግንኙነት ሊኖረው ስለሚገባ ስርዓት ዝርዝር የያዘ ነው፡፡

በምዕራፍ 21 የምናገኘው ተጨማሪ ህግ "የማህበራዊ ጉዳዮች ህግ" ይባላል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ማህበራዊ ኑሮአቸውን የሚመሩበት ዝርዝር ህግ በውስጡ ስለሰፈረ ነው፡፡

### መ. የአስርቱ ትዕዛዛትም ሆነ ሁለተኛው ህግ ትኩረት የሚያደርጉት

- በአንድ አምላክ አምልኮት ላይ ነው
- ከጣዖት አምልኮ መጠበቅን ወይም መራቅን
- በእግዚአብሔርና በእርስ በርስ ግንኙነታቸው ፍትህንና ቅድስናን መለማመድ ላይ ነው፡፡

እነዚህን ህጎች የእምነት ወይም ሀይማኖት፣ የአምልኮ፣ የአክብሮት፣ የጊዜ፣ የስልጣን፣ የህይወት፣ የንጽህና፣ የቁሳቁስ፣ አንደበትን የመጠበቅና እርካታን ማዕከል ያደረጉ ናቸው፡፡

### ሠ. በህግና በወንጌል መካከል ያለው ልዩነት

**ህግ፡-** የሰውን ሐጢአተኛነት ይገልጣል ከሐጢአት ለማምለጥ የሚቻልበትን አቅም ግን አይሰጥም፡፡ ይሁን እንጂ ህግን መጠበቅ ቢቻል ቀድሞም የተሰጠው ለመልካም ስለሆነ ሐጢአተኛው ህይወት ያገኝበታል፡፡ (1ጢሞ1፡8)

**ወንጌል፡** ለአማኞች ህግን በደስታ የመፈጸም ጉልበት ይጨምራል፡፡ እግዚአብሔርንም በፈቃደኝነት ለመታዘዝና ለማገልገል ያነሳሳል

**ህጉ፡-** እግዚአብሔርን እንደፈጣሪ እንድንታዘዘውና እንድናመልከው ሲያደርገን

**ወንጌል፡-** ግን በክርስቶስ በኩልና በርሱ ውስጥ እግዚአብሔርን እንድናመልከው ያደርገናል፡፡ በእርሱም ውስጥ የእግዚአብሔርን ጽደቅ፣ ሐይል ቅድስናና ምህረት እንድናይና እንድንለማመድ አስችሎናል፡፡

ጳውሎስ በገላቲያን 3፡24 ህጉ ወደ ክርስቶስ የሚያደርስ ሞግዚት ነው ይላል፡፡ ይህም የሚያሳየው ሰው በህግ በኩል ሐጢአተኛቱን ሲረዳ ህግ ወደፍርድ እንደማምጣት የመጀመሪያው የሚያደርገው ሐጢአተኛውን ወደ ክርስቶስ በማምጣትና ካለፈው ሐጢአት ከሚሰማው የጥፋተኝነት ስሜት አሁን ካለውም የሐጢአት መገኘት ለወደፊቱም ከሐጢአት ሐይል የሚድንበትን አቅም በእምነት እንዲቀበል ማድረግ ነው፡፡

እንዲሁም በሮሜ 7፡12 "ስለዚህ ሕጉ ቅዱስ ነው ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት።" በመጨረሻም የቃል ኪዳን መጽሐፍ የተባለው መመሪያ ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበለ ሲሆን (ዘጸ 21፡1-39፡9) እነዚህን መመሪያዎች በጽሑፍ እንዲያሰፍሩ ማድረጉን በምዕ 24፡4፤8 እንመለከታለን፡፡

- ህጎቹ የውጫዊ ስርዓት መገለጫዎች ብቻ ሳይሆኑ በውስጣዊና በልብ ጉዳይ ላይም የሚያተኩሩ ናቸው (ዘዳ 6፡5) "አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ።"
- የእግዚአብሔር ህግ ውጫዊ የሐጢአት ተግባራትን ብቻ ሳይሆን የሚከለክለው ውስጣዊ ሐሳቦችንም ጭምር ነው (ማቴ 5፡28) "ስለዚህ ሕጉ ቅዱስ ነው ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።"
- ህጉ አለማድረግን ሲያስጠነቅቀን በተቃራኒው ደግሞ ማድረግን ያስገድዳል፡፡ ለምሳሌ የአማላክህን ስም በከንቱ አትጥራ ይልና በተቃራኒው ደግሞ አክብረው ይላል፡፡
- በህጉ ሐጢአትን አለማድረግ ሲከለከል በተጨማሪም ለሐጢአት ምክንያት የሚሆኑ ሁኔታዎችም ተከልክለዋል፡፡ ለምሳሌ፡- ህጉ አትግደል ይልና በተጨማሪም ቁጣንና ቅንዓትንም ይከለክላል፡፡ ምክንያቱም ወደ ግድያ የሚያደርሱ መንደርደሪያዎች ናቸውና ነው፡፡ አመንዝራነትን ሲከለክል ከተቃራኒ ጾታ ጋር የሚደረጉ ቅድመ ሁኔታዎችንም ይከለክላል፡፡ (ምሳሌ 5፡8)

አንድ አካባቢ የበሽታ ወረርሽኝ ቢነሳና ሰዎችን ቢገድል ራስን ማዳን የሚቻለው ከዚያ ወረርሽኙ ከተዛመተባት አካባቢ ራስን በማግለል ነው፡፡ የህጉም ተግባር እንዲሁ ነው፡፡

- ህጉ ሁሉንም ሚዛናዊ በሆነ መለክ የሚዳኝ ነው፡፡ ለምሳሌ በቤተሰብ ህግ ውስጥ ስልጆች ወላጆቻቸውን ማክበር እንዳለባቸው በተሠጠው ህግ ውስጥ ወላጆችም ልጆቻቸውን በመውደድና መልካሙን በማድረግ እንዲያሳድጓቸቀው ያዝዛል፡፡ በተቃራኒውንም እንዲሁ ነው፡፡

- ህጉ ትልልቅ ሐጢአቶችን ብቻ ሳይሆን ትንንሽ ሐጢአቶችንም እንዳይደረጉ ይከለክላል፡፡ በእርግጥ ትልቅና ትንሽ የሚባሉ የሐጢአት አይነቶች አሉን? በራሳቸው ትልቅና ትንሽ ተብለው ባይጠሩም በንጽጽር ሲታይ ግን ወደዚህ ድምዳሜ ያመጣል፡፡

ለምሳሌ፡- ህጉ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ ይላል በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔርን በሐሰት ማምለክ አደገኛ ሆኑ እናየዋለን፡፡ “አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ፡፡ እሳትም ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ በላቸው፥ በእግዚአብሔርም ፊት ሞቱ፡፡” (ዘሌዋ 10፡1) ከዚህ የምንረዳው የአሮን ልጆች በህጉ የተከለከሉት ጣዖት እንዳያመልኩ ብቻ አይደለም ለእግዚአብሔር የማይገባ አምልኮ እንዳያቀርቡም ጭምር እንደሆነ እንጂ፡፡

- የእግዚአብሔር ህግ ሁሉ በእኩልነት ሊታይ ይገባል፡፡ የእግዚአብሔርን ህግ ከመፈጸም አኳያ ቅድሚያ ለዚህ ወይም ለዚያ በማለት ማበላለጥ ሳይኖር ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውም ሆነ ከጎረቤት ጋር የሚኖረንን ግንኙነት በተመለከተ የተሰጡ ህጎች ሁሉ እኩል ተፈጻሚነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ “እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ ከአዝሙድና ከእንስላል ከከሙንም አሥራት ስለምታወጡ፥ ፍርድንና ምሕረትን ታማኝነትንም፥ በሕግ ያለውን ዋና ነገር ስለምትተዉ፥ ወዮላችሁ፤ ሌላውን ሳትተዉ ይህን ልታደርጉ ይገባችሁ ነበር፡፡” (ማቴ 23፡23) “ዓመት በዓላችሁን ጠልቼዋለሁ ተጸይፌውማለሁ የተቀደሰውም ጉባኤአችሁ ደስ አያሰኘኝም፡፡ የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁና የእህሉን ቍርባናችሁን ብታቀርቡልኝም እንኳ አልቀበለውም ለምስጋና መሥዋዕት የምታቀርቡልኝን የሰቡትን እንስሶች አልመለከትም፡፡ የዝማሬህንም ጩኸት ከእኔ ዘንድ አርቅ የመሰንቆህንም ዜማ አላደምጥም፡፡ ነገር ግን ፍርድ እንደ ውኃ፥ ጽድቅም እንደማይደርቅ ፈሳሽ ይፍሰስ፡፡” (አሞጽ 5፡21-24) የእስራኤላዊያን ችግር እግዚአብሔርን የማምለክ ህግ አለመጠበቃቸው አልነበረም ከወንድማቸው ጋር እንዴት መኖር እንደሚገባቸው የተሰጣቸውን ህግ መተዋቸው ነበር፡፡
- የእግዚአብሔር ህግ የሚከለክለን እኛ ራሳችንን የምንሰራውን ሐጢአት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ሐጢአት እንዳንተባበር ጭምር ነው፡፡

**2. የእግዚአብሔር እና የእስራኤል ግንኙነት (የመገናኛ ድንኳን) (The Tabernacle) (ዘጸዓት 25-27)**

***ሀ/ በእስራኤል መካከል የእግዚአብሔር መኖሪያ* (ዘጸ 12፡37-14፡2፣ 15፡22-19፡2)**

እግዚአብሔር ሰዎችን የፈጠረበት አንዱ እና ትልቁ ዓላማ ህብረት (ከእርሱ ጋር እንዲያደርግ) ነው፡፡ በሐጢአት ምክንያት የፈረሰው ህብረት እንደገና እንዲታደስ እግዚአብሔር በህዝቡ መካከል ህልውናውን ማኖር ፈለገ፡፡ ስለዚህ ለሙሴ የመገናኛ ድንኳን እንዲያዘጋጅ አዘዘው፡፡ (24፡18 እና 25) ይህም ማደሪያ ለአዲስ ኪዳን ማደሪያ ጥላ መሆኑንን በዮሐንስ ወ. 1፡14 እንመለከታለን፡፡

እግዚአብሔር በሰዎች መካከል ማደር የፈለገው ክብሩን ወይም ማንነቱን ለሰዎች በመግለጥ ሰዎችን ከሞት እና ከጥፋት ለመመለስ መሆኑን ከተለያዩ የመጽሐፍት ቅዱስ የምንባብ ክፍሎችን መረዳት ይቻላል (ሮሜ 10፡9፣ 8፡9-11፣ ኤፌ 2፡19-22፣ 1ጴጥ 2፡4-5)፡፡

**ለ/ የመገናኛ ድንኳን ቅርጽ (ይዘት)**

- ⇨ የውጭ አደባባይ
- ⇨ ቅድስት
- ⇨ ቅድስት ቅድሳን

**በድንኳኑ ውስጥ የነበሩ እቃዎች መንፈሳዊ ትርጉም**

| የዕቃው ዓይነት | መንፈሳዊ ትርጉም |
|---|---|
| የብር መሰዊያ | በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ በኩል የሚገኝ ይቅርታና ድነት ያመለክታል (ዮሐ 1፡29፣ ዕብ 13፡12) |
| የመታጠቢያ ሳህን | መንጻት (ኤፌ 5፡22-27) |
| መቅረዝ | የክርስቶስ ኢየሱስ የሆነ የ ያበራ ህይወት (ዮሐ 8፡18) |
| የህብስቱ ገበታ | ከክርስቶሰ ጋር ባለ ህብረት መጽናት ወይም በክርስቶስ ላይ መደገፍ |
| የህጣን ማጠኛ | የምልጃ ጸሎት (ራዕይ 8፡3-5) |
| የቃል ኪዳን ታቦት | እግዚአብሔር መገኘት (ዕብ 9፡24) |

**ሐ/ የክህነት አገልግሎት** (ዘጸ 28፡29)

የክህነት አገልግሎት በይፋ ከመጀመሩ በፊት ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ የቤተሰብ መሪ፣ አባት፣ ወይም በቤተሰብ መካከል በእድሜ ጠና ያለ ሰው ቤተሰቡን በመምራት በጌታ ፊት መስዋዕትን የማቅረብ አላፊነት ነበረበት፡፡ ይህም እግዚአብሔርን የማምለክ አንዱ መንገድ ነበር፡፡ በመሆኑም የቤተሰቡ መሪ እንደ ካህን ያገለግል ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ነው የጋራ አምልኮ የተጀመረው፡፡ ስለዚህም ነው እግዚአብሔር ይህንን አገልግሎት በቤተመቅደስ ውስጥ በቋሚነት አላፊነት ወስደው የሚመሩ ሰዎችን የሾመው፡፡ በመሆኑም የሌዊ ነገድ ይህን አገልግሎት ከዳር ለማድረስ በእግዚአብሔር ተመረጠ፡፡

የእስራኤል ሽማግሌዎችና ካህናት ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብና ለህዝቡም መካከለኛ ለመሆን መስዋዕት ያቀርባሉ፡፡ የእነዚህም ሰዎች መስዋዕት ምሳሌነቱ የክርስቶስን ፍጹም መስዋዕት መሆን የሚያሳይ ነው፡፡ ራዕይ 13፡8 እንዲህ ይላል "ከዓለምም ፍጥረት ጀምሮ በታረደው በግ ህይወት መጽሐፍ ስሞቻቸው ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ ሁሉ ይሰግዱለታል፡፡"

**መ. የሊቀ ካህኑ እና የካህናቱ አልባሳት**

የካህናቱ የሚያብረቀርቀው ልብሰ ተክህኖ የሚያመለክተው የሊቀካህኑን የክርስቶስን ፍጡም ቅድስናና ንጽህና ነው፡፡ ለዚህም ነው አልባሳቱ በልዩ ትዕዛዝ ጥንቃቄ እንዲዘጋጁ የተደረገው፡፡

እንዲሁም በሊቀ ካህኑ ደረት ላይ የሚለጠፈው የአስራሁለት የእስራኤል ነገዶች ስም ምልክትነቱ ወይም ምሳሌነቱ የክርስቶስ አገልግሎትና ምርጦችን ወክሎ በላይ በሰማይ በአባቱ ዘንድ መግባቱን

አመላካች ነው፡፡ ይህንንም እውነት በኤፌ 3፡12 እንግዲህ ተብሎ እናነባለን “በእርሱም ዘንድ ባለ እምነታችን በኩል በመታመን ድፍረትና መግባት በእርሱ አለን፡፡”

### ሠ. በብሉይ ኪዳን የክህነት አገልግሎት

በብሉይ ኪዳን የክህነት አገልግሎት ከእግዚአብሔር የሆነ የአመራረጥና የሹመት ሂደት ነበረው

- ክህነት በመመረጥ ነው (ሌዊ ተመረጠ)
- በመወለድ (ከሌዊ ወገን የሆነ) ሲሆን በአዲስ ኪዳንም ቅዱሳን በክርስቶስ ኢየሱስ በመንፈስ ዳግሞ የክህነትን አገልግሎት ተቀብለዋል፡፡
- ይህ ብቻ አይደለም ካህናት አገልግሎታቸውን በይፋ ከመጀመራቸው በፊት ቢያንስ ለሰባት ቀናት የመንጻት ስርዓት (ለአገልግሎት የመለየት ሥርዓት) መፈጸም ይጠበቅባቸው ነበር፡፡ ይህም የሚያስተምረን በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ምንም ዓይነት አገልግሎት ከመስጠታችን በፊት ሁለንተናዊ ቅድስና አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ (ዘጸ 29፣30፣35 እና 37)
- በዘይት መቀባት
- የተለየ ልብሰተክህኖ መልበስ፡፡

በአዲስ ኪዳን አማኞች ሁሉ ካህናት ሲሆኑ ክርስቶስ ኢየሱስ ደግሞ ሊቀካህን መሆኑን ልብ እንበል፡፡

### ረ/ የመገናኛ ድንኳን ስራ መጠናቀቅ (ዘጸ 36-40)

የመገናኛውን ድንኳን ለመሥራት እግዚአብሔር ሁለት ሰዎችን መርጦ ኃይል አስታጠቃቸው፡፡ እንዚህም ሁለት ሰዎች ባስልኤልና ኤልያብ ይባላሉ፡፡ (ዘጸ 31፡1-11)

የመገናኛው ድንኳን ሲጠናቀቅ እግዚአብሔር የክብር ደመናውን በማውረድ ሥራቸውን ሁሉ እንደተቀበለ አረጋገጠ፡፡ ህዝቡን ሲመራ የነበረው ደመና በመገናኛው ድንኳን ላይ ወረደ ሞላውም፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔር የክብር ደመና ከመገናኛው ድንኳን በሚነሳበት ጊዜ የእስራኤል ህዝብ እግዚአብሔርን በመከተል ይጓዙ ነበር፡፡ (ዘጸ 40፡34-38)

# ምዕራፍ አራት

## ትምህርት አስር

## ዘሌዋዊያን "አምልኮና አገልግሎት" መስዋዕቶቹና ካህናቶቹ

### 1. የዘሌዋዊያን መግቢያ

ዘጸዓትን ስናጠና ከግብጽ የድንኳኑን መሰራትና በእግዚአብሔር ክብር መሞላቱን አይተናል፡፡ ስለ መገናኛው ድንኳን ስንነጋገር ደግሞ ህብረት ማዕከላዊ ጉዳይ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ በዘሌዋዊያን መጽሐፍ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግ የቻለ ማህበረሰብ ወይም ግለሰብ እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እና ማገልገል ይችላል? እንዴትስ ባለ መንገድ መስዋዕት ማቅረብ ይችላል? ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መስዋዕትስ ምን መምሰል ይገባዋል? ለሚሉ እና ተመሳሳይ ጥያቄዎች በቂ መልስ መስጠት የሚችል ግንዛቤ ለማግኘት የሚያስችለንን እውነታ እናያለን፡፡

በዘሌዋዊያን መጽሐፍ ከተራራ ራስ ላይ ሆኖ ሲናገር የነበረው እግዚአብሔር ወደ መገናኛው ድንኳን በመውረድ በዚያ ሁኖና ህዝቡንም ወደዚያ በመጥራት ያናግራቸዋል፡፡ ወደርሱ ጠርቶ ማናገሩን "ኤክሌሺያ" ከሚለው የግሪኩ የቤተክርስቲያን ትርጓሜ ጋር በማገናኘት በክርስቶስ የተጠሩ እና ድምጹን ከሚሰሙ በጎቹ ጋር ተያይዟል፡፡

በመሆኑም በዘሌዋዊያን መጽሐፍ ህዝቡ ተግባራዊ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ትዕዛዛትን እና ሀይማኖታዊ መመሪያዎችን (religious ordinances) እግዚአብሔር በሙሴ አማካኝት ወደ እስራኤላዊያን አስተላልፏል፡፡ ከመመሪያዎቹ ቀዳሚው ቅድስና ነው፡፡ በመጽሐፉ መካከለኛ ክፍል የተጠቀሰው የናዳብ እና የአብድዩ ኃጢአት ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ (ዘሌ 10)

### 2. የዘሌዋዊያን መጽሐፍ

#### ሀ/ የመጽሐፉ ስያሜ

የዘሌዋዊያን መጽሐፍ በዕብራይስጥ "Wayyiqra" «ወይክራ» የሚል ሲሆን በሰብቷጀንት ትርጉም ደግሞ አሁን የምናየውን ዘሌዋዊያን "Leveticus" የሚል ስያሜ ይዟል፡፡ ይህ ስያሜ የተሰጠበት ዋና ምክንያት የመጽሐፉ ይዘት እና ባህሪያ በካህናቱ ህይወት አገልግሎት እና በመስዋዕቱ ዙሪያ ስለሚያጠነጥን ነው፡፡

#### ለ/ የመጽሐፉ ይዘት/ አከፋፈል

- አምስቱ መስዋዕቶች (ምዕ 1-7)
- የክህነት ህግጋት (ምዕ 8-10)

- የመንጻት ህጎች (ምዕ 11-15)
- የስርየት ቀን (ምዕ 16)
- የቅድስና ህጎች (ምዕ 17-22)
- የተለያዩ ክብረ በዓላት (ምዕ 23-24)
- የመሬት መተዳደሪያ ደንቦች (ምዕ 25:27)

እንዚህ ህግጋት ሶስት መሰረታዊ ሀሳቦችን ይዘዋል፡፡

1. ወደ እግዚአብሔር መቅረብ
2. ከእግዚአብሔር ቤዛነት መቀበል
3. ከእግዚአብሔር ጋር ህብረትን ማድረግ

2. የእግዚአብሔር መገኘት (ዘሌ 1፡10)

**3. መስዋዕቶች**

በመጽሐፉ የመጀመሪያ ምዕራፍ ሁለተኛ ቁጥር ላይ ለእግዚአብሔር መቅረብ ስለሚገባው መባ ይናገራል፡፡ ህዝብ የሚያቀርበው መባ እግዚአብሔርን ደስ ካሰኘ የእግዚአብሔር ህልውና ከህዝቡ ጋር ይሆናል፡፡

**ሀ/ የእንስሳት መስዋዕት**

- የሚቃጠል መስዋዕቶች (1፡10)

- የቁርባን / የሰላም/ መስዋዕት (3፡1)

- የሐጢአት መስዋዕት (5፡6)

እነዚህ መሥዋዕቶች የሚቀርቡበት የየራሳቸው ምክንያት አላቸው፡፡ ይሁንና መስዋዕቶቹ ሁሉ ሰውን ከሐጢአት ሊያነጹ አልቻሉም፡፡ ነገር ግን ወደ ክርስቶስ ቤዛነት ያመለክታሉ (ዮሐ 1፡9፣ ዕብ 4፡16)፡፡ በክርስቶስ የተገኘው ስርየት ግን ሰውን ሁሉ ከየትኛውም ሐጢአት የሚያድን እና ህሊናን ከሞተ ሥራ የሚያነጻ ነው፡፡ (1ዮሐ 1፡7፣ ዕብ 9፡14)

**ለ/ ሌሎች መስዋዕቶች**

ዘሌዋዊያን 2፡1-7 የተጠቀሱት መስዋዕቶቸች የእንስሳ መስዋዕቶች አልነበሩም፡፡ እነዚህ መስዋዕቶች (በዘፍ 35፡14፣ ዘጸ 29፡40፣ ዘህ 6፡15 እና ዘዳ 32፡38) ተገልጸዋል፡፡ ሌሎች መስዋዕቶች እንደ እንስሳ መስዋዕት ክርስቶስን የሚያመለክቱ ሳይሆኑ መስዋዕት አቅራቢውን ወክለው ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ የእሳት ቁርባን ወይም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡ ስጦታዎች ናቸው (ዘሌ 2፡8-10)፡፡ ይህ መስዋዕት ይዘት (የጥራቱ ደረጃ) እንዲህ ተብሎ ተጽፏል «….ይህም ለእግዚአብሔር የሚሆን የእሳት ቁርባን ቅዱሳን ነው» ("a thing most holy")፡፡

**ሐ/ ካህናቶች (ዘሌ 8፡10)**

የመገናኛ ድንኳን ከተጠናቀቀ በኋላ (ዘጸ 40) እና ስለ መስዋዕቶቹ ሁኔታ (ዘሌ 1፡7) ከገለጸ በኋላ የፔንታቱክ ጸሐፊ ስለ ካህናቶች ቅድስና እና አገልግሎት ይናገራል። የካህናቶቹ ቅድስና በምዕራፍ 8፡6-30 የተገለጸ ሲሆን መቀደሳቸው በአራት መንገድ መሆኑን የምንባቡ ክፍል ይዘረዝራል።

የእንስሳው ደም ከመሰዊያው ላይ ተወስዶ በካህናቶቹ ጆሮ እጅና እግር ላይ ይቀባል። ጆሮ የእግዚአብሔርን ድምጽ በትክክል የሚሰማበት እጅ አገልግሎቱን እንዲሁም እግር ቅድስና የተሞላ ህይወት እና አኗኗር የሚወክሉ ሲሆን የክርስቶስ ኢየሱስ ደም ደግሞ ሁለንተናን በመቀደስ አሸናፊ ኑሮ እንድንኖር እና ለክህነት አገልግሎት ብቁ መሆን ያስችላል ብለው ምሁራን ያብራራሉ።

**3. መንፃት እና ሌሎች ህጎች**

**ሀ. መንፃት**

በአምስት የህግ መጽሐፍት «ፔንታቱክ» ውስጥ ቅድስና ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ጋር የመገናኛው መንገድ እርሱ ብቻ ከመሆኑ በተጨማሪ የእርሱ ቅድስና በህዝቡ ላይ እንዲታይ እግዚአብሔር በማቀዱ ነው። ይኸው ቅድስና እንደ አዎንታዊ ትዕዛዝ ሆኖ መቅረቡን በዘሌ 19፡2 እና በ1ጴጥ 1፡15-16 እንመለከታለን።

**አለመንጻትን የሚመለከቱ ጉዳዮች**

ንጽህና አልባ የሆኑ ነገሮች ንጹህ ባልሆነ እንስሳት፣ ሴቶች ንጹህ የማይሆኑበት ወቅት፣ የቆዳ በሽታዎች፣ ከሰውነት ከሚወጡ የበሽታ ፈሳሾች (ምልክቶች) እና በመሳሰሉት ነገሮች ተገልጿል። ቅድስና ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረንን ህብረት የማጠናከሪያ መንገድ መሆኑን ከማቴ 5፡8 እና ከዕብ 12፤14 የምንባብ ክፍሎች ላይ እንመለከታለን። ስለዚህ ከሐጢአት እና ከእርኩሰት መንጻት በእግዚአብሔር ለተጠራ ህዝብ መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር መሆኑን ያሳያል።

**ለ/ ቅዱሳን በዓላት (ዘሌ 23)**

የሰንበት ቀንና ሌሎች በዓላት ለእስራኤላዊያን የእግዚአብሔርን ቃል በመማር መንፈሳዊ ህይወታቸውን የሚያንጹበት፤ እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት እና እርስ በርስ የሚኖራቸውን ህብረት የሚያጠናክሩበት እንዲሆን ከእግዚአብሔር የተደነገገ መሆኑን ከተለያየ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መረዳት ይቻላል። ከሰንበት ቀን ውጪ ሰባት ዋና ዋና በዓላት የነበሩ ሲሆን ስያሜያቸው እና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙበት ክፍል እንደሚከተለው ነው።

1. **□□ሲካ በ□ል (23÷5)**
2. **□ቂ□ በ□ል (23÷6-8)**
3. **የመከር በኩራት በዓል (23÷9-14)**
4. **የጴንጤቆስጤ / የመወዝወዝ/ በዓል (23÷15-21)**
5. **መለከት የመንፋት በዓል 23÷23-25)**
6. **የስርየት ቀን (23÷26-32)**
7. **□□ስ በ□ል (23÷33-43)**

# ምዕራፍ አምስት

## ዘኁልቁ «እግዚአብሔርን ማገልገል»

## ትምህርት አስራ አንድ

### የዘኁልቁ መግቢያ

የዘኁልቁ መጽሐፍ የሚነግረን እግዚአብሔር ለህዝቡ ምን አደረገ የሚለውን ነገር ሳይሆን ለትልቅ ሃላፊነት እና ለልዩ አገልግሎት የመረጣቸውን ሰዎች ራሱ እግዚአብሔር ለህዝቡ ይፋ ያደረገበትን (ያስተዋወቀበተን) ሁኔታ ነው፡፡ ዋና ዋና ተብለው የሚጠቀሱት ሙሴ፣ አሮን፣ (ሊቀ ካህን)፣ ሌሎች ካህናት፣ ሌዋዊያን ናዝራዊያን እና የንገስታት ሁኔታ የሚያካትት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የዘህልቁ መጽሐፍ የሌዋዊያን አገልግሎት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት የሚችልበትን መንገድ የሚያሳየን መጽሐፍ ነው፡፡

በዚህ መጽሐፍ ንጽህና እና ቅድስና «cleanliness and holiness» ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች ሲሆኑ የእነዚህ ነገሮች አስፈላጊነት ለቀደሙት የእምነት ሰዎች ብቻ ሳይሆን የኛም ህይወት እና አገልግሎት በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚረዱ ጠቃሚ እሴቶች መሆናቸውን እንረዳለን፡፡

በመጨረሻም የእግዚአብሔርን ተስፋ ለመውረስ እምነት እና ታዛዥነት እንደሚያስፈልግ መጽሐፍ አበክሮ ይናገራል፡፡

### 1. የዘኁልቁ መጽሐፍ

### *ሀ/ ስያሜውና የታሪክ ሽፋን*

መጽሐፉ ስያሜውን ያገኘው በምዕራፍ 1ለ1-46 ባለው ምንባብ ክፍል ላይ ለሰልፍ (ለውትድርና) ብቁ የሆኑ ወንዶች የተቆጠሩበትን ሁኔታ መሰረት በማድረግ ቆጠራ «the numbers» ተብሎ «በሰፕቷጀንት»[10] መጽሐፍ ስያሜ አገኘ፡፡

በመጽሐፉ የመጨረሻ ክፍል በምዕራፍ 26፡1-51 በቃዴስ የቆዩባቸውን ዓመታት እና የገጠማቸውን ለማስታወስ ዕብራዊያን በምድረበዳ «in the wilderness» በዕብራይስጥ «ሚድባር» የሚል ስያሜ አለው፡፡ የዘሁልቁ መጽሐፍ 38-39 ዓመታትን የሚሸፍን መሆኑን (ዘኁልቁ 1፡1፤ ዘጸዓት 12፡39 እና ዘዳግም 1፡3) በማንበብ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም እስራኤላዊያን በሲና ተራራ አካባቢ የቆዩበት የጊዜ ርዝመት ማለት ነው፡፡

### 2. እስራኤል በሲና

*ሀ/ ቆጠራ እና ማደራጀት በሲና* (ዘኁ 1፡10)

[10] ሰብቷጀንት፡ በሰባ የአይሁድ ሊቃውንት ከእብራይስጥ ወደ ግሪክ የተተረጎመው የብሉይ ኪዳንን መጽሐፍት አጠቃልሎ የያዘ መጽሀፍ ነው፡፡

በዚህ ክፍል የተከናወኑት ተግባራት የህዝብ ቆጠራ ማድረግ እና ሰራዊቱ የሚሰፍርበትን ቦታ (የሰፈራ ቦታ) ለይቶ ማሳወቅ ሲሆን ሁለቱም ተግባራት ለጦርነት ዝግጅት ማድረግን ያመለክታሉ፡፡ ዝግጅቱም ከነዓንን በጦርነት ድል በማድረግ የተስፋውን ርስ (ምድር) ለመውረስ ነው፡፡ ይሁዳ የመሪነቱን ስፍራ መያዙ በዘፍጥረት 49፡8-10 የተነገረው ትንቢት መፈጸሙና ያመለክታል፡፡

በእግዚአብሔር ጥሪ እና በተሰጠው ስራ ክፍፍል መሰረት የመገናኛው ድንኳን እና በውስጡ ያሉትን ዕቃዎች (ንዋየ ቅዱሳቱን) መሸከም ከአራቱ የሌዊ ልጆች የሶስቱ ነበር፡- እነርሱም

- የቀዓት ልጆች (ዘኍ 4፡1-20)
- የጌዴሶን ልጆች (ዘኍ 4፡21-28)
- የሜራ ልጆች (ዘኍ 4፡29-33) ሲሆኑ የአሮን ልጆች የክህነቱን ስራ ያከናውኑ ነበር፡፡

**ትኩረት የሚሹ ነጥቦች**

- የህዝብ ቆጠራ (ዘኍ 1-2)
- የሚሰፍሩበት ስፍራ የንጽህና ሁኔታ (ዘኍ 5)
- የናዝራዊያን መለየት
  - የሚያሰክር ወይን ጠጅ አይጠጡም (ቁጥር 3-4)
  - ጸጉራቸውን አይቆረጡም (ቁጥር 5)
  - የሞተ ነገር አይነኩም (ቁጥር 6-7)
- የክህነት መሪዎች (ዘኍ 6፡22-27)
- የመሰዊያው ሁኔታ (7፡1-88)
- ካህናትና ሌዋዊያንን መሾም (ዘኍ 8)
- ከግብጽ ከወጡ በኋላ የመጀመሪያውን ፋሲካ አከበሩ (ዘኍ 9)
- የሲናን ተራራ መልቀቃቸው (ዘኍ 10) እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ስናጤን የዕብራዊያንን ከነዓን ለመግባት የነበራቸው ዝግጅት ምን ያህል የተሟላ እንደነበረ እንረዳለን፡፡

**3. ከሲና ወደ ቃዴስ በርኔ (ዘኍ 10፡11-13፡33)**

ዘኍልቁ 10፡13 ላይ እስራኤላዊያ ከሲና ተራራ መልቀቃቸውን የሚናገር ሲሆን የጉዞውን ቅደም ተከተል (ሁኔታ) ደግሞ ከቁ 14-28 ባለው የምንባብ ክፍል መመልከተ ይቻላል፡፡ በዚህ ወቅት የሙሴ አመራር አጣብቂኝ ወስጥ ገብቶ ነበር፡፡ ለዚህም ምክንያቱ

- የቅርብ ዘመዶቹ የሆኑት አሮንና ማሪያም
- ህዝቡ በሙሉ በሙሴ ላይ ባሳዩት ያልተገባ ባህሪ ምክንያት ነበር (ዘኍ 12 ፡1-5)

በምዕራፍ 13 እግዚአብሔር ሙሴን አስራ ሁለት ሰላዮችን ወደ ከነዓን እንዲልክ ትዕዛዝ ሰጠው (ቁ 1-16)፡፡ ሰላዮቹም ከአርባ (40) ቀናት በኋላ ወደ ሙሴ ተመለሱ (ቁ 17-25) የሰላዮቹም ሪፖርት ከቁ 26-33 በግልጽ ሰፍሮ ይገኛል፡፡

**የሰላዮቹን የስለላ ውጤት ያመጣው መከፋፈል**

- አንደኛው ቡድን ስለ ሰለሉት አገር ህዝቦች ታላቅነትና አስፈሪነት የሚገልጽ ሲሆን
- የሁለተኛው ቡድን ሪፖርት ደግሞ ምንም እንኳን የሰለሉት ሀገር ሰዎች በውጫዊ አካላቸው ግዙፍና አስፈሪ ቢመስሉም እስራኤላዊያን ማሸነፍ እንደሚችሉ የሚያብራራ ነበር፡፡

በእነዚህ በሁለቱ ቡድኖች በካከል ያለው ትልቁና መሰረታዊው ችግር እግዚአብሔርን በማወቅና በእርሱም በመታመን ላይ ያለ የመንፈሳዊነት ችግር ነው፡፡ የመጀመሪያው የሰዎችን ውጫዊ ማንነት በማየት ፍጻሜውን ሲወስን ሁለተኛው ቡድን ግን ከሰዎች ማንነትና ሁኔታ ይልቅ ትልቁን እግዚአብሔርን የሚያጎላን በእርሱም ላይ የሚታመን ማንነት ነው፡፡

**1. አለመታዘዝ እና ውጤቱ (ዘኍ 14)**

የህዝቡ ዓመጽ / አለመታዘዝ / እየጨመረና እየከፋ በመምጣቱ የእግዚአብሔር ቁጣ ተገለጠ፤ እግዚአብሔርም ለአባቶቻቸው ወደማልሁላቸው ምድር አይገቡም፡ በምድረበዳ ይሞታሉ ብሎ ተናገረ (ዘኍ 14፡ 23 እና 35)፡፡ አለመታዘዝ ሐጢአት ወደዚህ አለም የገባበት የመጀመሪያው ውድቀት መሆኑን በዘፍጥረት መጽሐፍ አይተናል፡፡

ከግብጽ ባርነት በእግዚአብሔር ጽኑ እጅ ነጻ ወጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲገሰግስ የነበረው ህዝብ ነገሩ ሁሉ ተገለብጦ እጅግ አስከፊ በሆነ ሁኔታ በምድረበዳ አሸዋ ተውጦ ይቀራል፡፡ ይህም የሆነው ህዝቡ የኢያሱን እና የካሌብን ጤናማ ሪፖርት ሳይሆን ስንፍና የተሞላውን እና የህዝብን ልብ የሚያቀልጠውን የአስሩን ሰላዮች ሪፖርት በመስማት እግዚአብሔር እና እቅዱን በመናቃቸው ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ለተቀሰቀሰውም ታላቁ አመጽ ምክንያት ሆኖ ለውድቀት ምክንያት ሆኗቸዋል፡፡ በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ አልፈው ከግብጽ ከወጡ ህዝቦች መካከል ወደ ተስፋይቱ ምድር የገቡ ሁለት ሰዎች ብቻ አሉ፡፡ እነርሱም ፡-

- ካልብ እና ኢያሱ ሲሆኑ (ዘኍ 14፡24-30) ሲሆኑ
- ከ20 ዓመት በታች የሆኑ በምድረበዳ የተወለዱ አዲሱ ትውልድ ናቸው፡፡

**2. አርባኛው ዓመት (ዘኍ 20፡36)**

በ20ኛው ምዕራፍ የሙሴ ዋና ዋና ረዳቶች ሞት እና የአዲስ ትወቅልድ ሁኔታ ተዘግቦ ይገኛል፡፡

ሀ/ የማሪያም መሞት (ዘኍ 20፡1)

ለ/ ተተኪው ትውልድ በሙሴና በአሮን ላይ ማጉረምረሙ (ዘኍ 20፡2-6)

ሐ/ የሙሴ ሐጢአት እና የእግዚአብሔር ቁጣ (ዘኍ 20፡7-13)

መ/ የአሮን በሆር ተራራ መሞት (ዘኍ 20፡20-29)

# ምዕራፍ ስድስት

## ዘዳግም፡- የምድረበዳ ቆይታ እና ማጠቃለያ

## ትምህርት አስራ ሁለት

### 1. የዘዳግም መግቢያ

በዘፍጥረት መጽሐፍ የተስፋው ህዝብ ምርጫ በዘጸዓት የተስፋውን ህዝብ መቤዠት (መዋጀት) በዘሌዋዊያን የተስፋውን ህዝብ የህያው አምላክ አምልኮ በዘኍልቁ የተስፋውን ህዝብ የምድረበዳ ዙረት (መንከራተት)፣ የዚህ ጥናት የመጨረሻ ክፍል በሆነው በዘዳግም መጽሐፍ ደግሞ የተስፋው ህዝብ የተስፋውን ምድር ለመውረስ የሚያደርገውን የእምነትና የመታዘዝ ዝግጅት እናያለን፡፡

የኦሪት ዘዳግም መጽሐፍ የዘሌዋዊያን እና የዘኍልቁ መጽሐፍት የያዙትን ሀሳብ በድጋሚ የሚያወራ እና የሙሴን የመጨረሻ ንግግር አካትቶ የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡ ህጉ በድጋሚ የተነገረበት መጽሐፍ ነው የሚባልበት ምክንያት መጽሐፉ ከዘኍልቁ አስራ አራት ከዘሌዋዊያን ደግሞ ሃያ ሁለት ምዕራፎችን አጠቃልሎ በመያዙ ነው፡፡

ይህ ወቅት ዕብራዊያን በምድረበዳ ከቆዩባቸው ዓመታት ውስጥ የመጨረሻዎቹ ዓመታት ሲሆኑ ወደ ከናዓን መግባት የናፈቁበት ወቅት ነው፡፡ በባላቅ ሴራ ምክንያት የበለዓምን ዕርግማን እንዲሁም በከነዓን የሚገጥማቸውን የጠላት ሰልፍ እንዳለ ቢረዱም ከነዓንን ለመውረስ ተነሳሽነት ነበራቸው፡፡

### ሀ. የትምህርቱ ዋና ዋና አላማዎች

ይህ ትምህርት ሲጠናቀቅ ተማሪው

- ⇨ ሙሴ ህዝቡን ለሚመጣው ወይንም ከፊታቸው ሊወርሱት ላለው ምድር ለማዘጋጀት እንዴት ያለፈውን ዘመን አጠቃላይ ሁኔታ እንደተረከላቸው ይረዳል
- ⇨ ለእግዚአብሔር መለኮታዊ አላማ መፈጸም የሰዎች መታዘዝና እምነት ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን ይረዳል
- ⇨ በህይወቱ ሊፈጸም ላለው መለኮታዊ አላማ ራሱን በቅድስና፣ በመተዘዝ እና በእምነት ያጎለብታል

### ለ. የመጽሐፉ አከፋፈል

- **ግምገማ** (retrospective) :- ላለፉት 40 ዓመታት በምድረበዳ ያሳለፉትን ሁኔታ መግምገም ወይንም የከፋን ማሰላሰል (ዘዳ 1-26)
- **ራስን ማየት** (introspective):- አዲሱ ትውልድ ህይወቱን /ራሱን እንዲመረምር ማድረጉ (ዘዳ 27-30)

- **ወደፊት ማየት** (prospective) ስለመጪው ዘመን ቅድመ ግንዛቤ ማግኘት ወይንም ወደፊት ማየት (ዘዳ 31-34)

**ሐ. የመጽሐፉ ዝርዝር ይዘትና አበይት ተግባራት**

1. ያለፉት አርባ አመታት በአዲሱ ትውልድ እይታ
    - እግዚአብሔር የሰጣቸውን ስኬት (1፡6-8፣ 9-18፣ 1፡19-2፡1፤ 2፡2-23፤ 2፡24-37፤ 3፡1-11፤ 12-20፤ 23-29)
    - ሀዘን እና ደስታ
    - የቆሬ ልጆች አመጽ (ዘኍ 16)

ሙሴ ለህዝቡ እያሳያቸው ያለው የእነርሱ ያለፈው ድል ለሚመጣው ዘመን ድል አመላካቸው ነው፡፡ (ዘዳ 3፡1-11) እነርሱ በእግዚአብሔር በመወደዳቸውና እነርሱ ከእርሱ ጋር ባላቸው ህብረት ምክንያት ከሰዎች ሁሉ የተለዩ መሆናቸውን ይነግራቸዋል፡፡

2. አዲሱ ትውልድ ራሱን እንዲመረመር (ዘዳ 29፡26-30)
    - ለሁለተኛ ጊዜ የህዝብ ቆጠራ መደረጉ (የቆጠራው የተደረገበት ምክንያት በቁጥ 54 ተልጿል)
    - በግብጽ ምድር የእስራኤላዊያን ቁጥር ከግብጻዊያኑ መብለጡ እና በደረሰባቸው መቅሰፍት ምክንያት በምድረበዳ ቁጥራቸው በጥቂቱ ማነሱ በዚሁ ክፍል ተገልጧል፡፡
3. ስለመጪው ዘመን ቅድመ ግንዛቤ ማግኘት (ዘዳ 31-34)
    - ወደ ከነዓን ለመንዝ የተደረገ ቅድመ ዝግጅት
    - የቤተሰብ አስተዳደር መመሪያ (ዘኍልቁ 27፡1-5)
    - ሌዋዊያን የሚያቀርቡት መስዋዕት (ዘኍ 28-29)
    - ዘኍልቅ 30 የተገለጹት መሃላዎች
    - በዘኍልቁ 29፡12-34 በዳስ በዓል ወቅት ስለሚቀርቡ ሰባት በዓላት እና በመሳሰሉ ጉዳዮች በድጋሚ ህጉ መሰጠቱን እንመለከታለን፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት የመጀመሪያው ትውልድ በምድረ በዳ ስላለቁ ለአዲሱ ትውልድ እንደገና ማሳወቅ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

**2. የቃልኪዳኑ እንደገና መስፋት (ዘዳ 5-26)**

ሙሴ ህጉን በህዝቡ ልብ ለማኖር እንደገና ስልታዊ በሆነ መንገድ ይገልጽላቸዋል፡፡ የዚህ ክፍል ቁልፍ ሐሳብ በዘዳግም 6፡4-5 ላይ የተገለጸው እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ ማምለክ የሚለው ነው፡፡ በእርግጥ ይህ ቃል የብሉይ ኪዳንን አስተምህሮ ህግ ሁሉ ጠቅልሎ የያዘ ነው፡፡ ኢየሱስም እንደ ብሉይ ኪዳን ህግ ማጠቃለያ አድርጎ ጠቅሶታል፡፡ (ማቴ 22፡37-48)

**3. መርገምና በረከት (ዘዳ 27-28)**

እግዚአብሔር በረከትና መርገም ለመግለጽ ሁለት ተራሮችን ተጠቅሟል፡፡

- የጌባል ተራራ የመርገም ምልክት ሆኖ ቀርቧል
- ገሪዛን ተራራ ደግሞ የበረከት ምልክት፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እና ሳምራዊቷ ሴት ሐሳብ የተለዋወጡበት ስለዚህ ተራራ ነው፡፡ (ዮሐንስ 4)

ይህ ህዝቡ የሚባረክበት የበረከት ተራራ ወደ ኋላ ዘመን ለአይሁድና ለሳምራዊያን የመከራከሪያ ቦታ ሁኗል፡፡ (ዘዳ 12፡5 እና ዮሐ 4፡20)

አይሁድ ኢየሩሳሌም ትክክለኛ የአምልኮ ማዕከል ናት ሲሉ ሳምራዊያን በበኩላቸው ጂሆቫን ለማምለክ የገሪዛን ተራራ እውነተኛው ወይንም ትክክለኛው ስፍራ ነው ይላሉ፡፡

በረከትም ሆነ መርገም በህዝቡ ምርጫ ላይ ተንተርሶ የሚታይ ነው፡፡ ህዝቡ ለመታዘዝና ላለመታዘዝ ፣ ወይንም በየትኛው ጎዳና መሄድ እንደሚገባው ሲወስን የሚገኘው ነው፡፡ በእርግጥ በህይወታችን ልዩነትን የሚፈጥረው ምርጫችን ነው፡፡

4. **የሙሴ የመጨረሻ ንግግር (ዘዳ 32 እና 33)**

**ሀ. ዘዳግም 32 የሙሴ መዝሙር**

ለምን ይሆን ሙሴ የመጨረሻውን መልዕክት በዝማሬ ሊያስተላልፍ የወደደው? መዝሙር ለረዥም ጊዜ በልብ የመቆየት ባህሪይ ስላለውና በቀላሉ ማስታወስ ስለሚቻል ነው፡፡ ስለዚህም ሙሴ ህጉን እንዳይረሱና በቀላሉ ማስታወስ እንዲችሉ ያደረገው ይሆናል፡፡ ከዚህ የመዝሙር ባህሪ ተነስቶ ነው ሙሴ ከፊት ለፊታቸው ስላለው ክህደት ወይንም መንፈሳዊ መንሸራተት በዝማሬ ሊያስጠነቅቃቸው የወደደው፡፡ መዝሙሩን በዘመሩ ቁጥር ትንቢታዊ መልዕክቱን በማስታወስ ያሉበትን ሁኔታ ይገመግማሉ፡፡ ዝማሬው የጣኦታትን ባዶነት ያነሳል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአይሁድን አምላክ የጂሆቫን ታላቅነት ያሳያቸዋል፡፡ በመሆኑም ክህደት በጥብቅ ተከልክሏል፡፡ ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ አምልኮተ እግዚአብሔር ለእስራኤል ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን እንደ አዎንታዊ ግዴታም / ትዕዛዝ (positive command) መሆኑን በማሳየት በተቃራኒው ደግሞ የቃል ኪዳን ህዝብ ከጣዖት ጋር ምንም ዓይነት ህብረት እንዳይኖረው ያስጠነቅቃል፡፡

**ለ. የነገዶች መባረክ (ዘዳ 33)**

ሙሴ አስራሁለቱን ነገዶች የባረከበት የምንባብ ክፍል ነው፡፡ ሙሴ ከአርባ አመት የመሪነት አገልግሎቱ በኂላ ከመካከላቸው የሚጠፋበት ጊዜ ሲደርስ ትንቢታዊ በሆነ በረከት መባረኩን የሚሳይ ታሪክ ነው፡፡

የቀደሙት አባቶቹ ይስሐቅና ያዕቆብ በየበኩላቸው ትውልዳቸውን ባርከዋል፡፡ ትልቁ የወንጌል ሰው ሐዋሪያው ጳውሎስም የኤፌሶንን መሪዎች ከፊታቸው ስለሚመጣው የሐሰት አስተምህሮ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ከነገራቸው በኂለ ለታመነው ለእግዚአብሔር ቃል እና ለመንፈስ ቅዱስ አሳልፎ ይሰጣቸዋል፡፡ ይህም ታላቅ መሪ እያደረገ ያለው ይህንኑ ነው ታላቁን ህዝብ ለእግዚአብሔር አሳልፎ ይሰጣል፡፡

በረከቱ በህዝቡ መልካምነት ወይም በሙሴ ደግነት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በመሆኑም የእግዚአብሔር ድምጽ የሚሰማ መሪ በመሆኑ ትንቢታዊ መልዕክት ለመላው እስራኤል በረከት አስተላልፏል፡፡

**ሐ/ የሙሴ ሞት (ዘዳ 34)**

ሙሴ ከሚወደው ህዝብ መካከል ሊወሰድ ተቃርቧል፡፡ ይህንን ታላቅ ሰው በነበረው ጠንካራ ማንነት ኢየሱስ ክርስቶስ በተደጋጋሚ ጠቅሶታል፡፡ እኛም ከህይወቱ ብዙ የምንማረው መንፈሳዊ ነገር አለ፡፡ የመሪነት ብቃቱ የተለየና የሚያነቃቃ ነው፡፡ ከእኛ በፊት በነበሩት እና እኛም እንደምናስበው ሁሉ ቀጣዩም ትውልድ የሚያስበው ታላቅ መሪና መልካም ምሳሌ የሚሆን የእግዚአብሔር ሰው ነው፡፡

ስለ ሙሴ ሞት እና ተያያዥ ስለሆኑ ነገሮች ብዙ መናገር የሚያስችሉ ሁኔታዎች አናገኝም (ስለ አሟሟቱ እና ስለ ቀብሩ ሁኔታ) ቁጥር 5 እና 6 ከምናነበው ትንሽ ሃሳብ በቀር፡፡ ይሁንና ስለአሟሟቱ የተጠቀሱት ጥቂት ሀሳቦች ቢሁኑ በኢያሱ ስለመጻፋቸው ብዙ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡

**መ. ኢያሱ የሙሴን የመሪነት ስፍራ ተረከበ**

ኢያሱ በሞዓብ ምድረበዳ የሙሴን የመሪነት ስፍራ ይረከባል፡፡ ኢያሱም ህዝቡን ከነዓንን እንዲወርሱ ህዝቡን በመምራት ዮርዳኖስን ያሻገራቸው መሪ ነው፡፡

የአርባ አመቱም ህልም ተስፋን በሰጠው በራሱ በእግዚአብሔር ብቃት ፍጻሜን አገኘ፡፡

**ሠ. የዘዳግም መጽሐፍ ማጠቃለያ**

የሙሴ ህግ በሃይማኖታዊ እና ህዝባዊ የመተዳደሪያ ህጎችን የያዘ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ምዕራፍ 6፡ እስራኤል እግዚአብሔርን መውደዷ የሚያስገኘ ጥቅም

ምዕራፍ 7፡ ከተስፋይቱ ምድር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሃሳቦች

- ከአህዛብ አማልክት እንዲለዩ (ቁጥር 1-6)
- ከነዓንን የመውረስ መብት
- እስራኤልን ከነዓንን የምትወርሰው በእግዚአብሔር እርዳታ ነው፡፡ (ቁጥር 17-24)

ምዕራፍ 12 የአምልኮ ቦታ

ምዕራፍ 13 ጣዖትን ማምለክ እና ሀሰተኛ ትምህርት የሚያስከትለው ቅጣት

ምዕራፍ፡ 14-26 ለቅዱስ ህዝብ የተሰጡ መመሪያዎች

ህዝበ እስራኤል እግዚአብሔር ሁሉ ነገሩ ነው፡፡ ስለዚህም እንደእግዚአብሔር ያለ ማንም እንደሌለ መገንዘብና ለዚህም እውነት እውቅና በመስጠት የሚጠበቅባቸውን ሊያደርጉ ይገባል፡፡ እስራኤል ግብጽ መኖሪያው አልነበረም፣ ከነዓንም ዘላለማዊ መኖሪያው አይሆንም፤ እግዚአብሔር ግን ዘለዓለማዊ መኖሪያው ነው፡፡ (ዘዳግም 33፡26-27)

# ማጠቃለያ

ከአምስቱ የህግ ወይንም የሙሴ መጽሐፍት ብዙ አስደናቂ እውነቶችን እና ለክስተቶችን አይተናል፡፡ የነገሮች ጅማሬ ከሆነው ከዘፍጥረት፣ ነጻ መውጣትና ህግጋትን ከዘጸዓት፣ የክህነትን ወይንም የድንኳን አገልግሎት ከዘሌዋዊያን፣ የህዝብ በምድረበዳ የመንከራረት እና የእግዚአብሔርን ፍርድ በዘኁልቁ እንዲሁም የህጉ እንደገና ለአዲስ ትውልድ መሰጠት በዘዳግም አይተናል፡፡ ከእንዚህ በተጨማሪ የእግዚአብሔርን ተዓምራት አድራጊነት ምህረት እና ሌሎችንም ባህሪያት ተመልክተናል፡፡ ከታች በጥቂቱ የዘረዘርናቸው ስነመለኮታዊ ጠቀሜታ ያላቸውን አስተምህሮዎችንም ተምረናል፡፡

## የአምስቱ የሙሴ የህግ መጽሐፍት ስነ መለኮት

1. እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው
2. ሐጢአት እና የመቤዠት ተስፋ እና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡
3. እምነት እና መታዘዝ
4. በእምነት የተገኘ ጽድቅ
5. የእግዚአብሔር መለያ ባህሪያት
   - የእግዚአብሔር ቅድስና ከዚህም የተነሳ የእስራኤል ህዝብ ሁሉ ቅዱስ እንዲሆኑ ትዕዛዝ የተሰጠበት (ዘሌ 19፡2)
   - የካህናት መንግስትና ቅዱስ ህዝብ በካህናት መሪነት በቤተመቅደስ (በመገናኛው ድንኳን) ቅዱሱን እግዚአብሔርን በማምለክ በሌሎች አማልክትና ህዝቦች ዘንድ ልዩነትን እንዲፈጥሩ ሲያደርግ (ዘጸ 19፡5)
   - የእግዚአብሔር በሲና ተራራ በቅድስና መገለጥና የህዝቡ ወደ ቅድስናው ስፍራ እንዳይቀርቡ መከልከል፡፡ (ዘጸ 3፡15፣19፡11-13)
   - ቅድስናው ከሉዓላዊነቱ አኳያ
6. መስዋዕት እና የክህነት አገልግሎት
7. የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት
8. ቃል ኪዳን
9. የእግዚአብሔርን ፍርድ እና ሌሎችንም ስነመለኮታዊ ጠቀሜታ ያላቸውን እውነቶች እናገኛለን፡፡

በመጨረሻም አምስቱ የህግ መጽሐፍት የያዙትን መንፈሳዊ እውነቶች ለግልና ለቤተክርስቲያን ጥቅም ለማዋል በግል እና በቡድን ሆነን በጥንቃቄ በማጥናት እንድትጠቀሙ እናበረታታለን፡፡

# Bibliography

Allis, Oswald T. God Spake by Moses. Philadelphia: The Presbyterian and Reformed Publishing Company, 1975.

Argaw Zelelew, Pentatuche, unpublished handout, Addis Ababa, 2003.

Assad, George. Pentatuch. Irving, Texas: ICI (third edition), 1988.

Barabas, Steven, associated. The Zondervan Pictorial Bible Dictionary. Grand Rapids, Michigan L: Zondervan Publishing House, 1967.

Cohen, Rabbi Harry A. A Basic Jewish Encyclopedia, Hertford, Connecticut: Hartmore House, 1965.

Free, Joseph P. Archaeology and Bible History, Wheaton, Lllinois: Van Kampen Press, 1950

Greve, Fred J. Old Testament Survey. Brussels, Belgium: International Correspondence Institute, 1975.

Holdcroft, L. Thomas. The Pentateuch. Oskland, California: Western Book Company, 1966.

The Intereter’s Bible. Vol.1. New York: Abingdon-Cokesbury Press, 1952.

Livingston, G. Hebert. The Pentateuch in Its Cultural Environment. Grand Rapids, Michigan: Baker Book Hous 1974.

Mackintosh, C.H. Genesis to Deuteronomy. Neptune, New Jersey: Loizeaux Brothers, Neptune, 1972.

Manley, G.T. The New Bible Handbook. London: The Inter-varsity Fellowship, 1947.

Mears, Henrietta C. What the Bible Is All About. Minneapolish, Minnesota: The Billy Graham Evangelistic Assocation 1966.

Morgan G. Campbell. The Unfolding Message of the Bible. Westwood, New Jersey: Feleming H. Revell Company 1961.

The New Bible Dictionary, Grand Rapids. Michigan: Wm. B. Eerdmans Publishing Co., 1962.

Scroggie,W. Graham. The Unfolding Drama of Redemption. Vol.1. Grand Rapids, Michigan: Zondervan Publishing House, 1953.

Tenney, Merrill C. The Zondervan Pictorial Bible Dictionary. Grand Rapids, Michigan: Zondervan Publishing House, 1967.

Unger, Merrill F. Unger’s Bible Dictionary. Chicago: Moddy Press, 1961.

መስፍን ሙሉጌታ ፔንታቱክ ያልታተም፡ አዲስ አበባ 2005